# ከአክራሪ እስልምና ወደ ክርስትና

እውነተኛ ታሪክ

ከ
ናህድ ማሕሙድ ሙትዋሊ

አርተር

ዲያቆን ዳንኤል ክብረት

2001 ዓ.ም.

© ዲያቆን ዳንኤል ክብረት

አዲስ አበባ፣ 2001 ዓም

የመጀመርያ እትም ኅዳር 2001 ዓ.ም.
ሁለተኛ እትም ጥር 2001 ዓ.ም.
ሦስተኛ እትም የካቲት 2006 ዓ.ም.

አሳታሚና አከፋፋይ

አግዮስ ኅትመትና ጠቅላላ ንግድ ሥራ ሐላ/የተ/የግል ማኅበር

አድራሻ፡- አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

መገናኛ፣ለም ሆቴል አጠገብ፣ማትያስ ሕንፃ፣ ቢሮ ቁ. 404

ስቁ፡- 251 911 098254/ 011- 663 9902

ኢሜይል፡- danielk@gmail.com

ገጸ ድር፡- www.agyos.com





መታሰቢያነቱ

ለቅኑ ሰው

ለአሥራት ከበደ

ይሁን

# የተርጓሚው ማስታወሻ

ቤካ መገርሳ የሚባል አንድ ወንድም አለኝ:: የሚኖረው በአሜሪካ ሚንያፖሊስ ከተማ ነው:: እኔ ሚንያፖሊስ በገባሁ ቁጥር እርሱ ወደ አንዱ የኢትዮጵያውያን ምግብ ቤት አይደለም ለግብዣ የሚወስደኝ:: Light and life Publishing ወደ ተባለው ክርስቲያናዊ መጻሕፍትን ወደሚያሳትመው ድርጅት ነው ይዞኝ የሚያመራው::

በ1999 ዓም በሄድኩ ጊዜ ከገዛልኝ መጻሕፍት አንዱ Islam encounters Christ የሚል ነበር:: አንዲት አክራሪ የነበረች ሙስሊም እኅታችን ተአምራዊ በሆነ ራእይ አማካኝነት እንዴት ክርስቲያን እንደ ሆነች ይተርካል:: ይህንን መጽሐፍ እዚያው ሀገሬ ስገባ ተረጋግቼ አነብበዋለሁ ብዬ ቆጠብኩት:: በልዩ ልዩ የአሜሪካ ከተሞች ስዘዋወር ዕድል ገጥሞኝ ወደ ግብጽ ቤተ ክርስቲያን ጎራ ካልኩ እዚያ የማገኛቸውን ካህናት ስለ ናህድ ማሕሙድ ሙትዋሊ ሳልጠይቃቸው አልቀርም ነበር:: በዚህ አጋጣሚም ሴትዮዋን በአካል የሚያውቋት ሁለት ካህናት አግኝቻለሁ::

የናህድ የምስክርነት መጽሐፍ መጀመርያ የታተመው ሲሆን «ክርስቶስን አገኘሁት» በሚል ርእስ በዐረብኛ ነበር የታተመው:: ይህ መጽሐፍ ወደ ፈረንሳይኛ፣ ጀርመንኛ ደች እና ሮማንያኛ ተተርጉሟል:: እነሆ ዛሬ ደግሞ አማርኛ ዕድል ደረሰው ማለት ነው::

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የአንዳንድ ሰዎች ስሞች ቀርተዋል፤ የሌሎች ሰዎች ደግሞ ተለውጠዋል:: ይህም የሆነው ለሰዎቹ ደኅንነት ሲባል መሆኑን የመጀመርያዎቹ ተርጓሚዎች ገልጠዋል:: ታሪኩ በእውነት የተፈጸመ መሆኑን እኔም ካገኘኋቸው ግብጻውያን አበው እንዲሁም በኢንተርኔት አማካኝነት ከሚገኙት መረጃዎች ለማረጋገጥ ተሞክሯል::

ናህድ በአሁኑ ጊዜ ዋና መኖርያዋ ሆላንድ ሲሆን በተለያዩ የዓለም ክፍሎች በመዘዋወር ስለ እምነቷ ምስክርነት ትሰጣለች:: ከሆላንድ በምታዘጋጀው የቴሌቭዥን ፕሮግራምም ብዙዎችን ለውጣለች:: በስሟ በጉግል መኅልኅያ ብታስሱ አያሌ መጻሕፍቷንና የቪዲዮ ፕሮግራሞቿን ማግኘት ይቻላል::





# የባለ ታሪኳ ማስታወሻ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፣ አሜን::

ስቃወመው እና ሳሳድደው የነበረውን እምነት ዛሬ በጽናት እንድመሰክርለት ጸጋውን የሰጠኝ ጌታ እግዚአብሔርን አመሰግናዋለሁ:: ለእግዚአብሔር አብ እና በመከራችን ወቅት ረድኤቱ ለማይለየን ፣እኔን ትጉቱ ባርያውን ለእናንተ መጽናኛ እሆን ዘንድ ለፈቀደ ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምስጋና ይገባል::

ይህንን ሁሉ ያደረገልኝ ስለ በጎ ሥራዬ አይደለም፤ ለእናንተ ድኅነት ሲባል በእኔ ላይ ባደረው በእግዚአብሔር ጸጋ ምክንያት እንጂ:: ዘወትር እግዚአብሔርን አክብሩት፣ በእኔ ያደረገውን ድንቅ ሥራውንም አስቡ፣ እኔን ሰው ሰብኮ አልመለሰኝም:: እምነቴን ያገኘሁት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ከራሱ ነው:: ዛሬም ዘወትርም ክብር ምስጋና ለእርሱ ይሁን፤ አሜን::

ይህንን ምስክርነት የምጽፈው በእግዚአብሔር ፊት ነው:: እንደ ማልዋሽ እርሱ ያውቃል:: የእግዚአብሔር ሥራው እንዴት ድንቅ እንደ ሆነ፤ በእኔም ላይ ያደረገውን ድንቅ ሥራ እመሰክራለሁ::

ጌታ ሆይ ስምህን ለመስደብ አንደበቴ ፈጣን እና ያልታረመ ነበር:: አንተ ግን ያንተ በግ አደረግከኝ:: ከአሁን በኋላ ራሴን ለአንተ አሳልፌ ሰጥቻለሁ:: አንተን ለዓለም እሰብካለሁ:: ከአሁን በኋላ የእኔ ሳይሆን ያንተ ፈቃድ ይሁን:: ሁለመናዬ ያንተ ነው:: ይህ መሆኑ ብቻ ለእኔ በቂዬ ነው:: ሌላ ተጨማሪ ነገር አልጠይቅህም:: ከፈቃድህ ውጭ አንዳች ነገር አደርግ ዘንድ አሳልፈህ አትስጠኝ:: እባክህን በልቡናዬ ያለው ፍቅርህ ይምራኝ::

መስማትንስ በጆሮዬ ሰምቼ ነበር፤ አሁን ግን ዓይኔ አየችህ፤
(ኢዮብ. 42÷25)

# የዘመናችን ገድል

## ከዲያቆን ብርሃኑ አድማሴ

የኔታ ከሚመልሱልኝ መልሶች ውስጥ እየጸነነኝ /እውነትነቱን እየተጠራጠርኩ/ የተቀበልኩት አንድ ነገር ነበር። «አንዳንድ በቁርዓኑ የበቁ እስላሞች መጨረሻ ላይ ጠፍተው ገዳም እየገቡ ተጠምቀው ያርፋሉ፤ በእኛ ሀገርም እንደ ዋልድባ ባሉት ገዳማት የተፈጸመበት ጊዜ አለ» ያሉኝን።

ነገሩ እንዲህ ነው። እንደ ዲማ ጊዮርጊስ ሁሉ በዘመነ መሳፍንት ቅባቶችና ጸጐች ያልረገጡት ሌላው ቦታ ደብረ ሃይማኖት መካነ ኢየሱስ ነው። ታዲያ አሥራ አንደኛ ክፍል ከሆንኩበት ጊዜ አንሥቶ ለሦስት ዓመታት ያህል በዚሁ ታላቅ ደብር የመጻሕፍት ትርጓሜ ከሚያስተምሩት ከየኔታ ኃይለ ሚካኤል ዘንድ እየሔድኩ አንዳንድ ትምህርቶችን እማር ነበር። እኔ የምማረው መጽሐፍ ባይኖርም፣ በጉባኤ ተቀምጠን እንሰማለን፤ ጥያቄም እንጠይቅና እንረዳለን።

በየኔታ ቤት እጅግ ብዙ መጻሕፍት ስላሉ ከእነርሱ አንዱን እቀበልና አነባለሁ። የመጻሕፍት ተማሪዎችም በወንበር ያሔዱትን /የተማሩትን/ ሲቀጽሉ /ሲያጠኑ/ ይውላሉ። ቦታው የመጻሕፍት ትርጓሜ ቤት በመሆኑ ነው መሰል የማታው ጸሎት የሚካሔደው በዜማ ሳይሆን በቁጥር /እየተዞረ እየታደለ/ ነው። ታዲያ እንደ ጉባኤ ቤቱ ሥርዓት ውዳሴ ማርያም፣ መልክአ ማርያም፣ መልክአ ኢየሱስ፣ መልክአ ጊዮርጊስ እና መልክአ ሚካኤል ከተጸለየ በኋላ ዳዊትና ነቢያት ይታደላሉ። ይህ ካለቀ በኋላ እዚያው ጉባኤ ቤቱ በር እንደተቀመጥን ሲቀጽል የዋለ ተማሪም እኔም ካነበብሁትና ካዳመጥሁት ጥያቄ እናቀርባለን። ይህ ሰዓት ከወንበሩ /ከመደበኛው የመጻሕፍት ትርጓሜ ሰዓት/ ውጭ ስለሆነና ለጥያቄ የተጋለጠ በመሆኑ እንወደዋለን።

በአንድ ወቅት ከየኔታ መጻሕፍትን ወስጄ ለማንበብ ሳማርጥ ቁርዓን አገኘሁ፤ እናም ትንሽ አነበብኩለት። በሁኔታው ተገርሜ ነበርና ማታ በተለመደው ሰዓት ጊዜ ጥያቄዬን አቀረብኩ። ያን ጊዜ የጠየቅሁትን ቃል በቃል ባላስታውሰውም እንዴት ቁርዓን ሊያነብቡ እንደቻሉ መጠየቄ ትዝ ይለኛል። የኔታም በቁርዓን ውስጥ ስላለው በተለይም የቁርዓኑን «ሱረቱ አል መርየም» እና የመሳሰሉትን ገልጸው ነገሩኝ። እኔም ደግሜ ጠየቅሁ። ታዲያ በቁርዓን ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እና ስለ እመቤታችን ከተጻፈ በመጽሐፍ ቅዱስ ግን ስለ ቁርዓንም ስለ መሐመድም ካልተጻፈ ተራው ሰው እንኳ ቢቀር እንዴት የተማሩት ሙስሊሞች በክርስትና አያምኑም አልኩኝ። በዚህ ጊዜ ነበር የኔታ «በመንፈሳዊነት እና በእውነት ቁርዓኑን የሚመረምሩት እኮ የኋላ የኋላ ወደ እውነቱ እየደረሱ ተደብቀውም ቢሆን ይጠመቃሉ። እንዲያውም አንዳንዶቹ እንደ ዋልድባ





ባሉት ገዳማት እየገቡ በዚያው ቶሎ ለብቃት ይደርሳሉ፤» ብለው ተንትነው ያስረዱኝ።

ለጊዜው አልተዋጠልኝም። እርሳቸው ግን «ያልተረዱትን ነገር «መንክር መንክር» ብሎ አድንቆ ጸልዮ ሲያልፉት የተሰወረውን በኋላ እግዚአብሔር ይገልጠዋል» የሚለውን ምክራቸውን እና ትምህርታቸው ለገሡኝ። እኔም ምክራቸውን ተቀብዬ «መንክር ወዕፁብ» ብልም ለብዙ ዓመታት ያህል ግን ትምህርታቸውን ልረዳው አልቻልኩም ነበር።

ይህን ነገር በልቤ ይዤው በምኖርበት ጊዜ «ኢትዮጵያ የዓለሙ መፋረጃ» የሚለው የንቡረ ዕድ ኤርምያስ መጽሐፍ ታትሞ ወጣና አነበብኩት። በዚህ መጽሐፍ ከገጽ 297-299 አንድ ታሪክ አገኘሁ። ታሪኩ ቀድሞ ሼክ ዘከርያ የሚባሉ አንድ ሙስሊም ወንድማችን ቁርዓንን በጥብዓት ሲመረምሩ እንደ አብርሃም ያለ ኀሊና ይመጣባቸዋል።

አብርሃም ከአባቱ ተቀብሎ የተሸከመውን ጣዖት መርምሮ ደካማነቱን ዐውቆ ወደ እግዚአብሔር እንደ ደረሰው ሁሉ፤ እርሳቸውም ከአባቶቻቸው የወረሱትን ቁርዓን ሲጠይቁት የአምላክነት መልስ አልሰጣቸው ይላል። በዚህ ምክንያት ተቀንጫጭቦ የተጠቀሰውን የጌታንና የእመቤታችንን የታሪክ ጭራ ይዘው ወደ እውነተኛው ብርሃን ወደ ወንጌል ብቅ ይላሉ። ተጠምቀው ቁርዓንን በማስረጃነት እየጠቀሱ፣ ወንጌልን ለመስበክ እንደበቁ የንቡረ እድ መጽሐፍ ይተርካል። በዚህ ጊዜ የኔታ ያሉኝ ነገር እውነት መሆኑን በመረጃ ደረስኩበት። መጻሕፍትን በማንበቤ እንደዚያ ቀን የተደሰትኩበትን ቀን አላስታውሰውም። ይህም ሆኖ ግን አንድ ፍላጐት በውስጤ ነበር። «ምን አለ በእኛ ዘመን ተፈጽሞ ብናየው» የሚል።

በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ የጅማና የኢሊባቦር ጭፍጨፋዎች ሲከሰቱ እንደገና አለቃ ዘካርያስን ተመኘኋቸው። እርሳቸውንም በሥራዎቻችን እያስታወስናቸው እያለን ዲ/ን ዳንኤል ክብረት የዚህን መጽሐፍ ረቂቅ እንዳነብለት ሰጠኝ። መጽሐፉን እንደ ልብ ወለድ ቶሎ ጨረስኩት። በርግጥም የኔታ «በጊዜው ጥያቄህን ይመልስልሃል» ያሉኝ ደረሰ። አንድ ሌላ ሰው ከቁርዓን ተነሥቶ ወደ ወንጌል ብርሃን ሲገባ በዘመናችን ለማየት በቃሁ። በዚህም «ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ዘላለሙም ያው ነው» ያለው ቃለ መጽሐፍ መተግበሩን አረጋገጥኩ። «ትናንት» በሕገ ልቡና እነ አብርሃምን እንደጠራ እንደለየ፣ በዘመነ ሥጋዌውም እነ ማቴዎስን፣ ራሱን ቅዱስ ጳውሎስን እንደጠራ እንደለየ፣ ከዚያም ወዲህ «ዛሬ» እነ ናሕድን ሲጠራና ሲመልስ በዘመናችን አየን፤ ሰማን። በዚህም ራሱ ጌታ «አባቴ እስከ ዛሬ ይሠራል፣ እኔም ደግሞ እሠራለሁ» በማለት ለአይሁድ የመለሰላቸውን መልስ እናስታውሳለን ዮሐ. 5፥17። ከናሕድ ሙሐመድ ልዩ ግለ ታሪክ /Special auto Biography/ የምናየውም ይኸንኑ ድንቅ የእግዚአብሔር ሥራ ነው።

በዚህ መጽሐፍ የተገለጸው የናሕድ ታሪክ እጅግ ብዙ ነገሮችን የሚያስተምር ነው። የመጀመሪያውን ደረጃ የሚይዘው እንደ ጥንቱ ዘመነ ክርስትና የዘመናችንንና ተጨባጩን የግብጽ ሁኔታ የሚያሳይ ተጋድሎ /ወይም

የዘመናችንን ገድል/ ለማየት ዕድል ይሰጣል። ልብን በሚማርክ አተራረክ በቀረበው በዚህ መጽሐፍ አዲስ የክፍለ ዘመናችንን ገድል ቁልጭ አድርገን እናያለን። ምክንያቱም የመጽሐፉ አተራረክ በጊዜ ቅደም ተከተል የሚፈጸም ድርጊትን ተከትሎ በየተጋድሎው ያለውን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መገለጥ ያሳያል። ከዚህም በላይ በዘመናችን ቴክኖሎጂው፣ ሥልጣኔውና ውስብስብ ማኅበረሰብ ባለበት ካይሮን በመሰለ ቅልጥ ያለ ከተማ፣ የስለላ፣ የደኅንነትና የቁጥጥር ሥርዓቱም ሆነ የመረጃ መሰብሰቢያው ዘዴ እንዲህ በረቀቀበትና በዚህም በማይታማው የግብጽ እስላማዊ መንግሥት አስተዳደር ውስጥ ያንን ሁሉ የሚያሳልፈውን የእግዚአብሔርን ርዳታ፣ ከእግዚአብሔር ጋር የሚደረግን የቃል በቃል ንግግር ስለሚያሳይ ለእኔ ከዚህ የተለየ የገድል መጽሐፍ የለም። ይህም ልቡና ላለው ሰው የትናንቱን ገድል በገቢር የሚያሳይ ትልቅ የመፍትሔ ደወል ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ የዘመናችን ቤተ ክርስቲያን በዚህች ልውጥ ክርስቲያን የሕይወት ውጣ ውረድ ውስጥ ፍንትው ብላ ትታየናለች። ቤተ ክርስቲያን ዘክርስቶስ ዛሬም እንደ ሐዋርያት ኃላፊነታቸውን ያልዘነጉ፣ መከራውን ሁሉ ተቋቁመው በጎቻቸውን የሚጠብቁ፣ የሚመግቡም ካህናት አሏት። በዚያው መጠን ደግሞ ከሺሕ ዘመን በኋላ «ዲያብሎስ ከእሥራቱ ይፈታል» የተባለውን ቃለ መጽሐፍ የሚያረጋግጡ፣ ስማቸው ከግብራቸው ያልተዋሐደ፣ ገዳም ገብተው የሚሰልሉ፣ ልክ እንደ ፈሪሳውያን መንፈሳዊ ሹመታቸውን ለሥጋ ፍላጐታቸው መጠቀሚያ የሚያደርጉ፣ ምንኩስናን እንደ ዲግሪ የግል ተልእኮአቸውን ለመፈጸም መሸሸጊያ ዋሻ የሚያደርጉትን ሁሉ ያሳያል።

መጽሐፉን ተወዳጅ የሚያደርገው ደግሞ እነዚህን አካላት በማሳየቱ ሳይሆን እውነተኞቹን ከሐሰተኞቹ እንድንለይ በማስቻሉ ነው። በርግጥም በአንዱ ይሁዳ ሌሎቹ ሐዋርያት እንደማይነቀፉት ምንኩስናን ዋሻ ጥግ አድርገው ተመሳስለው የሚሠሩትን በመለየት ከማሳየቱም አልፎ የቤተ ክርስቲያን ጸጋ የገዳማቱም ቅድስና እነዚህን በመሰሉ ሰዎች የማይረክስ መሆኑንም በገቢር የሚመሰክር ነው። ይህ ደግሞ ሉተራውያን እንደ ማስረጃ /ቄሱን፣ መነኩሴውን.../ እያቀረቡ ለሚያስደነብሩት ወጣት ፍቱን መፍትሔ ይመስለኛል።

እንደ እኔ ያሉ አንባቢዎች ልውጧ ክርስቲያን ናሕድ የሚገጥሟትን ደካማ ካህናትና መነኩሳት ሲያዩ እርሷ ወደ ኋላ እንዳትል በማሰብ ሊፈሩ ይችላሉ። ነገር ግን ክርስቶስን በማመን ለጸኑትና ናሕድን ለመሰሉት «በዓለት ላይ የተሠራውን ቤት» በዓይን ስለሚያሳይ ጐርፉም፣ ዝናቡም ነፋሱም ሲገፉቸው እንጂ ሲያናውጻቸው እንኳን አናያቸውም። መሠረቱ ጽኑው ዐለት ክርስቶስ ነውና። ማቴ.7፥28፣ 1ኛ ቆሮ.10፥5 ናሕድ ትዝ የሚሏትም «ቄስ ቡትሮስን» /ጴጥሮስ/ የመሰሉት የመከራዋ ተሳታፊዎች ካህናት እንጂ ይሁዳዎችንና ዴማሶችን ልትጸልይላቸው ካልሆነ በሌላ አትመለከታቸውም። በዚህም መጽሐፉ ተግባራዊ ወንጌል /Applied Gospel/ መሆኑን እናረጋግጥበታለን።





እኅታችን ናሕድ በጥንት ሕይወቷ እንደ ቅዱስ ጳውሎስ አሳዳጅ እንደ አይሁድ ቀናተኛ፣ በክርስቲያኖቹ ላይ ግፍ ስትፈጽምና ስትጨክንም «እግዚአብሔሯን» የምታገለግል የሚመስላት ሴት ነበረች። ይሁን እንጂ ይህን ሁሉ የሰይጣን አጥር አልፎ እንደ ቅዱስ ጳውሎስ ጠራት። እነ ሔሮድስ፣ ፈርኦንና ኔሮን የመሳሰሉት ጭካኔ የሚፈጽሙት ለራሳቸው ክብርና ገናንነት ስለሆነ እንደ እነርሱ ያሉት ሲመለሱና ሲድኑ የሚያሳይ መጽሐፍ አላነበብኩም። ቅዱስ ጳውሎስን የመሰሉት ግን ቅንዓታቸው «ለእግዚአብሔራቸው» ጥፋታቸውም እውነት መስሎ ለታያቸው ሃይማኖታቸው በመሆኑ ብቻ ሳይሆን ልባቸውም እውነትን ከመፈለግ ስለማይቦዝን እንደየዘመኑ ሁኔታ የወንጌልን ብርሃን እግዚአብሔር ያበራላቸዋል። ናሕድ የዚህ ሁኔታ ዐቢይ አስረጂ ናት።

የናሕድን ሕይወትና ይህን የመሰሉትን ታሪኮች የሚመረምር ሰው ዐቢይ የሆነውን የእግዚአብሔር አሠራር ሳይረዳ የሚቀር አይመስለኝም። ናሕድ ታሳድድ በነበረበት ሀገር መልሳ ተሳዳጅ በሆነች ጊዜ በእርሷ ላይ የተነሡት እጅግ ብዙዎች ነበሩ። አክራሪ እስላሞች ብቻ ሳይሆኑ የግብጽ መንግሥት በተለይም ደኅንነቱ፣ ልጆቿ፣ ዘመዶቿ፣ ፈሪና አድርባይ ክርስቲያኖች፣...... እነዚህ ሁሉ መንገዱንና ሀገሩን ሞልተውት ናሕድ በታክሲ እና በአውቶቡስ ትንቀሳቀሳለች፣ ሥራ ትሠራለች። በየመንገዱ ኬላ ተዘግቶ እየተፈተሸ ሳያይዋት በመካከላቸው ታልፋለች፣ ይህ ነው ትልቁን አሠራር የሚያሳየኝ። ምክንያቱም የአብርሃምን ሕይወት ጭምር የሚያሳይ በመሆኑ።

በአብርሃም ትውፊታዊ ታሪክ እንደምናውቀው ሰይጣን በአራቱም ማዕዘን ራሱን ገምሶ ተቀምጦ ሐሰትን በመናገር ይዋጋው ነበር። እግዚአብሔር ግን አብርሃምን ጉበኝ እንጂ ሰይጣንን አላባረረውም። እርሱ ወጥመዱ አልይዝ ሲል ራሱ ይሸሻልና። የእግዚአብሔር አሠራር ያልኩት ይህንኑ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ወደ ቤተ ክርስቲያን /የአብርሃም ድንኳን/ ለመድረስ ሰይጣንን ማባረር አያስፈልግም። እርሱ እንዳለ፣ አጥሩን አጥሮ እንደ ዘጋ፣ እግዚአብሔር ወደ ድንኳኑ ይመጣል። ዛሬም ይኸው ነው።

የአብርሃም ድንኳን የተባለችውን ቤተ ክርስቲያንን ሰይጣን በአራቱም ማዕዘን ተጉልቶባታል። በርግጥ በዝና የመጡትን እንደዚያ ዘመን እንግዶች አስደንብሯቸው ይሆናል። አብርሃም የተለወጠ እንደመሰላቸው ቤተ ክርስቲያንም የተለወጠች የሚመስላቸውም አይጠፉምና። እውነታው ግን ያው እንደ ነበረ ነው።

አብርሃምም የተራበውና ደጅ የጠናው ለጊዜው ነው። ናሕድም ይህን ታሳየናለችና። መንገድ ላይ በምትሐቱ እንደ ተመለሱት እኛም የዛሬዎቹ ወጣቶች ደንብረን በሌላ ጐዳና እንዳንሔድ ትነግረናለች።

እንደ አብርሃም «ውስጥ ነን፣ ከድንኳኑ አልራቅንም» ለምንለው ደግሞ ምትሐተኛውን ለማባረር እንዳንደክም፣ እርሱ የሚነግሥበት የራሱ ጊዜ እንዳለና እንግዶቹ ሁሉ እንደሚሰባሰቡ ትነግረናለች። በርግጥም ሳይሆን አይቀርም። ስለዚህም ወጣቶች ሁሉ ሰይጣን የመሰላቸውን ለማባረር መታገል አያስፈልጋቸውም። እርሱ እስከ ጊዜው ይቀመጥ። እኛ እንደ አብርሃም

በተጋድሎው ስንጸና እግዚአብሔር ወደ እኛ በሰዓቱ ይመጣል፤ ያን ጊዜም ሰይጣን ራሱ ይሸሻል ስትል ናሕድ ትሰማኛለች፡፡ በርግጥም ሰይጣንን ሊዋጋ የዘመተ አላየንም፡፡ ቢዘምትም ሊያሸንፈው አይችልም፡፡ እንኳን ዕሩቅ በእሲጥንት የተዋጉት መላእክት መጀመሪያ አላሸነፉትም፡፡ ያሸነፉት የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰምተው ትዕምርተ ኃይላቸውን መስቀልን ሲይዙ ነበር፡፡ ይህ መጽሐፍ አንድ በአንድ በሕይወት ተርጉሞ የሚያቀርብልን፤ አጉልቶም የሚያሳየን ይህን የመሰሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ነው፡፡

ከእኛ ሀገር ወቅታዊና ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ሲታይ ደግሞ የመጽሐፉ መታተም ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነው፡፡ ለአክራሪዎቹ እንድንጸልይላቸው ናሕድን ለመመለስ ታላቅ ተጋድሎ እንደፈጸመችው እንደ ሳሚያ በያለንበት ሥራ እንድንሠራ ይጠራናል፡፡ የሳሚያ ታማኝነት የክርስትናዋ ጽናት፣ ትሕትናዋ እና አይበገሬነቷ በርግጥ በየትኛው መንገድ ይጓዙ ዘንድ ለሚያመነቱ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ መስተዋት ነው፡፡

በአጠቃላይ የዚህ መጽሐፍ መተርጎም ለሀገራችን ክርስቲያኖች አንድ ተጨማሪ ዕድል ነው፡፡ ስለዚህም ተርጓሚውን ወንድማችን ዲ/ን ዳንኤል ክብረትን ማመስገን ይገባኛል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ቅዱስ ጳውሎስ «ውጊያችን ከሥጋና ከደም ጋር አይደለም፤....» ሲል የገለጸልንን በገቢር በማሳየት የዘመናችንን የብርዕ ተጋድሎ በመወጣት እንድንከተላቸው ከሚጠሩን አባቶችና ወንድሞች አንዱ በመሆኑ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በታሪኳ ቅዱሳት መጻሕፍትን በየዘመኑ እየተረጐመች ታመጣ ለነበረችው ቤተ ክርስቲያን ከታሪካዊ ኃላፊነቷ ተሳታፊ በመሆን ይህን የመሰለውን የዘመናችን ገድል እንድናገኝ ስላደረገን ምስጋና ቢያንሰው እንጂ አይበዛበትም፡፡

«ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ዘላለምም ያው ነው» እንደተባለው ሳውልን በደማስቆ መንገድ ላይ እንደ ጠራው አሳማ ቢንላደንን የመሰሉትንስ እየጠራ ይሔድ እንደ ሆነ ማን ያውቃል? መጽሐፉን አንብቤ ስጨርስ ኀሊናዬ ያቀረበው ጥያቄ ነበር፡፡ እንደ ሄሮድስ ለክብራቸው እና ለጥቅማቸው ሲሉ ከክርስትና ጋር የሚታገሉ እንደ ሔሮድስ ይጠፋሉ፤ ስለ«እግዚአብሔራቸው»ክብር የሚቀኑ ካሉ ግን እውነተኛውን እግዚአብሔር ማግኘታቸው አይቀርም፡፡ ስለ እነርሱም የሚጸልዩ ከእኛ ወገን ብዙዎች መኖራቸውን አልጠራጠርም፡፡ እንኳን ከእኛ ከኤልያስም የተሰወሩ ነበሩና፡፡ ሐዋርያው እንዳለው «ዓለምን የሚያሸንፈው እምነታችን ነውና» እንደ ሳሚያ ባለ የእምነት ጽናት እንደ ናሕድ ያሉትን ለመመለስ ጊዜው ዛሬ ነው፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ዲ/ን ብርሃኑ አድማስ

የሐመር መጽሔት ዋና አዘጋጅ





# ምዕራፍ አንድ
# ማን ነበርኩ?

ናህድ ማሕሙድ ሙትዋሊ እባላለሁ፡፡ ሴቶችን ብቻ የሚያስተምረው የሄልሜት ኤል ዘይቱን ትምህርት ቤት ዲን ነበርኩ፡፡ በካይሮ የታወቀ እና ትልቁ ትምህርት ቤት ነው፡፡ 4000 ልጃገረዶችን ያስተምራል፡፡ ከተማሪዎቹ ብዛት የተነሣ ት/ቤቱ የሚያስተምረው በጠዋት እና በከሰዓት ፈረቃ ነበር፡፡ የት/ቤቱ ዲን እንደመሆኔ መጠን ሁለቱንም ፈረቃዎች መከታተል ነበረብኝ፡፡ ምንም እንኳን ከሁሉም ዲኖች በዕድሜ ታናሿ እና በቅርቡ ከኮሌጅ የተመረቅኩ ብሆንም ይህንን ወንበር እንዳገኝ ግን ሁለት ነገሮች ረድተውኛል፡፡

እግዚአብሔር ብስለትን፣ በራስ መተማመንን፣ እንዲሁም ኃላፊነቴን በሚገባ የመወጣት ችሎታን አድሎኝ ነበር፡፡ የማንም ርዳታ ሳያስፈልገኝ የሚሰጠኝን ሥራ ሁሉ በአፋጣኝ የማከናወን ልምድ አለኝ፡፡ ሰዎች አንድን ነገር ሲሠሩ መመልከት ብቻ ለእኔ በቂዬ ነበር፡፡ ያንኑ ነገር ወዲያውኑ ልምድ እንዳለው ሰው አድርጌ ማከናወን እችላለሁ፡፡

በዚህ ችሎታዬ የተነሣ ይህንን ቦታ ያገኘሁት ቦታውን ላገኘው ከሚገባኝ ዐሥር ዓመታት ቀድሜ ነበር፡ ከዚህ ችሎታዬ ጋር ተጨምሮ በት/ቤቱ የነበሩትን የሁለቱን ረዳት ዳይሬክተሮች ተግባር የማወቅ ዕድልም ገጥሞኛል፡፡ የተማሪዎችን ስሞች በምሥጢራዊ ኮድ መመዝገብ እና ፈተና ማዘጋጀት፣ እንዲሁም ፈተናዎችን ማተም ካገኘኋቸው ዋና ዋና ልምዶች መካከል የሚጠቀሱት ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለቱ ተግባራት ደግሞ በት/ቤታችን ውስጥ ዋነኞቹ ሥራዎች ናቸው፡፡ ምክንያቱም ሁለቱም ፍጹም የሆነ ምሥጢር ጠባቂነትን የሚጠይቁ ናቸውና፡፡

አንደኛው ረዳት ዳይሬክተር በ60 ዓመቱ ጡረታ ወጣ፤ ሌላው ደግሞ ወደ ሌላ የዓረብ ሀገር ለሥራ ሄደ፡፡ ይህንን አጋጣሚ በመጠቀምም እነዚህን ሁለቱን ኃላፊነቶች ጠቀለልኳቸው፡፡ ይህም የት/ቤቱን ቁልፍ ቁልፍ አስተዳደራዊ ኃላፊነቶች እንድቆጣጠር ዕድል ከፈተልኝ፡፡

እነዚህን ኃላፊነቶች ከጠቀለልኩ በኋላ ልክ የት/ቤቱ ንግሥት የሆንኩ ያህል ይሰማኝ ነበር፡፡ በእነዚህ ነገሮች ሙሉ ሥልጣን እና

ፍጹም የሆነ ኃላፊነት ነበረኝ። ሌላው ቀርቶ የእኔ የበላይ የሆነችው
የት/ቤቱ ዳይሬክተር እንኳን በጣም ትቀርበኝ፣ የምትሠራውንም ነገር
ሁሉ ታማክረኝ ነበር። የምፈራ፣ ኃይለኛ፣ አድራጊ ፈጣሪ ሆንኩ።

ለምኞቴ ወሰን አልነበረውም። ለዝቅተኛ ተማሪዎች የሚሰጠውን
የትምህርት እገዛ እኔ ራሴ እንድከታተለው ኃላፊነቱ እንዲሰጠኝ
አስተዳደሩን ጠይቄ ተፈቀደልኝ። በዚህ የተነሣም በየወሩ ከእነዚህ
ክፍሎች ለሚሰበሰበው ከ12ሺ - 15ሺ ለሚጠጋው ገንዘብ ኃላፊ
ሆንኩ። ለዚህ ኃላፊነቴ እንዲሁም ፈተና ለማዘጋጀት እና ለማባዛት
ተግባሬ የሚከፈለኝ ገንዘብ ወርኃዊ ገቢዬን በሦስት እጥፍ አሳደገው።

ወደዚህ የሥልጣን እርከን ያሸጋገረኝ ሌላው ነገር ደግሞ የቤተ
ሰቦቼ ታዋቂነት እና በመንግሥታዊ ቦታዎች ያላቸው ሥልጣን
ነበር። ወንድሜ በማዕከላዊው የአስተዳደር እና የአመራር ሥርዓት
ቢሮ ውስጥ ሥራ አስኪያጅ ነበር። አንደኛው ዋርሳዬ ደግሞ የማዘ
ጋጃ ቤቱ ረዳት ጸሐፊ እና የት/ቤቱ የወላጆች እና መምህራን ማኅ
በር ፕሬዚዳንት ነው። የእርሱ ሁለቱ ሴቶች ልጆቹም የት/ቤቱ
ተማሪዎች ነበሩ።

ሌላው ዋርሳዬ ደግሞ የቤተ መንግሥቱ ፓይለት ነው። እንቴ
የሄልዮፖሊስ አካባቢ የት/ቤቶች አስተዳደር የሕዝብ ግንኙነት ሥራ
አስኪያጅ ናት። ባልዋም በማዕከላዊው የመረጃ አገልግሎት ሹም
ነበር። እነዚህ ሁሉ ከእኔ ሰብእና እና በት/ቤቱ ከተፈጠረው ክፍተት
ጋር ተደማምረው ከሥልጣን ወደ ሥልጣን አሸጋገሩኝ።

ይህ ሁሉ በሀብት እና በሥልጣን ይጥቀመኝ እንጂ ውስጤን ግን
ትዕቢተኛ፣ ዕብሪተኛ እና ግብዝ አድርጎኛል።

በሌላ በኩል ልቡናዬን ለሚያይ ደግሞ የተለየሁ ፍጥረት ነበርኩ።
አምላኬን እወድዳለሁ የምል ቆዳ ስሱ ሰው ነኝ። አዎን ጌታዬ ሆይ
ምንም እንኳን ከአንተ ርቄ ብኖርም በፍጹም ልቤ እወድድህ እና
እፈራህ ነበርኮ። እግዚአብሔርን ስፈልገው ኖሬያለሁ፤ እነዚያ የሕይ
ወቴ የተበላሹ ገጽታዎች ግን እርሱን እንዳላገኘው የመከለያ ግንብ
ሆነውኝ ኖረዋል። ይህንን ግንብ እንዴት አድርጌ እንደምሻገረው አላ
ውቅም ነበር። አብዝቼ እጸልያለሁ፤ ቁርዐንንም አዘውትሬ አነባለሁ፤
ይሁን እንጂ በውስጤ አንዳች የጎደለ ነገር መኖሩ ይሰማኝ ነበር።
ክርስቲያኖች እኔ የምወደውን አምላክ አይወዱትም ብዩ ስለማስብ
አብዝቼ እጠላቸው ነበር። እግዚአብሔርን እኔ በማመልክበት መን
ገድ ለምን አያመልኩትም? እነርሱ ከእግዚአብሔር የኮበለሉ ናቸው
እያልኩ እጅግ እጠላቸው ነበር።





ክርስቲያኖችን ከመጥላቴ የተነሣ እነርሱን ለማዋረድ፣ ለመጉ
ዳት እና በእነርሱ ላይ አንዳች ችግር ለመፍጠር ዘወትር እጥር
ነበር። ይህንን የማደርገው ግን በውስጤ ለሰው ክፉት ስላለኝ ሳይሆን
የምወደውን እና የማመልከውን አምላክ ለምን አያመልኩም፤ ለምንስ
አይወዱም? ብየ ነበር። በርግጥ ሁልጊዜ የሚገርመኝና የሚያሳስበኝ
አንድ ነገር አለ። እኔ ላገኘው የምጓጓለትን ውሳጣዊ ሰላም ክርስ
ቲያኖች ገንዘብ አድርገውታል። እንዴት?

ከክርስቲያኖቹ የተሻለ ሀብት አለኝ። እጅግ ውድ የሆኑትን
ልብሶችም እለብሳለሁ። የሚጎድልብኝ ምንም ነገር አልነበረም። ይሁን
እንጂ እኔ ያላገኘሁት አንድ ጠንካራ ነገር እነርሱ ጋ አለ። በማን
ኛውም ክርስቲያን ዓይን ላይ በራስ የመተማመን፣ መረጋጋት እና
ሰላማዊነት ይነበባል። ያንን ውሳጣዊ ሰላማቸውን ለማሳጣት እነርሱን
ማበሳጨት ለምን እንደሚያስደስተኝ ዛሬ ሳስበው ይገርመኛል።

አንድ ቀን አንድ ካህን ወደ ቢሮዬ መጣ። ቀሚሱን ለብሶ
ከቢሮዬ በር ላይ ሳየው አንዳች የሚያንቀጠቅጥ ነገር ጠራርጎ የወሰ
ደኝ መሰለኝ። ወዲያው እንደምንም ተረጋግቼ ራሴን እንዲህ
አልኩት «ይህ ካህን ዛሬ በእኔ እጅ ላይ ወድቋል፤» እናም ከነመኖሩ
ረሳሁትና ሥራዬን መሥራት ቀጠልኩ። ወደ ውስጥ ዘልቆ ገባና ፊት
ለፊቴ ቆመ። እኔም ዶክመንቶቹን እያገላበጥኩ በሥራ የተጠመድኩ
መሰልኩ። ለጥቂት ደቂቃዎች ያህል ከጠበቀኝ በኋላ ቀስ ብሎ
«ወ/ሮ ናህድ ሙትዋሊ ማለት እርስዎ ነዎት?» ሲል ጠየቀኝ።
እኔም ቀና ብየ እንደዋዛ አየሁት።

ዓይኖቹን በዓይኖቼ ሳያቸው ፍርሃት ተሰማኝ። ረጋ ያለ፤ ትጉት
እና ቁጥብ ሰው ነው። እኔም በንቀት «አዎን» ብዬ መለስኩለት።
ሴት ልጁን በላዕላይ ግብጽ ካለው ት/ቤት ወደ ሄልሜት ኤል ዘይ
ቱን ለማዛወር የተጻፈ ማመልከቻ ሰጠኝ። ረጋ ባለ ሁኔታ ጥያቄ
ውን እንድቀበለው ለመነኝ። በመሐል አቋረጥኩትና ድምፄን ከፍ
አድርጌ «ከላዕላይ ግብፅ ወደ ሄልሜት ኤል ዘይቱን በአንድ ጊዜ፣
ለምን?» ስል ጮህኩበት። እርሱ ግን በትኅትና «እባክዎን ከዐቅሜ
በላይ በሆነ ችግር ምክንያት ነው» ሲል መለሰልኝ። ቀጠል አድርጎም
«ት/ቤቱ ባለበት አካባቢ ለመኖሬ ማስረጃው ይሄው፣ እንቶቿ በአካ
ባቢው ወደሚገኘው የሕዝብ ት/ቤት እና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ
ት/ቤት የተዛወሩበት ማስረጃም እነሆ» ሲል አቀረበ።

ጥያቄውን ላለመቀበል የሚያስችለኝ አንዳች ምክንያት ባገኝ
ብዬ ዶክመንቶቹን መረመርኳቸው። ነገር ግን ምንም ላገኝ አልቻ
ልኩም። ከዚያም ቀና ብዬ አየሁት። ፊት ለፊቴ ቆሞ በሚገርም

ሁኔታ ያስተውለኛል:: ሰላማዊ፣ ጸጥተኛ፣ በራሱ የሚተማመን ዓይነት የተረጋጋ ሰው ነው:: «አስቀድመን ለት/ቤታችን ስጦታ እንፈልጋለን» ብዬ ላበሳጨው ፈለግኩ:: እርሱም «ከእኔ ነው» ሲል መለሰልኝ:: «አንድ መቶ ፓውንድ[1] የሚያወጣ ቁሳቁስ ገዝተህ ለት/ቤቱ ማምጣት አለብህ» አልኩት:: «እስማማለሁ» ሲል ወዲያው መለሰልኝ:: ከዚያም «እባክዎ ዝውውሩን ግን አሁኑኑ ያጽድቁልኝ፤ ምክንያቱም ላዕላይ ግብጽ ወዳለው ት/ቤት ከጥቂት ሰዓታት በኋላ በሚሄደው ጓደኛዬ በኩል መላክ አለብኝና:: ከዚያ በኋላ የፈለጉትን ነገር እገዛለሁ» ሲል ተማጸነኝ::

በርግጥ ልጁ ለዝውውሩ ብቁ ናት:: ግን የማቀርብለትን ነገር ላይቀበለው ይችላል ብዬ ላበሳጨው ነበር የፈለግኩት:: እርሱ ግን ተስማማ:: እናም ይህ እንዳልተሳካልኝ ሳዉቅ ጮክ ብዬ «መጀመርያ የተጠየቅከውን መፈጸም አለብህ» አልኩት:: በተረጋጋ ሁኔታ እያየኝ «ይመኑኝ፤» ሲል ተማጸነ:: ያንን ትሑት የሆነ ልመናውን መቃወም አልቻልኩም:: እናም በዝውውሩ ወረቀት ላይ ፊርሜ ማኅተም አሳረፍኩበት:: ከዚያ በፊት እንዲህ አድርጌ አላውቅም:: የጠየቀውን እንዳደርግለት የሚገፋፋ አንዳች ኃይል ሳይኖረው አይቀርም:: በውስጤ «ርዳታውን አንፈልገውም፤ በዚህ መልኩ ስላስተናገድኩህም ይቅር በለኝ» ልለውም አስቤ ነበር:: ነገር ግን አንዳች ቃል ከአፌ አልወጣም:: ከሄደ ከአንድ ሰዓት በኋላ አንድ መቶ ፓውንድ የሠፈረበት የገንዘብ ማዘዣ ይዞልኝ ሲመጣ ተደነቅኩ:: የመማርያ ጠረጴዛውን ለማምጣት በፈለግኩት ጊዜ አንድ ሰው ብቻ መላክ እንደሚበቃኝ ነገረኝ::

በሕይወቴ ለመጀመርያ ጊዜ የጥፋተኛነት ስሜት

በውስጤ ተሰማኝ::

ካህኑ አመስግኖኝ እጄን ጨብጦ ተመለሰ:: እርሱ በውስጤ የፈጠረውን እንግዳ ስሜት ያወቀ አይመስለኝም:: ኀዘን ተሰማኝ:: ደግሞም አንድ ጥያቄ ይረብሸኝ ነበር:: «በዚህ ሰውዬ ውስጥ ምን አለ? እንዴትስ እንዲህ እያመናጨቅኩት በትኅትና ሊመልስልኝ ቻለ? እርሱ እኔ ያጣሁትን ነገር አግኝቶታል ማለት ነው? እኔኮ ዘወትር የምፈልገው ይህንን ነበር፡- የማይናወጥ ውሳጣዊ ሰላም::

አጋጣሚውን ለመርሳት ደጋግሜ ሞከርኩ:: ነገር ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ የካህኑ አስተያየት ዓይኔ ላይ መጥቶ ድቅን ይላል:: በጥልቀት የሚያዩት ሰላማውያን ዓይኖቹ በዓይነ ኅሊናዬ ይመጡብኛል:: ብዙ

1.የግብጽ ገንዘብ ፓውንድ ነው የሚባለው::





ጊዜ ከታገልኩ በኋላ ያንን ስሜት ረስቼ ወደ ቀደመው ጠባዬ ተመለስኩ::

በ1986/87[2] የትምህርት ዘመን የትምህርት አስተዳደር ቢሮው ክርስቲያን ዳይሬክተር ለት/ቤታችን መደበ:: ዜናውን ስሰማ እጅግ ደነገጥኩ:: እንዴት ተደርጎ ክርስቲያን አለቃ ሊኖረኝ ይችላል? በጭራሽ ልቀበለው የምችለው ነገር አይደለም:: እርሷን አንዳች ነገር አድርጌ ከት/ቤቱ ለማባረር የምችልበትን ተንኮል ማውጠንጠን ጀመርኩ:: በትምህርት ቤቱ ውስጥ ተመችቷት ረዥም ጊዜ እንዳትቆይ የሚያበሳጯትን ነገሮች ማድረግ አለብኝ:: ብቸኝነት እንዲሰማት ማድረግ አለብኝ:: እኔ በቃሌ የሸመደድኳቸውን የት/ቤቱን ደንቦች እና መመሪያዎች አታውቃቸውም:: ስለዚህም አንድ ሃሳብ ስታመጣ እነርሱን እየጠቀስኩ ማጣጣል እችላለሁ:: ልትሠራቸው የምትችላቸውን ጥቃቅን ስሕተቶች ሁሉ እየነቀስኩ አወጣቸዋለሁ:: ለእርሷ አንዳች ክብር የሌለኝ መሆኑን በየአጋጣሚው ማሳየት አለብኝ::

አዲሷ ዳይሬክተር እንደመጣች የወጠንኳቸውን ተንኮሎች ሁሉ በመፈጸም ማበሳጨት እና ሰላም መንሳት ቀጠልኩ:: በመጨረሻም አንድ ወርቃማ አጋጣሚ ተፈጠረልኝ:: በሳይንስ ዲፓርትመንት የዐሥረኛ ክፍል አብዛኞቹ ተማሪዎች ክርስቲያኖች ነበሩ:: በተሰጣቸው ፕሮጀክት መሠረት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ያሉበት የግድግዳ መጽሔት አዘጋጁ:: ሁኔታውን የጠቆመኝ አንድ ሙስሊም መምህር ነው:: እንደ ሰማሁ በቁጣ እና በፍጥነት ወደ ክፍሉ በማምራት መጽሔቱን ቀዳድጄ ጣልኩት::

ስጠብቀው የቆየሁትን አጋጣሚ አሁን አገኘሁት:: ለምሥራቅ ካይሮ ወረዳ የት/ቤቶች ተቆጣጣሪ መሥሪያ ቤት «ከባድ ምሥጢር» የሚል ማኅተም ያረፈበት ደብዳቤ ጻፍኩ:: በዚያ ደብዳቤ ላይ ተማሪዎቹ ይህንን ጥፋት እንዲሠሩ ያበረታታቻቸው ዳይሬክተሯ መሆንዋን ገለጥኩ:: ከዚህም በተጨማሪ የዳይሬክተሯ ዓላማ በትምህርት ቤቱ የሃይማኖት ውዝግብ እንዲፈጠር ማድረግ መሆኑን አስረዳሁ:: ሁኔታው በአፋጣኝ ተጣርቶ ርምጃ መወሰድ እንዳለበትም አሳሰብኩ:: ለአስቸኳይነቱም በተላላኪ በኩል ወዲያውኑ ላክሁት::

በነጋታው የሥራዬን ውጤት ለማየት ስለ ጓጓሁ በጠዋት ነበር ወደ ት/ቤት ያመራሁት:: የት/ቤቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን አንዲት ኃይለኛ ሙስሊም ሁኔታውን አጣርታ ሪፖርት እንድታደርግ ላከ:: አጣሪ ሆና የመጣችው ሰው ሂጃብ ከፊቷ አውልቃ የማታውቅ እና ለክርስቲያኖች ቅንጣት ታህል ትዕግሥት የሌላት መሆንዋን ዐውቃ

2. የዘመን አቆጣጠሩ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ነው

ለሁ:: አጣሪዋ በጉዳዩ እጃቸው አለበት የተባሉትን አራት ተማሪዎች በመመርመር ሥራዋን ጀመረች:: ሁሉም በየተራ ከምርመራው ክፍል ሲወጡ ከደረሰባቸው ማስፈራራት የተነሣ እያለቀሱ ነበር:: እያንዳንዳቸው አንድ አንድ ሰዓት የፈጀ ምርመራ ተካሂዶባቸዋል::

የዚያች ክርስቲያን መምህርት ተራ ደረሰ:: የርሷ ምርመራ ከተማሪዎች የበለጠ ጊዜ ፈጀ:: ከምርመራው ክፍል ስትወጣ ከማል ቀሷ የተነሣ ዓይኖቿ በርበሬ መስለው ቀልተው ነበር:: በእርጋታው እና በጭምትነቱ ከሚታወቀው ክርስቲያን የሂሳብ መምህር ጋር ወደ ቢሮዬ መጥታ «ተማሪዎቹን እንዲህ ዓይነት ነገር እንዲያደርጉ የምቀሰቅሰው ያንን ያህል አእምሮዬን ያጣሁ መሰለሽ» እያለች አለቀሰች:: እኔ ግን አልመለስኩላትም::

በመጨረሻ የዳይሬክተርዋ ተራ ደረሰ:: በምርመራው ተበሳጭታ ስትጮህ እሰማታለሁ:: «አይደለም፣ አይደረግም፣ ይህ ሊሆን አይችልም፣ ይህንን ክስ አልቀበለውም፣ ይህንን ለመሰለ ውንጀላ መልስ መስጠት አልፈልግም፤ ምርመራውንም ፈጽሞ አልቀበለውም፤ የትምህርት ቢሮ ኃላፊውን ማነጋገር እፈልጋለሁ» እያለች ስትጮህ እሰማታለሁ:: ከዚያም ክፍሉን ጥላ ወጣች::

ከዚያን ቀን በኋላ በት/ቤቱ በሚገኙ ክርስቲያኖች ላይ የወደቀውን ፍርሃት እና ድንጋጤ ልገልጠው አልችልም:: በሠራሁት ሥራ ኮራሁ:: በዚህ ትምህርት ቤት ያሉትን ክርስቲያኖች ሁሉ እያደንኩ ላጠቃቸው ወሰንኩ:: ከዚህ በኋላ ማንም ከፊቴ ቆሞ ሊቋቋመኝ አይቻለውም:: መጀመርያ በወሰድኩት ርምጃ ክርስቲያን ተማሪዎች መስቀል ያለው ምንም ነገር እንዳይለብሱ መመርያ አወጣሁ:: በዚህም የክርስቲያኖች ዋና ጠላት መሆኔን አሳየሁ:: ሕጋዊ ቢሆንም ባይሆንም ማንኛውንም ዓይነት ጥያቄያቸውን አላስተናገድም ነበር::

ከዚያን ቀን ጀምሮ በት/ቤቱ ማኅበረሰብ ዘንድ የተፈራሁ ሰው ሆንኩ:: ለእኔ ያላቸው ፍርሃት ከእኔ ጋር ማንኛውንም ዓይነት ግንኙነታቸውን ርግፍ አድርጎ እስከመተው አደረሳቸው:: ይህ ብቻውን ግን የሚያረካኝ አልሆነም:: እናም ለዚያች ክርስቲያን ዳይሬክተር የመሰና በቻውን ዱላ ማቅመስ ፈለግኩ:: ይህንን ለማድረግ ደግሞ አመቺ የሆነ አጋጣሚ እስኪፈጠርልኝ ድረስ መጠበቅ ነበረብኝ:: ለዚህ ሲባል ብቻዋን አንድ ቀን ማግኘት አለብኝ:: ቢሮ የምትደርስበትን ሰዓት ሳጠና እንደ ወፍ በማለዳ የምትነሣ መሆንዋን ደረስኩበት:: ስለሆነም ማንም ሰው ከመምጣቱ በፊት ብቻዋን ላገኛት ወጠንኩ::

በማግስቱ በማለዳ ወደ ት/ቤት መጣሁ:: እርሷም ከደቂቃዎች በኋላ ደረሰች:: ልክ ቢሮዋ ስትገባ ፊቴን መከራ አስመስየ ተከተልኳትና ገባሁ:: ስታየኝ ለነገር የፈለግኳት መሆኑ ገባት መሰል ነቃ





አለች:: ይህ ደግሞ ለእኔ የልብ ልብ ሰጠኝ:: ከዚያም ቁርጥ አድርጌ «እዚህ ምን ትሠሪያለሺ፣ እዚህ ት/ቤት ውስጥ ከአንቺ ጋር ፈጽሞ መሥራት አልችልም፤ አንቺን በዚህ ቦታ ማየት ከቶውንም አልሻም፤ ውጭ ከዚህ!» አልኩና ጮኽኩባት:: የማደርገውን እውነት ነው ብላ መቀበል የቻለች አልመሰለኝም:: ደነገጠችና «ምን እያልሽ ነው? አእምሮሽን ሳትሽ እንዴ?» አለችኝ:: እኔም ቁጣዬን ጨመ ርኩና «እንዳንቺ ጆላጆል አይደለሁም፤ አብረን አንድ ቦታ ልንሠራ ፈጽሞ ፈጽሞ አንችልም፤ ውጭ!» ብየ አንባረቅኩባት::

ከእኔ ለመሸሽ ፈለገች፤ እኔም ሁኔታውን ስረዳ ለመማታት የቃጣሁ መስዬ እጄን ሰነዘርኩና «በአስቸኳይ ከዚህ ቦታ ለቅቀሽ ውጭ፤ እዚህ ከቆየሺ ግን እገድልሻለሁ» አልኳት:: ወዲያው ከቢሮዋ በርራ ወጣች:: የሆነን ሰው ለርዳታ ስትጣራ በፍጥነት ከቢሮዋ ወጥቼ አጠገቡ ወዳለው ቢሮዬ ገባሁ:: ከዚያም ምንም እንዳልተፈጠረ ሁሉ የተለመደውን ሥራዬን ማከናወን ቀጠልኩ:: አጠገቧ ለነበሩ ሰዎች «ናህድ ልትገድለኝ ነው» እያለች ስትጮኽ እሰማታለሁ:: የተወሰኑት መምህራን ሰብሰብ ብለው ሲመጡ የተለመደ ሥራዬን ስሠራ አገኙኝ:: እኔም እርሷን እርሷን እያየሁ «ምን እያልሺ ነው? የምታወሪውን የሚያምንሺ አንዳች አታገኝም» አልኳት:: ከዚያም የትምህርት ቢሮ ኃላፊውን ለማነጋገር እየተጣደፈች ወጣች:: በዚያው ቀን ሁኔታውን ለማጣራት ከትምህርት ቢሮው አንድ ሙስሊም መርማሪ ተላከ::

መርማሪው ስለ እኔ ተናገረች ያለውን ነገረኝ:: ሽምጥጥ አድርጌ ካድኩ:: ደግነቱ እርሱም ምንም ሳይከራከር አመነኝ:: እኔም ሞኝ አይደለሁም ፤በዚያች ሰዓት ከእኔ ጋር በቢሮዬ እንደነበሩ አድርገው የሚመሰክሩ ብዙ የሐሰት ምስክሮች አዘጋጅቼ ነበር:: ከዚህም በላይ እርሷ እንደምትጠላኝ፣ ይህንንም የሐሰት ታሪክ የፈጠረችው እኔን አባርራ በክርስቲያን ለመተካት ስላሰበች መሆኑን ምስክሮቹ አስረዱልኝ:: በዚህም ምክንያት ጉዳዩ የሃይማኖት ጠብ መስሎ ቀረበ:: ይህ መሆኑ ደግሞ እኔን ይጠቅመኛል:: ዳይሬክተሯ ብዙም አልቆየችም ፤ዝውውር ጠየቀችና ሄደች::

ከዚያ በኋላ በትምህርት ቤቱ ለሚገኙ ክርስቲያኖች የመጨረሻ ጨካኝ ሆንኩባቸው:: እጅግ ይፈሩኝ ጀመር:: በዚያ ግቢ ውስጥ ተቀናቃኝ የሌለኝ ንግሥት ሆንኩ:: ሁሉም ነገሮች በእኔ ቁጥጥር ሥር ሆኑ:: ትእዛዜን የሚቃወም ማንም አልነበረም:: የሚከራከረኝ እንኳን አልተገኘም:: አንድ ተማሪ መስቀል አድርጎ ካገኘሁት ከአንገቱ በጥሼ መሬት ለመወርወር ቅንጣት ታህል ትዕግሥት አልነበረኝም::

ናህድ ማሕሙድ ሙትዋሊ ማለት ይህ ነበርኩ::

# ምዕራፍ ሁለት

# እንዴት ክርስቲያን ሆንኩ?

እግዚአብሔር እንዲህ አስቸጋሪ እና ትዕቢተኛ ያደረገኝ ለካ የራሱ የወደፊት ዓላማ ሊኖረው ኖሯል:: እርሱ ሁሉንም ነገር ለእርሱ ስል እንድተወው ሊጠይቀኝ በዝግጅት ላይ ነበር:: ደግሞም ይህንን ሁሉ ጠንካራ ሰብእና፣ ዕውቀት፣ እንደበተ ርቱዕነት፣ በተጠየቃዊ መንገድ ማሳመን እና ኃይል ያስታጠቀኝ ለሌላ ተልዕኮ ሲያዘጋጀኝ ኖሯል:: አይበገሬ፣ ገናና እና ያለ ተቀናቃኝ የምገዛ የትምህርት ቤቱ ንግሥት በመሆን ላይ ነበርኩ::

ይህ ሁሉ ቢሆንም ግን በውስጤ ኀዘን ነበር:: ውስጤን ሳዳምጠው ባዶነት ይሰማኛል:: አምላኬን በፍጹም ልቤ የምወደው ቢመስለኝም ከእርሱ ግን እጅግ ርቄ ነበር:: በእኔ እና በእርሱ መካከል የመከለያ ግንብ ነበር:: አንዳንድ ጊዜ ይህ ግንብ ኃጢአቴ ይሆንን? እላለሁ:: አንድ ቀን እንዲያውም ለራሴ «አሁን ብሞት ለአምላኬ የማቀርበው ምን በጎ ሥራ አለኝ?» ብዬ ጠየቅኩ:: ኃጢአቴን አሰብኩትና ለዘላለም ሕይወት የሚሆን አንዳች ነገር ማድረግ አለብኝ ብዬ ወሰንኩ:: ሀብት አለኝ፤ ስለሆነም «ወደ ሳዑዲ ዐረቢያ ተጉዤ መካን እና መዲናን መሳለም አለብኝ» ብዬ ወሰንኩ::

ዝግጅቴ ብዙ ጊዜ አልፈጀብኝም:: ለጉዞ የሚያስፈልገውን ቀሚስ ገዛሁ፤ ከዚያም በአውሮፕላን ጅዳ ገባሁ:: ጅዳ ስገባ እኩለ ሌሊት ካለፈ አንድ ሰዓት ያህል ሆኗል:: ከጅዳ በመኪና ወደ መካ አመራሁ:: ምንም እንኳን መንገዱ አስቸጋሪ ቢሆንም ሃይማኖታዊውን ጉዞ እስኪነጋ ጠብቄ ለመጀመር ትዕግሥት አልነበረኝም:: በቀጥታ ወደ ከዓባ አመራሁ[3]:: እዚያ ስቆም ወደ አምላኬ እጅግ የቀረብኩ ስለመሰለኝ በውስጤ የጋለ ስሜት ተፈጠረ:: እዚህ የቆምኩትኮ አምላኬን ምን ያህል እንደምወደው ለመግለጥ ነው:: ነገር ግን አሁንም የራቅኩ ያህል ነው የሚሰማኝ:: «እባክህ ወደ አንተ አቅርበኝ፤ እባክህ ከእኔ ጋር መሆንህን ልረዳው፣ እባክህ ልቤን ንካው፤ አምላኬ ሆይ

3. ከዓባ በእስልምና ትምህርት መሠረት መካ ውስጥ የሚገኝ የተቀደሰ ድንጋይ ነው፣ ሙስሊሞች ሐጅ የሚፈጽሙት እርሱን በመዞር ነው::





ስለ አንተ ያለኝን ስሜት ሰይጣን እያደበዘዘው እንዳይሆን እባክህ እርዳኝ» እያልኩ የከዓባን ድንጋይ እዞረው ነበር:: ምናልባት አንዳች ነገር ውስጤን ቢያነቃንቀው የሚል ተስፋም ነበረኝ::

ከዐሥር ቀን ቆይታ በኋላ ወደ ግብፅ ስመለስ ከበፊቱ የባሰ ጭንቀት ወርሶኝ ነበር:: ዝም ብየ ራሴን ስፈትሸው አንዳች ያጣሁት ነገር እንዳለ ገባኝ:: ምናልባት ራሴን አጥቼው እንዳይሆን ብዬም ፈራሁ:: እናም ፍለጋዬን ማቆም እንደሌለብኝ ወሰንኩ::

«አምላክ እኛን ፈጥሮ በክፉ መንገድ እንድንጠፋ ትቶናል ብሎ ማሰብ ይቻላል?» እያልኩ ዘወትር ራሴን እጠይቅ ነበር:: እንደገና ደግሞ «አይሆንም፤ አንድ ያልገባኝ ነገር መኖር አለበት» እላለሁ:: «እግዚአብሔር ጨካኝ ነው ብሎ ማሰብ የሚቻል አይመስለኝም፤ ይህን ማሰብ ምክንያታዊ አይሆንም፤ እግዚአብሔር ይህንን ዓለም የፈጠረው ለደስታ እንጂ ለመከራ አይሆንም፤ በዚያ ያለውን ሁሉ እንድንገዛ ኃይል ሰጥቶናል፤ ይህ ማለት ደግሞ እኛን ይወድደናል ማለት ነው::» እላለሁ ደግሞ መልሼ:: እንዲህ እንደተምታታብኝ ጥቂት ጊዜያት አለፉ::

ነገሮችን አጥርቼ ለማወቅ እጅግ ብተጋም ልፋቴ ሁሉ ከንቱ ነው የሆነው:: በመጨረሻም እስቲ መጀመርያ አምላኬን ለማስደሰት ልሞክር ከዚያም እርሱ ራሱ ወደ ትክክለኛው መንገድ ይመራኛል ብዬ አሰብኩ::

እየቆየ በውስጤ የሚሰማኝ ባዶነት ኅሊናየን ያሰቃየው ጀመር:: ከአምላኬ መራቄ ውስጤን ይረብሸዋል:: እናም በመጨረሻ «አምላኬ የሰጠኝን ይዤ በመደሰት ይህን ነገር መርሳት አለብኝ» ብዬ ደጋግሜ ወሰንኩ:: ይሁን እንጂ የሚያስፈልገኝ ነገር ሁሉ እንዳለኝ እየተረዳሁ እንኳን ይህንን የውስጤን ጥያቄ ማዳፈን አልቻልኩም::

ከኮሌጅ የተመረቅኩት በ1963 ነው:: የሚያስቀና ደረጃ፣ በትምህርት ቢሮው ዘንድ የገነነ ዝና፣ ከፍተኛ ደመወዝ (በመንግሥት የደመወዝ ስኬል ቁጥር አንድ የተባለ)፣ ረዥም ጊዜ የዘለቀ ገናና ስም፣ ከአንዳንድ ኃላፊነቶቼ የማገኘው ተጨማሪ ገቢ አለኝ:: ከዚህም በተጨማሪ ጎበዝ ተማሪዎች የሆኑ አንድ ወንድ እና ሁለት ሴት ልጆች አሉኝ:: ከተከራየሁት ጀምሮ ተቀምጨበት የማላውቅ አንድ አፓርትመንት እና የራሴ መኪናም አለኝ [4]::

4. ግብፅ ውስጥ አፓርትመንት ማግኘት ጀብዱ እንደ መፈጸም ይቆጠራል:: ብዙ እጮኛሞች በቤት ማጣት የተነሣ መጋባት ከሚፈልጉበት ጊዜ በጣም ዘግይተው ነው የሚጋቡት፤ በዚያን ጊዜ የግል መኪና የሀብት እና ታላቅነት ማሳያ ነበር።

በዚህ መሐል አንድ ቀን ሴቷ ልጄ አንድ እንግዳ ጥያቄ ጠየቀ
ችኝ:: «እማዬ ክርስቲያን ባል ማግባት እችላለሁ?» ስትል:: በድን
ጋጤ ጮኽኩና አፈጠጥኩባት:: «አይደረግም፤ በጭራሽ አይደረግም፤
ፈጽሞ ሊሆን የሚችል ነገር አይደለም፤ ይህንን ነገር እንኳን ልታደ
ርገው ደግመሽ እንኳን ብታስቢው እኔ ራሴ እገድልሻለሁ» አልኳት::
እርሷ ግን «ኢንጂነር እኮ ነው፤ ደግሞም ከታወቀ ቤተሰብ የተወለደ
ነው፤ ቤተሰቦቹ ወደ አሜሪካ ሊጓዙ ስለሆነ እኔም አብሬው መሄድ
እፈልጋለሁ፤ እዚያ እንጋባለን፤ ደግሞም ከአንቺ በቀር ይህንን የሚያ
ውቅ ማንም የለም» ስትል መለሰችልኝ:: ፊቷ ላይ አፈጠጥኩና እንደ
ብራቅ እየጮኽኩባት «አምሞሻል፤ ሙስሊም እኮ ነሽ! እንዴት አድ
ርገሽ ነው ክርስቲያን የምታገቢው፤ ኃጢአት እኮ ነው» ብዬ ጮኽ
ኩባት:: ከዚያም እኔን ሳታማክረኝ ጋብቻን በተመለከተ ምንም
ማድረግ እንደሌለባት ቃል አስገባኋት::

ፈጣሪ ለእኔ እና ለልጄ አንድ ጸጋ ሰጥቶናል:: በአስቸጋሪ ነገር
ውስጥ ሆኜ አምላኬን ስለምነው መልሱን በሕልም ይነግረኝ ነበር::
ልጄም ልክ እንደ እኔው ናት:: እናም ይህንን ወጣት በተመለከተ
ፈጣሪንን በጸሎት እንድትጠይቅ እና በሕልሟ ያየችውንም ሳትደ
ብቅ እንድትነግረኝ መከርኳት:: በነጋታው ጠዋት ልጄ በሕልሟ ያየ
ችውን ነገረችኝ::

«በምንጭ አጠገብ በተሠራ ሰፊ ጎዳና ላይ እየተንዝኩ ነበር፤
በመንገዱ መጨረሻ መስቀለኛ መንገድ አገኘሁ:: በየትኛው መንገድ
መቀጠል እንዳለብኝ ግራ ገብቶኝ ስቆም ሦስት ሂጃብ የተሸፈኑ ልጃገ
ረዶች መጡና ከእኛ ጋር እንሂድ አሉኝ:: ነገር ግን ከእነርሱ ጋር
ለመሄድ ልቤ አልፈቀደም:: ከዚያም መስቀሎች የሞሉበት አረንጓዴ
ቀሚስ የለበሰች ልጃገረድ አየሁ:: እርሷም እጄን ያዘችኝ:: እኔም
በልቤ ደስ ብሎኝ ተከትያት ሄድኩ» አለችኝ::

የዚህን ሕልም ትርጉም ልረዳው አልቻልኩም ነበር:: እርሷንም
«ይህ ወጣት ልብሽን ስላማለለው ባልተጨበጠ ነገር እየቃዠሽ ይመስ
ለኛል:: ልታገቢው በጣም ሳትፈልጊ አልቀረሽም፤ ይህንን ሃሳብሽን
ቸል የምለው እንዳይመስልሺ:: በይ ይህንን ነገር ደግመሺ እንዳታ
ነሺብኝ» ስል ተቆጣኋት:: እርሷም ያልኳትን እንደምታደርግ ቃል
ገባችልኝና ነገሩ በዚህ ተዘጋ::

የትምህርት ቤቱ ጸሐፊ በሆነችው ሙስሊም እና በእኔ መካከል
አንዳንድ ግጭቶች መፈጠር ጀመሩ:: እኔም እርሷን ወደ ሌላ ቦታ
አዛውረው በጥሩ ጸሐፊ እንዲተኩልኝ አመለከትኩ:: አንድ ቀን የአስ
ተዳደር እና ፋይናንስ ኃላፊው ት/ቤቱን ሊጎበኝ ሲመጣ ጉዳዩን አነ





ሣሁበት:: እርሱም ይህችኛዋን ጸሐፊ አዛውሮ በሌላ ትጉኅ፣ ቀል
ጣፋ፣ ጠንካራ እና ተግባቢ በሆነች ጸሐፊ እንደሚተካልኝ ቃል ገባ::
ምን ያደርጋል ታድያ፣ ልጂቱ ክርስቲያን ናት:: «ጸሐፊ ማለት እኮ
በእያንዳንዱ ነገር የምንገናኝ ሰው ናት፤ ፈጽሞ ክርስቲያን ልትሆንማ
አትችልም» ስል አምርሬ ተቃወምኩ:: ኃላፊው ግን በጸሐፊነት ተግ
ባር ወሳኝ የሆነውን ታማኝነትን ገንዘብ ያደረገች በመሆንዋ ልቀበ
ላት እንደሚገባ አሳመነኝ:: እንዲያውም እርሷን የሚያምነውን ያህል
ራሱን እንደማያምን ነገረኝ::

አዲሷ ጸሐፊያችን ሳሚያ ትባላለች:: ለዳይሬክተሯ ሪፖርት
ለማድረግ ስትመጣ ምን እንደምትመስል ለማየት በዳይሬክተሯ ቢሮ
ቁጭ ብዬ ጠበቅኳት:: እኔን የምትመለከትበት መንገድ የተለየ ነው::
ከሁሉም ሰዎች አስቀድማ በትኅትና ሰላም አለችኝ:: እኔም በለበጣ
ፈገግታ ምላሹን ሰጠኋት:: እርሷ ግን ሳትናደድም ሳትገረምም ፈገግ
አለች:: በአንገቷ ላይ ትልቅ የቆዳ መስቀል አጥልቃለች:: እኔም
«ለት/ቤቱ አዲስ በመሆኗ ማን እንደሆንኩና ምን እንደምፈልግ ገና
አልገባትም ማለት ነው» አልኩ:: «አንድ ሰው ወደፊት ሲነግራት
ያለ ማንገራገር ለትእዛዞቼ ሁሉ ተንበርካኪ ትሆናለች» ብዬ
አሰብኩ::

በነጋታው ቢሮዩ ድረስ እንድትመጣ ነገርኳት:: እርሷም ያለማወ
ላወል አደረገችው:: በትዕቢት መንፈስ አንገቴን ወደ ወንበሩ አዘን
ብዩ እንድትቀመጥ አመላከትኳት:: እርሷም እሺ ብላ ተቀመጠች::
የምታደርገውን ሁሉ በአትኩሮት እከታተል ነበር:: ቀድሞ ከማውቃ
ቸው ሁሉ ለየት ያለች ናት:: ጠንካራ ሰብእና፣ ድፍረት፣ የደስደስ
ያለው ገጽታ እና በራስ የመተማመን ችሎታ ታድሏታል:: ምንም
ዓይነት ትችት ባዘንብባትም አትደናገጥም:: የምፈልጋቸው ዓይነት
ጠባይዕት ያሏት ሴት ትመስላለች::

በሕይወቴ ለመጀመርያ ጊዜ ሐፍረት ተሰማኝ:: ምንም እንኳን
እኔ የ45 ዓመት ሴት እርሷ ደግሞ በሠላሳዎቹ ውስጥ ያለች ወጣት
ብትሆንም ውስጤ ግን ከእርሷ እጅግ ያነስኩ ያህል ይሰማው ነበር::

የሥራ ግንኙነታችንን ሁኔታ መላልሼ ገመገምኩት:: ሳሚያ
ሥራዬን ቀላል እና ቀና ለማድረግ ዘወትር ትጥራለች:: ከእኔ በላይ
የእኔን የሥራ ጫና ተሸክማለች:: የምትወደኝ መሆንዋን እንድገነዘብ
ለማድረግ ምንጊዜም ጥረት ታደርጋለች:: እኔ ግን ይህንን ሁሉ ክብ
ካቤና ጥንቃቄ ለእኔ ለማድረግ ለምን እንደምትፈልግ ዕንቆቅልሽ
ሆኖብኛል:: ምናልባትም በት/ቤቱ ያሉ ክርስቲያኖች ስለ እኔ ጠባይ
እና ከእኔ ምን መጠበቅ እንዳለባት አስቀድመው ሳይነግሯት እንዳ

ልቀሩ ገምቻለሁ:: ሳሚያን ከመጥላት ይልቅ እንዴውም በየጊዜው እየወደድኳት መጣሁ:: ለየት ያለ የንግግር ችሎታ፣ ለስላሳ ድምፅ፣ ትኅትና እና ጥበብ በእርሷ ዘንድ አሉ:: የተረጋጋ እና ሰላማዊ የሆነ ድባብም በዓይኗ ላይ ረብቧል:: እኔ ግን ስለ እነዚህ ነገሮች አንሥቼ አስተያየት ሰጥቻት አላወቅም::

ምንም እንኳን የትምህርት ቤቱ ንግሥት እኔ መሆኔን ባውቅም እርሷ ግን በሁለመናዋ ከእኔ ላቅ ብላ ትታይ ነበር:: እኔም እያደር ሳሚያን ይበልጥ እየወደድኳት መጣሁ:: በመካከላችን መራራቅ ቀርቶ ወዳጅነት እየጠነከረ መጣ:: ከውስጧ አንዳች ልዩ የሚስብ ፣ የሚማርክ እና የሚቆጣጠር ነገር አላት:: እኔም ይህንን ተሰጥኦዋን ለመመርመር ወደድኩ:: ለዚህ እንዲያመቸኝም የሆነ ምክንያት እየፈጠርኩ እርሷን ወደ ቢሮዬ እጠራት ነበር::

አንድ ቀን በጥቅምት 1987 ዓም ለብዙ ሰዓታት ሳንሰለቻች ከተጨዋወትን በኋላ «ሳሚያ ለመሆኑ በእግዚአብሔር ታምኛለሽ?» ስል እንደዋዛ ጠየቅኳት:: እርሷም «አዎ፤ ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ አምላክ የለም» ስትል መለሰችልኝ:: ጆሮዬን ማመን ነው ያቃተኝ:: እጅግ በጣም ተገርሜ «ክርስቲያኖች በአንድ አምላክ ብቻ ነው እንዴ የሚያምኑት?» ስል ጠየቅኳት:: እርሷም መለስ አድርጋ «አዎን በአንድ አምላክ ነው የምናመልከው» ስትል መለሰችልኝ:: እኔም «እኔ እንደሚገባኝ ግን ክርስቶስ እና ድንግል ማርያም የሚባሉ ተጨማሪ አማልክት አሏችሁ::» አልኳት:: እርሷም ተመቻቸችና «ያማ በብዙ አማልክት ማምለክ ነው:: እኛኮ በብዙ አማልክት አናመልክም፤ የምናመልከው በአንድ አምላክ ነው::» ቀጠል አድርጋም «ድንግል ማርያም የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ናት እንጂ አምላክ አይደለችም» ስትል ገለጠችልኝ::

አንድ ትልቅ ፒራሚድ አናቴ ላይ የተናደ ነበር የመሰለኝ:: 'ክርስትና በአንድ አምላክ ማመንን ያስተምራል' የሚለው ለእኔ እንግዳ ነገር ነው:: ይህ ጉዳይ እኔ ስለ ክርስትና ከማስበው ፈጽሞ የተለየ ነው:: ለክርስቲያኖች አስቸጋሪ እና ጨካኝ የሆንኩት ባለማወቄ መሆኑ ገባኝ:: ምንም እንኳን በውስጤ ፀፀት እና ሐፍረት ቢሰማኝም ከእርሷ ግን ብዙ ነገር ለመስማት ጓጓሁ:: በክርስቲያኖች ላይ የፈጸምኩት ሁሉ ትዝ አለኝ:: ምን ዓይነት አሰቃቂ ወንጀል ነው በእነርሱ ላይ ስፈጽም የኖርኩት? ስለ እነርሱ የበለጠ ለማወቅ ጓጓሁና «እስቲ ስለ ክርስትና ንገሪኝ» ስል ጠየቅኳት::

ስለ ክርስትና መናገር ስትጀምር የዕጣን መዓዛ ክፍላችንን ዐወደው:: የሚገርም እኮ ነው:: እንዲህ ያለ መዓዛ ከዚያ በፊት ሸትቶኝ





አያውቅም:: ዐቅሌን የሳትኩ መሰለኝ:: ለመሆኑ በሕልሜ ነው ወይስ በእውኔ ይህ ሁሉ የሚሆነው? ስል ራሴን ጠየቅኩ:: ሃሳቤን እንደ ምንም አሰባሰብኩና ገለጻዋን በጥሞና መከታተል ጀመርኩ:: «ድንግል ማርያም ከእናት ከአባትዋ ተለይታ አሥራ ሁለት ዓመት እስኪሆናት ድረስ በቤተ መቅደስ በሃይማኖታዊ ሥነ ሥርዓት አደገች:: ከዚያም በትውፊቱ መሠረት ይጠብቃት ዘንድ ለአንድ አረጋዊ አደራ ተሰጠች፤ ነገር ግን በሁለቱ መካከል ምንም ዓይነት ግንኙነት ሳይኖር ኢየሱስ ክርስቶስን ወለደች»

በመሐል አቋረጥኳትና «ልክ ነሽ ይህማ በቁርዐንም ተገልጧልኮ» አልኳት:: ከዚያ በኋላ ውይይቱን መቀጠል አልቻልኩም:: የድካም እና የመድረቅ ስሜት ተሰማኝ:: ውይይታችንም እዚያ ላይ ተገታ:: እርሷም በውስጤ የፈጠረችውን ነገር ሳትረዳ ቢሮውን ለቅቃ ወጣች:: እንደ እውነቱ ከሆነ ላጠፋው የማይቻለኝ እሳት ለኩሳብኝ ነበር የሄደችው::

ከዚያ ውይይት በኋላ «ክርስቶስ ማነው?» እያልኩ ለራሴ መጠየቅ ጀመርኩ:: ስሙ በተነሣ ቁጥር ከዚህ ቀደም አጋጥሞኝ የማያውቅ እንግዳ ስሜት ውስጤን ይሰማኛል:: የሚያጽናና፣ የሚያስደስት ዓይነት ስሜት:: ባላውቀውም እንዲሁ እወድደው ጀመር:: ስለ እርሱ በሚገባ የማወቅ ጉጉት አደረብኝ::

ለዚህ ስል ከሳሚያ ጋር ይበልጥ መቀራረብ ጀመርኩ:: ከእርሷ ጋር የማደርገውን ውይይት በማለዳ ለመወጠን ስላሰብኩ በጠዋት ት/ቤት እገባ ጀመር:: ከተዋወቅንበት ዕለት ጀምራ የምትወድደኝ መሆኑን እንድረዳ አድርጋኛለች:: በት/ቤቱ የሚገኙ ክርስቲያኖች የነገሯትን ማስፈራርያዎች ሁሉ ተቋቁማ እኔን ለመከባከብ እና ለመቅረብ መሞከሯም የዚህ ማሳያ ነው:: እንደ እውነቱ ከሆነ ወዳጇ እሆን ዘንድ ፍቅሯ አስገድዶኛል::

ይህ ሁሉ እየሆነ እንኳን ክፉ ሃሳቦች በኅሊናየ መመላለሳቸው አልቀረም:: እናም አንድ ቀን ታማኝነቷን መፈተን አለብኝ ብዬ ተነሣሁ:: አንድ ጊዜ ከተሰበሰበው የት/ቤቱ ክፍያ 1000 ፓውንድ አንሥቼ ደጋግሜ መቁጠሬን እና ስሕተት ሊገኝበት እንደማይችል ከነገርኳት በኋላ በድብቅ አሥር ፓውንድ ጨምሬ ሂሳቡን እንድትሠራው ሰጠኋት:: ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ «ተጨማሪ አሥር ፓውንድ አገኘሁ» ብላ መለሰችልኝ:: በሌሎች ተመሳሳይ አጋጣሚዎችም ታማኝነቷን ፈትኛለሁ:: ነገር ግን ልትበገር አልቻለችም:: ስለዚህም በአነጋገሬ እርሷን ለማበሳጨት እና ትዕግሥቷን ለመፈታተን ፈለግኩ:: ንግግሯን ሆን ብዬ አንቋሽሻለሁ:: ሃሳቧን አጣጥለዋለሁ:: መቃ

ወም በሌለብኝ ነገር ሁሉ እቃወማታለሁ:: እርሷ ግን ምንም እንዳል ተፈጠረ አድርጋ ታልፈዋለች:: ትኅትናዋን እና ትዕግሥቷን በምንም መንገድ አታጣውም:: ፈገግታዋ እና ሰላማዊ ጠባይዋ አይለዩዋትም:: አንዳንዴማ ይህንን የማደርግበትን ምክንያት ቀድማ ያወቀች ሁሉ ይመስለኛል::

እንዲህ እንዲህ እያሉ ብዙ ቀናት አለፉ:: ስለ ክርስቶስ የማሰቡ ነገር ግን ፈጽሞ ሊተወኝ አልቻለም:: ሳሚያን ስለ ክርስቶስ እና ስለ ትምህርቱ በየጊዜው እጠይቃታለሁ:: የሚገርመው ነገር እርሷ ስለ ክርስቶስ መናገር ስትጀምር የሚያስደስት የዕጣን መዓዛ ክፍላችንን ያውደው ነበር:: ታድያ ስለ ክርስቶስ በምናደርገው ውይይት እና በዕጣኑ መዓዛ መካከል ያለው መስተጋብር የማወቅ ጉጉቴን ይበልጥ አቀጣጠለው:: ይህ ሁኔታ ሲደጋገምብኝም ጊዜ ምናልባት የእኔን የማወቅ ጉጉት ለመጨመር በማሰብ ሳሚያ አንዳች የሚሸት ነገር ደብቃ እያመጣች ውይይት ስንጀምር እየረጨችው ይሆን እንዴ? ብዬ ማሰብ ጀመርኩ::

ይህንን ለማጣራት ደግሞ በምትናገርበት ጊዜ የምታደርገውን ሁሉ በንቃት መከታተል ጀመርኩ:: ነገር ግን ምንም ነገር ማግኘት አልቻልኩም:: ቀጥዬም ምናልባት በክፍሉ እና በውይይታችን መካከል አንዳች ግንኙነት ካለ ብዬ በመገመት ቦታውን ለመለወጥ ወሰንኩ:: ከዚያ ቀን ጀምሮ አንዳንድ ቀን ወደ ፎቁ ሌላ ጊዜ ደግሞ ወደ አትክልቱ ሥፍራ ሄደን እንወያያለን:: በጣም የሚገርመው ግን የዕጣኑ መዓዛ በምንሄድበት ቦታ ሁሉ ይከተለን ነበር:: በመጨረሻም የሳሚያን ትምህርት ትክክለኛነት ለማረጋገጥ እግዚአብሔር የሚሠራው ተአምር ነው ብዬ አመንኩ::

ተምታታብኝ!

ግራ ተጋባሁኮ!

ለመሆኑ እውነቱ የት ነው ያለው?

አምላኬ በሙሉ ልቤ እና በሙሉ ሰውነቴ እንደምወደው ያውቃል:: ነገር ግን ደግሞ ከእርሱ እንደራቅሁ ሆኜ ይሰማኛል:: ይህ ስሜት ደግሞ በጣም እየጎዳኝ ነው:: ከእርሱ መራቄን ባሰብኩት ቁጥር ውሳጣዊው ሕመሜ ይበረታብኛል:: ይህ ነው እንግዲህ መቆሚያ እና መቀመጫ የሚያሳጣኝ:: እየተረዳሁት እንደመጣሁት ከሆነ በእኔ እና በአምላኬ መካከል የመከለያ ግንብ ተዘርግቷል:: በፍርድ ቀን በፊቱ ቆሜ ለሠራሁት ሥራ እንደምጠየቅ ዐውቃለሁ:: ነገር ግን ሕይወቴን ስገመግመው ከኃጢአት ብቻ በቀር የሠራሁት አንዳች በጎ





ነገር የለም:: ስለሆነም ምንም ይሁን ምን እውነቱን ማወቅ አለብኝ ብዬ ወሰንኩ::

በኅዳር 15 ቀን 1987 ዓም ሳሚያ ወደ ቢሮዬ አርፍዳ ነበር የመጣችው:: ደስተኛ እና ፍልቅልቅ ሆና ነበር:: እኔም ሁኔታዋ ስለገረመኝ «እንዲህ በጣም ደስተኛ የሆንሺው ምን አግኝተሽ ነው» ስል ጠየቅኋት:: እርሷም እየተፍለቀለቀች «ዛሬ እኮ የገና ጾም የመጀመርያው ቀን ነው» አለችኝ:: እኔም በአሽሙር «ደግሞ ክርስትና ጾምን ይቀበላል? ለመሆኑ በደንብ ትጾማላችሁ ወይስ እየበላችሁ እና እየጠጣችሁ ጾምን ትላላችሁ?» አልኳት:: እርሷም «እንደርሱ አይደለም፤ እኛ ክርስቲያኖች በርግጥ እንጾማለን፤ ለረዥም ሰዓታትም ከመብላት እና ከመጠጣት እንቆጠባለን፤ ከዚህም በተጨማሪ በጾም ወቅት የተቀደሰ ሕይወት እንኖራለን» ስትል አብራራችልኝ::

ከዚህ በኋላ በምትለው ነገር ላይ መቀለድ አልቻልኩም:: ዝምታዋን በርጋታ ሳስተውለው ቆየሁ:: በመካከልም ካደረገችው መስቀል ጀርባ አንዳች የሚያንጸባርቅ ነገር ተመለከትኩና «ምንድን ነው?» ስል ጠየቅኋት:: «የድንግል ማርያም ሥዕል ነው» ስትል መለሰችልኝ:: ገረመኝና «በዚያ ጊዜ ፎቶ ግራፍ የሚያነሡ ወይስ ሥዕል የሚስሉ ሰዎች ነበሩ እንዴ? ሥዕሏ ከየት ተገኘ? ደግሞስ ሰዓሊዎቹ የእርሷ ሥዕል ለመሆኑ እንዴት ርግጠኞች ሆኑ? እነዚህ ክርስቲያኖች ሞኞች ናቸው ማለት ነው፤ አንድ ሰዓሊ በሃሳቡ የፈጠረውን ሥዕል የድንግል ማርያም ሥዕል ነው ብሎ አሳምኗቸዋል ማለት ነው:: ደግሞ የሚገርመው ነገር እነርሱ እውነት ነው ብለው መቀበላቸው ነው »

ይህንን እያሰብኩ እያለ ከመስቀሉ ጀርባ ይታየኝ የነበረው ነፀብራቅ ጠፍቶ ደማቅ ብርሃን በቦታው ተተካ:: ዓምድ የመሰለ ቅርጽ ሠርቶ የዕጣኑ ጢስ ወደ ላይ ሲወጣ አየሁት:: ወዲያውም ቤቱ በመዓዛው ታወደ:: በጢሱ ውስጥ አንዲት ሴት ቆማ ተመለከትኩ:: ደርባባ ናት:: ፊቷ ላይ አይቼው የማላውቀው ገጽታ ይነበባል:: ወደ እኔ እያየች ፊት ለፊቴ ነበር የቆመችው:: ሰማያዊ ቀሚስ ለብሳ እጆቿን ወደ እኔ ዘርግታለች:: በልቤ «ድንግል ማርያም ትሆን እንዴ?» ብዬ አሰብኩ:: ኮማ ውስጥ የገባሁ መሰለኝ:: የማየው ሁሉ በእውኔ አልመስልሽ አለኝ:: ደግሞ ልጠራጠረው በማልችል ሁኔታ አይቻታለሁ:: ወዲያው ያቺ ሴት ከፊቴ ተሠወረች::

ወደ ልቡናዬ ስመለስ እኔ እና ሳሚያ በዕንባ ተሞልተን ነበር:: ከዚያ በኋላ የድንግል ማርያምን ሥዕል በተመለከተ የተሞኘሁት እኔ መሆኔን እና የነገረችኝ እውነት መሆኑን ተረዳሁ:: ውስጤ ተረበሸ:: ባዶ የሆንኩ እና ዙርያዬም በገለባ የተሞላ መስሎ ታየኝ::

«አምላክ ሆይ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ዐውቅ ዘንድ እባክህ ርዳኝ።»

የሥራ ሰዓቴ ሲያልቅ በቀጥታ ወደ ቤቴ አመራሁ። በሦስቱ ልጆቼ ላይ ዓይኖቼን ተክዬ «አሁን እኔ ክርስቲያን ብሆን ምን ይሰማቸው ይሆን፤ የአባታቸውስ ምላሽ ምን ይሆን ይሆን? አባታቸው የአልዛሃር ዩኒቨርሲቲ[5] ዋና አስተዳዳሪ ነው። በርግጥ ከ1983 ዓም ጀምሮ ተፋትተናል። ነገር ግን ለልጆቻችን ደኅንነት እና ጤናማነት ስንል በትዳር እንዳሉ ሰዎች በአንድ ቤት ነው የምንኖረው። የቤተሰቦቼ አመለካከት እና ያላቸው ሥልጣን ፊቴ ድቅን አለ። ሁሉም የሐፍረታቸው ምንጭ አድርገው ሊመለከቱኝ እንደሚችሉ ጥርጥር የለውም።

ደግሞስ እኔ ራሴ በስንት መከራ ያገኘሁት ክብር እና ሥልጣንስ ቢሆን፤ ይህንን ሁሉ አፈር ድሜ ሳስግጠው ነው ማለት ነው።» እነዚህ ሁሉ በሃሳቤ ሲወጡ እና ሲወርዱ ግራ መጋባቴን አባባሱብኝ። ለመሆኑ ቤተሰቦቼ ክርስቲያን መሆኔን ቢያውቁ የራስዋ መብት ነው ብለው ይተውኛል? ፈጽሞ! የአእምሮ ሕመምተኞች ወዳሉበት ቤት ነው የሚያስገቡኝ።

ሌላው ቀርቶ ለሃይማኖቴ እቀናለሁ ብሎ የሚያስብ አንዱ ሊገድለኝም ይችላል። ይህ በእስልምና ዘንድ የ«ሪዳህ»ን ሕግ[6] እንደመፈጸም ይቆጠራልና።

በመሐል አንድ መፍትሔ ብልጭ አለልኝ። «አምላክ እኔን ከሙስሊም ቤተሰብ ተወልጄ ሙስሊም ሆኜ እንድኖር ፈጥሮኛል። ስለዚህም እንዲህ ስላለው ጉዳይ ዳግመኛ ማሰብ የለብኝም። ደግሞም በጥረቴ ያገኘኋቸውን እነዚህን ሁሉ ዕድሎች ማበላሸት የለብኝም። እንዲያውም ሳሚያ ወደ እኔ ቢሮ ዳግመኛ እንዳትመጣ ማድረግ አለብኝ። ውይይታችንም ሥራን በተመለከተ ነገር ብቻ መሆን አለበት። ካሁን በኋላ እንደ ቀድሞዬ በመሆን አምላኬ እውነቱን እንዲገልጥልኝ መጸለይ ብቻ ነው ያለብኝ። ነጻ ጊዜ ሳገኝም የቁር

5. የአልዛሃር ዩኒቨርሲቲ ካይሮ፣ግብፅ ውስጥ የሚገኝ ከ1300 ዓመት ዕድሜ በላይ ያለው በዓለም ላይ ዕድሜ ጠገብ ታዋቂ የእስልምና ዩኒቨርሲቲ ነው።

6. የ«ሪዳሕ» ሕግ ማለት ሃይማኖቱን የካደን ሰው መቅጣትን የሚፈቅድ ሕግ ነው። ይህ ሕግ እስልምናን ትቶ ወደ ሌላ ሃይማኖት የገባ ሰውን ሙስሊሞች እንዲገድሉት ያዝዛል። የሚገድሉት ሰዎችም ገነትን እንደሚወርሱ ያረጋግጣል። ሌላው ቀርቶ ሰውየው ሌላ እምነት ሲቀበል እያዩ ዝም የሚሉ ሰዎች እነርሱ ራሳቸው እንደ ከሃዲ ስለሚቆጠሩ ተመሳሳይ ፍርድ እንደሚጠብቃቸው ያትታል።





ዐንን ቃላት ማስታወስ አለብኝ። ከእንግዲህ እንዲህ በመሰለው ነገር መጠመድ የለብኝም» ብዬ ወሰንኩ።

በቀጣዩ ቀን ቁርዐኔን ገለጥኩና ማገላበጥ ጀመርኩ። አምላኬም ሳላስበው ወደ «ሱረቱ መርየም»[7] መራኝ። በመጽሐፉ ውስጥ:-

16. መርየምንም ከቤተሰቧ ወደ ምሥራቃዊ ሥፍራ በተለየች ጊዜ (የኾነውን ታሪኳን) አውሳ።

17. ከነሱም መጋረጃን አደረገች፤ መንፈሳችንንም (ጅብሪልን) ወደርሷ ላክን፤ ለእርሷም ትክክለኛ ሰው ሆኖ ተመሰለላት።

18. - እኔ ከአንተ በአልረሕማን እጠብቃለሁ፤ ጌታህን ፈሪ እንደሆንክ (አትቅረበኝ) አለች።

19. - እኔ ንጹሕን ልጅ ለአንቺ ልሰጥሽ የጌታሽ መልእክተኛ ነኝ አላት።

20. (በጋብቻ) ሰው ያልነካኝ ኾኜ፤ አመንዝራም ሳልሆን እንዴት ልጅ ይኖረኛል! አለች።

21. አላት:- ነገሩ እንደዚህሽ ነው፤ ጌታሽ:- እርሱ በእኔ ላይ ገር ነው፤ ለሰዎችም ታምር ከኛም ችሮታ ልናደርገው (ይህንን ሠራን) የተፈረም ነገር ነው ፤አለ፤ (ነፋባትም)።

22. ወዲያውኑም አረገዘችው፤ በርሱም (በሆድዋ ይዛው) ወደ ሩቅ ሥፍራ ገለል አለች።

23. ምጡም ወደ ዘንባባይቱ ግንድ አስጠጋት፣ ዋ ምኞቴ! ምነው ከዚህ በፊት በሞትኩ፣ ተረስቼም የቀረሁ በኾንኩ፤ አለች።

24. ከበታቿም እንዲህ ሲል ጠራት:- አትዘኝ ጌታሽ ከበታችሽ ትንሽ ወንዝ በርግጥ አድርጓል

25. የዘምባባይቱንም ግንድ ወዳንቺ ወዝውዢት፤ ባንቺ ላይ የበሰለ የተምር እሸት ታረግፍልሻለችና።

26. ብይም፣ጠጭም፤ ተደሰችም፤ ከሰዎችም አንድን ብታይ:- እኔ ለአል ረሕማን ዝምታን ተስያለሁ፤ ዛሬም ሰውን በፍጹም አላነጋግርም በይ።

7. የማርያም ታሪክ የተጻፈበት የቁርዐን ክፍል ነው።

27. በርሱም የተሸከመችው ኾና ወደ ዘመዶችዋ መጣች:- መርየም ሆይ ከባድን ነገር በእርግጥ ሠራሽ አሏት።

28. የሃሩን እኅት ሆይ አባትሽ መጥፎ ሰው አልነበረም! እናትሽም አመንዝራ አልነበረችም አሏት።

29. ወደርሱም ጠቀሰች፤ በአንቀልባ ያለን ሕፃን እንዴት እናናግ ራለን! አሉ።

30. (ሕፃኑም) አለ:- እኔ የአላህ ባርያ ነኝ፤ መጽሐፍን ሰጥቶኛል፣ ነቢይም አድርጎኛል።

31. በየትም ስፍራ ብኾን ብሩክ አድርጎኛል፤ በሕይወትም እስከአለሁ ሶላትን በመስገድ ዘካንም በመስጠት አዞኛል።

32. ለእናቴም ታዛዥ(አድርጎኛል፤ ትዕቢተኛ፣ እምቢተኛም አላደረገኝም።

33. ሰላምም በእኔ ላይ ነው፤ በተወለድሁ ቀን በምሞትበትም ቀን ሕያው ኾኘ በምቀሰቀስበትም ቀን፤[8]

ሁሉም ነገር ግራ የሚያጋባ ሆነብኝ። ለመሆኑ እውነቱ የት ላይ ነው ያለው? መረጋጋት አልተቻለኝም። የበፊቱን ውሳኔየን ተውኩና እውነቱን ለመፈለግ እንደገና ተነሣሁ። በውስጤ የሚተራመሰውን ነገር እንዲሁ ንቄ ማለፍ አልቻልኩም።

«ይህቺ ሴት የአንድ ተራ ሰው እናት ከሆነች በቁርዐን ውስጥ ይህ ሁሉ ምስጋና እንዴት ሊጻፍላት ቻለ? ክርስቶስስ አንድ ተራ ሰው ወይም ነቢይ ከሆነ ከተፈጥሮ ሕግ በላይ በሆነ እንዲህ ባለ መንገድ እንዴት ሊወለድ ቻለ? ይህንን ሁሉ ኃይል፣ ሙታንን ማስነሣት፣ ድውያንን መፈወስ፣ ዕውራንን ማብራት፣ ለምጻምን ማንጻት፣ እንዴት ለእርሱ ከአምላክ ሊሰጠው ቻለ? ደግሞም እነዚህ ሁሉ ተአምራት በቁርዐን ተመዝግበዋል»

«እንዲሁም ሳሂህ አል- ቡካሪ[9] ክርስቶስን በተመለከተ በሐዲት

8. <u>የተርጓሚው ማስታወሻ</u> :-ይህንን የቁርዐን ክፍል የአማርኛውን ትርጉም እንግሊዝኛውን ከመተርጎም ብዬ ነጃሽ አሳታሚ በ1997 ዓም ካሳተመው የአማርኛ ቁርዐን ነው የወሰድኩት።

9.ሐዲት ማለት የነቢዩ መሐመድን አባባሎች ሰብስቦ የያዘ መሆኑ በሙስሊሞች ዘንድ ይታመናል። ሙስሊሞች ሐዲትን ከቁርዐን እኩል የሆነ ቦታ ሰጥተው የሚቀበሉት መጽሐፍ ነው።በውስጡ ያለውም በነቢዩ መሐመድ በኩል የተነገረ የአላህ ቃል ነው ብለው ያምናሉ። ሳሊሀ አል ቡካሪ እና ሳሂህ የተሰኙት የሐዲት መጻሕፍት እውነተኞች፣ሊጠቀሱ የሚ ችሉ፣ታማኞች እና በደንብ የተጠናቀሩ የሐዲት ቅጅዎች ተደርገው ይታመናሉ።





ላይ "የመርየም ልጅ ኢሳ እስኪመጣ ድረስ ጊዜው አልደረሰም ነበር። እርሱ በፍትሕ እና በርትዕ ይመራችኋል" ይላል። ታድያ አሁን የት ነው ያለው? ላለፉት 2000 ዓመታት በገነት ተቀምጦ እስከ መጨረሻው ቀን ይጠብቃል ማለት ነው? እርሱ ከሰዎች ሁሉ የተለየ ነው ማለት ነው? እርሱ ከሰዎች ሁሉ በላይ ነው ማለት ነው? ታድያ እርሱ ማን ነው?

በውስጤ ውጊያ እየተካሄደ ነው። በአንድ በኩል እኔን ከፈጣሪዬ ሊለዩኝ በሚጥሩት ኃያል እና አስጨናቂ ሃሳቦቼ፣ በሌላ በኩል ደግሞ እውነትን ለማወቅ በማደርገው ጉዞ መካከል ውጊያው ቀጥሏል።

1987 አልፎ 1988 እስኪተካ ድረስ ረዣዥም እና አስጨናቂ ቀናት አለፉ። ዓመቱ ሲጠናቀቅም የግብጽ ክርስቲያኖች የጌታን የል ደት በዓል የሚያከብሩበት ቀን ደረሰ[10]። እኔም ራሴን እንደገና መጠ የቅ ጀመርኩ። «የልደት በዓል? የማን የልደት በዓል? ለመሆኑ በዓሉ የሚከበርለት ክርስቶስ ማነው?» ታኅሳስ ሃያ ዘጠኝ ቀን በት/ቤታችን ለሚገኙ ክርስቲያኖች የበዓል ቀን ነበር። በዚያ በገና ቀን ከት/ቤት ወደ ቤት ስመለስ የኀዘን ስሜት ተጫጭኖኝ እና በስጋት መንፈስ ውስጥ ነበርኩ። አየሩ ቀዝቀዝ ያለ ነበር። በቀጥታ ከሁለቱ ሴቶች ልጆቼ ጋር ወደምንጋራው መኝታ ቤቴ ሄድኩ። ሌሊቱን ሙሉ ስገላበጥ ባድርም እንቅልፍ ግን በዓይኔ ሊዞር አልቻለም። ልቤ በጉጉት ስለተሞላ መንፈሴ መረጋጋት አቅቶታል።

ለራሴ ታማኝ መሆን አለብኝ አልኩ። ለምን እፈራለሁ፤ ይልቅስ ከማንም በላይ መፍራት ያለብኝ ፈጣሪዬን ነው። እውነቱን ከማወቅ እየሸሸሁ እንዴት አምላኬን እወደዋለሁ ብዬ አፌን ሞልቼ መናገር እችላለሁ። ፈጣሪዬን ፊት ለፊቴ ቆሞ ያገኘሁት መሰለኝ። እናም ልቤን ሰብስብ አደረግኩና ጥልቅ በሆነ ስሜት «ፈጣሪዬ ሆይ ምን ያህል እንደምወድድህ አንተ ታውቃለህ። ምን ያህል እንደማከብር ህም ትረዳለህ። ፍላጎቴ ሁሉ ያለ ኃጢአት ካንተ ጋር መኖር ነው። እባክህ ፈጣሪ እውነቱን ግለጥልኝ? እንዴት ነው ላውቅህ የምች ለው?» ብዬ ጸለይኩ።

እንደገና ደግሞ መለስ ብዬ «ጥፋቴ ምንድን ነው? የተወለድኩት ከሙስሊም ቤተሰብ ነው። ታድያ ይህ ለመሆኑ ተጠያቂዋ እኔ ነኝ?» አልኩ።

10.የግብጽ ክርስቲያኖች እንደ ኢትዮጵያውያን ሁሉ የልደትን በዓል የሚያከብሩት ታኅሳስ 29 ቀን ነው። የአውሮፓ ክርስቲያኖች ግን በታኅሳስ 15 ቀን ነው።

ፈራሁ እንዴ? ኧረ በጭራሽ! ጌታ ሆይ አባክህ እለምንሃለሁ:: ከልጅነቴ ጀምሮ በበረከትህ አጥለቅልቀህኛል:: የጠየቅኩህን ነገር ሁሉ መልሱን በሕልም ትገልጥልኛለህ:: ወደ አንተ የመምጫ መንገዱ ክርስትና ከሆነ መስቀሉን አሳየኝ፤ እስልምና ከሆነ ደግሞ ሌላ ምልክት አሳየኝ:: ከዚያ በኋላ አንተ ያዘዝከኝን እፈጽማለሁ:: የፈለገው ነገር ይምጣ እንጂ ለእኔ ዋናው ነገር አንተ ነህ:: ማንንም አልፈራም:: ጊዜያዊው ክብሬ እና መዓርጌም ግድ አይሰጠኝም:: እኔ የሚገደኝ ካንተ ጋር ያለኝ ግንኙነት ነው:: ለእኔ ልጆቼ ዋናዎቹ ነገሮች አይደሉም:: ዋናው ነገር አንተ ነህ:: አንተን ካገኘሁ ከዚያ በኋላ አንተ ትጠብቀኛለህ:: ቢገድሉኝም እንኳን ወደ አንተ የምመጣበትን መንገድ ያሳጥሩልኛል እንጂ አይጎዱኝም::

እንደዚያ ሌሊት ልቤ ተግቶ አያውቅም:: ልክ ፊት ለፊቱ ተቀምጬ ከፈጣሪዬ ጋር የማወራ ነበር የመሰለኝ:: እስከ ሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ ልቤ ነቅቶ እንቅልፍ ሳይዞርብኝ ነበር የቆየሁት:: ሊነጋጋ ሲል ደካከመኝና ራሴን አዞረኝ:: ከዚያም ሰዓቴን አሥራ ሁለት ሰዓት ላይ እንዲቀሰቅሰኝ ሞላሁትና አልጋዬ ላይ በድካም ተዘረጋሁ:: ዓይኔን ለመክደን ሞከርኩ:: ነገር ግን ይህንን ያህል ደክሞኝ እንኳን እንቅልፍ ሊወስደኝ አልቻለም::





# ምዕራፍ ሦስት

# ጌታዬን አየሁት

ዘርፋ መሬት የደረሰ ረዥም ገዋን ለብሼ ድንገት ራሴን በራእይ አየሁት:: ገዋኑ ግራጫ መልክ ሲኖረው በብር የተሸለመ ሆኖ ረዣዥም እጅጌዎች አሉት:: ያደረግኩትን ቀሚስ የመሰለ ሰፊ ቀበቶ ወገቤ ላይ ታጥቄያለሁ:: ተመሳሳይ ቀለም ያለው ሻሽም በራሴ ላይ አሥሬ ነበር:: በለበስኩት ልብስ በጣም ከመደሰቴ የተነሣ «ይህንን የመሰለ ልብስ ያገኘሁት መቼ ነው?» እያልኩ ራሴን እጠይቅ ነበር:: እንደዚህ ያለ ገዋን ከዚህ በፊት አይቼ አላውቅም:: ያንን የመሰለ ውብ ነገርም በሕይወቴ አላጋጠመኝም:: አስገራሚ ነው::

ዝቅ ብዬ ስመለከት ባዶ እግሬን ነኝ:: ነገር ግን ቀሚሱ ረዥም ሆኖ እግሬን ስለሸፈነልኝ ግድ አልነበረኝም:: መሬቱን ሳየው አስደናቂ መልክ ነበረው:: ደማቅ አረንጓዴ:: እንደዚያ ዓይነት ውብ ቀለም ከዚያ በፊት አይቼ አላውቅም:: እንደዚያ ዓይነት ለስላሳ ነገርም ገጥሞኝ አያውቅም:: ይህ ለስላሳ መስክ ምን እንደሆነ ለማወቅ ስለፈለግኩ በእግሬ ደጋግሜ ፈተግ ፈተግ አደረግኩት:: ምንጣፍ ነው ልበል? ኧረ ፈጽሞ! ሐር መሆን አለበት:: ከዚያም ቃላት ሊገልጡት የማይቻላቸውን ድንቅ ነገር እመለከት ዘንድ ዓይኖቼን አነሣሁ::

ይህ አሁን የማየው ነገር በምናባችን ብቻ የምንስላቸውን ቤተ መንግሥቶች ይመስላል:: ኧረ እንዲያውም ከዚያም በላይ እጅግ አስደናቂ ነው! ይህ ነገር በሃሳባችን ልንደርስበት ከምንችለው በላይ ነው:: እጅግ ታላቅ የሆነ ቤተ መንግሥት ፊት ለፊቴ ይታየኛል:: ረዣዥም ዓምዶች አሉት:: የዓምዶቹን ጫፍ ዓይን ሊደርስበት አይችልም:: ዓምዶቹ በሚያምር ሐር የተንቆጠቆጡ እና ውብ ብርሃን የሚፈነጥቁ ናቸው:: አካባቢው በዕጣን ታውዷል:: አዎ ይህንን መዓዛ ዐውቀዋለሁ:: ከሳሚያ ጋር ስለ ክርስቶስ ስንነጋገር የሚያውደን መዓዛ ነው:: ይህኛው ግን ከዚያም ይበልጣል::

ቀዝቀዝ ያለ ነፋስ በላዬ ላይ ሲነፍስ ተሰማኝና ልቡናዬ በሐሴት ተሞላ:: ርግቦች በላዬ ላይ ክንፋቸውን እያራገቡ ሲበሩ የሚሰማኝ ዓይነት ስሜት ተሰማኝ:: ርግቦቹን አላያቸውም ነገር ግን አሁንም የሚያልፉ ይመስለኛል:: ሰላም፣ ጸጥታ፣ መጽናናት በልቤ ውስጥ ነግሠዋል::

በዙርያዬ በተዘረጋው መስክ ላይ ወዲያ እና ወዲህ ስል በድንገት በመካከሉ ላይ ረዥም እና ሰፊ ከሆነ ዙፋን ፊት ደረስኩ:: ከኋላው የቤተ ክርስቲያን ዶም የመሰለ ነገር ይታየኛል:: እኔም ጠጋ አልኩና ወዲያ እና ወዲህ እያልኩ መጎብኘቴን ቀጠልኩ:: በጉብኝቴ መካከል አንድን እንግዳ ለመቀበል የተዘጋጀ በሚመስል ሁኔታ የክብ ሩብ ሠርተው የቆሙ ሽማግሌዎች ተመለከትኩ:: በጣም ደማቅ የሆነ ነጭ ልብስ ለብሰዋል:: ራሳቸውንም በሚያንፀባርቅ ነጭ መሸፈኛ ሸፍነዋል:: ጢማቸው ረዣዥም እና ነጭ ነው:: እርስ በእርሳቸው በሆነ ጉዳይ ላይ የሚወያዩ ይመስል በቀስታ ይነጋገራሉ:: ምን እንደሚሉ ለማወቅ እችል ዘንድ ወደ እነርሱ ተጠጋሁ:: ነገር ግን የሚናገሩትን ማወቅ አልቻልኩም::

እነርሱን ባሉበት ትቼ ወደሌላ ቦታ ዘወር ብዬ ያንን ውብ ሥፍራ መጎብኘት ቀጠልኩ:: የዓይኖቼ መቃድ ሙሉ በሙሉ ሊያየው አልተቻለውም:: ያ ሥፍራ ፈጽሞ ዳርቻው ሊታይ አይቻልም::

በዚህ መካከል በድንገት አንድ ሰው ብቅ አለ::

እንዴት እና ከየት እንደመጣ አላወቅኩም:: ያ ሰው ወደዚያ ታላቅ ዙፋን ሲያመራ እነዚያ ሽማግሌዎች ለእርሱ ተንበረከኩ:: እርሱ ይሄዳል፤ ነገር ግን በመሬት ላይ በእግሩ ሲሄድ አይታይም:: በደመና ወይም ጥላ በመሰለ ነገር ተጭኖ የሚሄድ ነው የሚመስለው:: በዚህ ሁኔታ ወደ ዙፋኑ ደርሶ ተቀመጠ::

እንዴት አስደናቂ ነገር መሰላችሁ:: ለካ ሳላስበው እና ልብ ሳልለው እኔም እርሱን በመከተል ላይ ነበርኩ:: እስከ ዙፋኑ ድረስ ተከትዬው ሄድኩና እግሩ ሥር ተደፋሁ:: እንግዳ እና ምሥጢራዊ የሆነ ስሜት ወረረኝ:: ደስታ፣ ፍርሃት፣ ርካታ፣ ሰላም፣ ተቀላቅለው ይሰሙኛል:: ኤሌክትሪክ የያዘኝ ይመስል ኃይለኛ ንዝረት በሰውነቴ ተሰማኝ:: ራሴን መቆጣጠር አልቻልኩም:: እናም ከቁጥጥሬ ውጭ በሆነ ሁኔታ እንቀጠቀጥ ነበር::

«ይህ ምሥጢራዊ ስሜት ምንድን ነው?» ስል ራሴን ጠየቅኩት:: «ከእነዚህ ሽማግሌዎች ጋር አብሬ የሰገድኩለት ይህ ማን ነው?» ማንነቱን ለማወቅ እችል ዘንድ አንገቴን ቀና አድርጌ ማየት አለብኝ አልኩና ኃይሌን ሰብስብ አድርጌ ቀና ብዬ አየሁት:: እግዚኦ! ምንድን ነው እባካችሁ የማየው! በጭራሽ ልገልጠው አልችልም:: እርሱን ልገልጥባቸው የምችልባቸው ተስማሚ ቃላት ማግኘት ይቸግረኛል:: የሚያበራ ገጽ፣ ይህስ እብነ በረድ የመሰለ ነገር ምንድን ነው? ይህ ውበትስ ምንድን ነው? የፊቱ ገጽታ ላስተዋለው የደከመው እና የታከተው ይመስላል:: ቀጭን በቀለማት ያሸበረቀ ልብስ





ለብሷል:: በግራ ትከሻው ላይ እንደ ደም የቀላ የአንገት ልብስ ጣል አድርጓል:: ወርቃማ ፀጉሮቹ በትከሻዎቹ ላይ እንደ አጥላስ ተዘናፍለው ወርደዋል::

ለምን ግን እንደዚህ አዘነ? አልኩኝ በልቤ:: ዓይኖቹ ተከድነዋል:: እጆቹ ጉልበቱ ላይ አርፈዋል:: አንገቱ ዘንበል ብሏል:: የሚገርመው ነገር አንዴ ካዩት በኋላ ዓይንን ከእርሱ መንቀል አይቻልም:: አንድ ነገር የሚፈልግ ይመስላል:: ገጽታውን ሳየው ደስተኛ አይመስልም:: ፊቱ በኀዘን ተሞልቷል:: ይህ ታላቅ ሰው ማነው? እያልኩ ደጋግሜ ራሴን እጠይቅ ነበር:: እንዲህ ያለ ውብ ንጉሥ አይቼም ሰምቼም አላውቅም:: ይህንን ታላቅ ሰው ያሳዘነው ማን ይሆን?

ብሩኅ ገጹን እና አስደናቂ የሆነውን አንገቱን በመመልከት ላይ ነበርኩ:: ባየሁት ቁጥር ይበልጥ ወደ እርሱ እሳባለሁ:: በተጠጋሁት ቁጥር ደግሞ ስለ እርሱ ለማወቅ ይበልጥ እጓጓለሁ::

ድንገት ዓይኑን ገለጠና ወደ እኔ ተመለከተ:: ዓይኖቹን በዓይኖቼ ለማየት ስላልቻልኩ አቀርቅሬ መሬት መሬቱን ማየት ጀመርኩ::

ኦ ጌታዬ ! ምንድን ነው ያየሁት? እነዚህ ዓይኖች ምንድን ናቸው?

ባየሁት ነገር የተነሣ ራሴን የምስት ወይም ደግሞ የምሞት መሰለኝ:: ዓይኖቹ ታላላቅ፣ ኃይለኛ እና፣ የፀሐይ ጨረር የመሰለ ብርሃን የሚፈነጥቁ ናቸው:: የዓይኖቹ መቃዶች ሰፋፊ እና ዓለሙን በሙሉ ሊይዙ የሚቻላቸው ናቸው:: ቀለማቸው እንደ ጠራ ሰማይ ወይም ደግሞ በአረንጓዴ ቀለም የተለወሰ ውኃ ይመስላሉ:: እንደ ኤሌክትሪክ እየነዘሩኝ በውስጤ የሚያልፉት እነዚያ የብርሃን ጨረሮች ምንድን ናቸው? ለአፍታ እንኳን ችዬ ላየው አልቻልኩም:: በሚገባ ማንነቱን ለማወቅ ወደድኩ፤ ደግሞ በልቤ ውስጥ አንዳች እንድወድደው የሚያደርገኝ ነገር አለ:: ላየው በጣም እፈልጋለሁ፤ እናም ያለ የሌለ ዐቅሜን አሰባስብኩና ራሴን ቀና አድርጌ አየሁት:: አ! እንዴት ያስደንቃል:: ትኩር ብሎ ይመለከተኛል:: ወደ እኔ ይበልጥ የቀረበ መሰለኝ:: እንዴት ያለ ገጽ ነው? ፍቅር፣ ርጋታ፣ ጽንዕ::

የሚለምን በመሰለ ድምፅ «ይበቃል ናህድ» ሲለኝ በአፍጢሜ ተደፋሁ:: ይህንን ፍቅር ፣ይህንን ርኅራኄ፣ ይህንን ደግነት ልቋቋመው አልተቻለኝም:: ያየሁትን ነገር እንዴት ባለ ቋንቋ ልግለጠው:: ይህ ታላቅ ሰው እንዲህ እያለ የሚለምነኝ እኔ ማነኝ? እርሱ ከምትወድድ እናት በላይ የሚያፈቅር ነው:: ይህ ታላቅ ሰው ስሜን ያውቃል:: የጠራኝም በስሜ ነው:: እርሱ በሚገባ ያውቀኛል ማለት ነው:: ነገር ግን «ይበቃል ናህድ?» ሲል ምን ማለቱ ነው? የተና

ገረውን ነገር ልረዳው አልቻልኩም። ልጠይቀው ይሆን? አልኩ። ፈጽሞ! እንዲህ ያለውን ሰው ሊጠይቁት የሚያስችል ዐቅም አይገኝም። እርሱን ሊታዘዙለት ብቻ የሚገባ ነው። እነዚህ ሃሳቦቼ በኀሊናዬ ተመላለሱ። ደግሞምኮ ለጥያቄው አፋጣኝ ምላሽ መስጠት አለብኝ። ራሴን አረጋጋሁና «አዎ ይበቃል! ኧረ ይበቃል!» ብዬ መልሱን ሰጠሁት።

እርሱን ለማወቅ ይበልጥ ስለ ጓጓሁ ዐቅሜን አሰባስቤ ለሦስተኛ ጊዜ ላየው ፈለግኩ። እናም ቀና ብዬ ሳየው ወደ እኔ ይበልጥ ተጠግቷል። በቀደመው ዓይነት ፍቅር፣ ደግነት እና ርኅራኄ ያየኛል። አሁንም በልመና መልኩ «ርግጠኛ ነሺ ናህድ?» ሲል ጠየቀኝ። በነፍሴ ውስጥ የተሠወረውን ፈልፍሎ የሚያይ ይመስል የዓይኖቹ ጨረሮች ውስጤን ዘልቀውኝ ሲገቡ ይታወቀኛል። ለሁለተኛ ጊዜ እግሩ ሥር ተደፋሁ። ይህንን የመሰለ ፍቅር፣ ይህንን የመሰለ ደግነት እና ርኅራኄ ገጥሞኝ አያውቅም። ይህ ሁሉ ለእኔ ነው? ይህ ታላቅ ንጉሥ ለእኔ ይህንን ያህል ትኩረት ይሰጠኝ ዘንድ እኔ ማነኝ? እንደ ገና ከራሴ ጋር በሃሳብ ወደ መከራከር ተመለስኩ «ርግጠኛ ነሺ?» ያለኝ ምኑን ነው? ምን ማለቱ እንደሆነ ግልጽ አልሆነልኝም። ነገር ግን በማናቸውም ነገር ልታዘዝለት ዝግጁ ነበርኩ። ምን ማለት ነው? ብዬ መጠየቅ አላሻኝም። ራሴን ቀና ሳላደርግ ባለሁበት አቀርቅሬ «አዎን ርግጠኛ ነኝ» ስል መለስኩለት።

ማነፃፀርያ የሌለውን ፍቅሩን ቀምሻለሁና ልቤ በፍቅሩ ተሞላ። ምንም እንኳን ፍርሃት በውስጤ ቢሠርጽም ለአራተኛ ጊዜ ኃይሌን አሰባስቤ እርሱን ለማየት ቀና አልኩ። መረጋጋት፣ ደስታ እና ሰላም ውስጤን አጥለቀለቁት። አየሁትኮ! እጅግ ድንቅ ነው። ደግሞም ወደ እኔ ይበልጥ - ተጠግቷል። ፍቅርን በተሞሉ ዓይኖቹ እያየኝ በተረጋጋ እና ለስላሳ በሆነ ድምፅ «በዚህ ጉዳይ ላይ ደግሜ መጨነቅ የለብኝም ናህድ?» አለኝ። እኔም አንገቴን ደፍቼ «በእርግጠኝነት! ስለዚያ ነገር ከአሁን በኋላ አትጨነቅም፣ ፈጽሞ አትጨነቅም» ስል መለስኩለት። ቀጠል አደረገናም «ወደ እኔ ተመልከቺ» አለኝ። እኔም አንገቴን እንደ ደፋሁ «አልቻልኩም» አልኩት። እርሱም በሚያረጋጋ ድምፅ «አትፍሪ አይዞሺ! ወደ እኔ ተመልከቺ» አለኝ። «አትፍሪ» የሚሉትን ቃላት ስሰማ እውነትም ፍርሃቴ ጥሎኝ ሄደ። አንገቴን ቀና አድርጌ አየሁት። መቼም ውበቱን የሚገልጡ ቃላት አይገኙም። ከዓይኖቹ የሚረጩት ጨረሮች የሚያስደምሙ እንጂ የሚያስበረግጉ አይደሉም። ጌታ ሆይ ይህ ሁሉ ምንድን ነው? ፍቅር፣ ደግነት፣ ልስላሴ፣ ርኅራኄ፣ ንጽሕና፣ ቅንነት፣ ያየሁትን ሁሉ ዘርዝሬ ለመግለጥ ፈጽሞ ያስቸግረኛል።





ጥቂት ደቂቃዎች አለፉ። አሁንም እርሱን እርሱን በማየት ላይ ነበርኩ። ቀስ በቀስ ወደ እርሱ እየተጠጋሁ ነው። ከዚያም ለስለስ ባለው ድምፁ «ምን እያየሺ ነው?» ሲል ጠየቀኝ። እየፈተነኝ ይሆን እንዴ? ብዬ አሰብኩ። ለአፍታ ዝምታ ዋጠኝ። አስብ አደረግኩና «ሕፃን ልጅ ይታየኛል» ስል መለስኩለት። ያን ጊዜ በፊቱ ላይ ይነበብ የነበረው ኀዘን ፀሐይ እንደመታው ደመና ተገፍፎ ጠፋ። ፈገግ ግን አላለም። ከዚያም እንደገና ዓይኖቹ በዕንባ ተሞልተው አየሁ። ቀጥሎም ዕንባው በልብሶቹ ላይ የሚያልፍ ወንዝ መስሎ ከዓይኖቹ ሲወርድ ተመለከትኩ። እኔም አብሬው ለረዥም ሰዓታት ያህል አለቀስኩ። ሰውነቴ በብርቱ ተርገፈገፈ። በርግጥ ውስጤ ደስታ ተሞልቶ ነበር። ትክክለኛውን ምላሽ በመስጠቴ ደስተኛ የሆነ ይመስለኛል። ጥቂት ተጨማሪ ደቂቃዎች ደግሞ አለፉ። ሰውነቴ አልጋዬን ሲመታው ታወቀኝ። ከዚያም ነቃሁ።

ዓይኔን ስገልጥ ራሴን እንደመሳት ያልኩ መሰለኝ። የት ነኝ? የትስ ነበርኩ? እነዚያ ለብሻቸው የነበሩ ልብሶችስ የት ሄዱ? ለተወሰነ ጊዜ ያህል አእምሮዬ የዞረ መሰለኝና ተምታታብኝ። ዳግም ወደ ዚያ ቦታ መሄድ ፈለግኩ። እባክህ ከአንተ ርቆ ከሚኖረው ከዚህ ዓለም እኔም እንድርቅ እርዳኝ። በእያንዳንዱ የሕልውናዬ ጉዞ ሁሉ እወድሃለሁ፤ ከልቤ እወድሃለሁ፤ በሕይወቴ አግኝቼ በማላውቀው ዓይነት ፍቅር እንደምትወድደኝ ተረድቻለሁ። እነዚያ ከዓይኖቹ ይወጡ የነበሩት ጨረሮች እንደ አዲስ የብረት ቅይጥ አቅልጠውኛል። ያንን ልመናውን አሁንም አስታውሰዋለሁ።

ዓይኖቹን ወደ እኔ ዘወር ሲያደርግ ይወጡ የነበሩት የብርሃን ጨረሮች ክበብ ይሠሩ ነበር። ረጋ ያለው ደግ ድምፁ አሁንም በጆሮዬ ያቃጭላል። ይህን ሁሉ ማሰብ በደስታ እንድዋጥ አድርጎኛል። እርሱ ከማንኛውም ዓይነት እሳቤ እና ማነፃፀርያ ሁሉ በላይ ነው። እርሱ የሚያስደንቅ ኀብር ነው። ደግ፣ ሩኅሩኅ፣ አፍቃሪ ቢሆንም ደግሞም ኃያል ነው። እርሱን ለመግለጥ መጀመሩ እንኳን ያስቸግረኛል።

ዝም ብዬ ተመስጬ ከቆየሁ በኋላ ሴት ልጄን ቀሰቀስኳት። የሕልሜ ነገር በእውን የተፈጸመ ያህል ሆኖ ስለተሰማኝ እርሷም እንደ እኔው ያየቺው መሰለኝ። እናም በጉጉት «ከእኔ ጋር ይነጋገር የነበረውን ሰው አይተሺዋል?» ስል ጠየቅኳት። እንደመወራጨት አለችና

ቀሰስ ባለ ድምፅ «እማዬ ድምፅሺን ዝቅ አድርጊው፣ ማን ነው ሲያወራሽ የነበረው?» አለችኝ:: ያየሁትን ነገር ገለጥኩላት:: «ይህ መልአክ ነው፣ መልአክ መሆን አለበት» ስትል ነገረችኝ:: በምላሿ አልረካሁም:: በጭራሽ ያለችው እንዳልሆነ ልቤ ተረድቶታል:: ማን እንደ ሆነ ውስጤን ገብቶታል:: የተናገረኝ ቃል ምን ማለት እንደሆነ ተረድቼዋለሁ::

እርሷን ተውኩና ወደ ወንዱ ልጇ አልጋ ሄጄ ለሴቷ ልጇ የነገርኳትን ነገርኩት:: እርሱም እንደ እርሷ ተደነቀ:: እንደዚያ ባለ ሁኔታ አይቶኝ አያውቅም:: እናም «እማዬ ድምፅሺን ቀንሺው፣ መልአክ ሳይሆን አይቀርም፣ የገለጥሺልኝ ነገር ከመልአክ ሁኔታ ጋር የሚመሳሰል ነው» የሚል ምላሽ ሰጠኝ:: ነገር ግን ያለው ፈጽሞ አላሳመነኝም:: እኔ ራሴ ለራሴ ማረጋገጡ ቢከብደኝም ያየሁት ማን እንደሆነ ገብቶኛል:: ከፍ ብሎ የሚሰማውን የኛን ንግግር ሰምቶ ባለቤቴም ከመኝታ ክፍሉ መጣ:: ለእርሱም ያየሁትን ነግሬ ማን እንደሆነ እንዲነግረኝ ጠየቅኩት:: እርሱ ደግሞ «ጻድቁ ዮሴፍ መሆን አለበት ፤እርሱ ተመሳሳይ የሆነ መልክ አለው» አለኝ:: ይህም ቢሆን አልተስማማኝም:: እኔኮ ማን እንደሆነ ዐውቄዋለሁ:: ያየሁት ነገር የሚያስደንቅ እና የተረዳ በመሆኑ ከሆነ አካል ማረጋገጫ ባገኝ ደስ ይለኛል::

ልክ በሌላ ዓለም ያለሁ ያህል እየተሰማኝ በጠዋቱ ወደ ት/ቤት በፍጥነት ገሠገሥኩ:: ያየሁት እና የሰማሁት ነገር ማንንም የሚያስደንቅ ነው:: ወደ ሳሚያ አመራሁና «በራእይ ያየሁትን የዚያን ታላቅ ሰው መግለጫ ይስማማዋል የምትይው ማንን ነው?» ስል ጠየቅኳት:: ገርሟት ታየኛለች:: ያየሁትን ሁሉ አንድ በአንድ ዘርዝሬ መንገር ስጀምር ራሴን መቆጣጠር ተሳነኝና አለቀስኩ:: በራእይ ያየሁትን ነገር አሁን ያየሁት ያህል ቆጥሬ ስተርክላት እጅግ እንቀጠቀጥ ነበር::

ያንን ታላቅ ሰው ደግሜ አየሁት፤ ያንን ሩኅሩኅና ደግ ድምፅ ደግሜ ሰማሁት፤ ተርኬላት ስጨርስ ሳሚያ በአግራሞት ትመለከተኝ ነበር:: ቦርሳዋን ከፍታ የተወሰኑ ሥዕሎች አሳየችኝ:: ከሥዕሎቹ መካከልም የተወዳጁን የኢየሱስ ክርስቶስን ሥዕል አነሣሁና «ያየሁት ይህንን ነው የሚመስለው:: ያኛው ግን ከዚህ እጅግ የሚበልጥ ግሩም ድንቅ ነው» አልኳት:: የሳሚያን ምላሽ መጠበቅ አላስፈለገኝም:: በእርግጥ ያየሁት ኢየሱስ ክርስቶስን እንደሆነ ከአስተያየቷ አረጋግጫለሁ:: ሳሚያም «ስለ ጉዳዩ ካህኑን ጠይቄ ምላሹን እነግርሻለሁ» አለችኝ::





ወደ ቢሮዬ ሳመራ ሞፊድ የተባለው ክርስቲያን መምህር በሃሳቤ መጣ:: በትምህርት ቤታችን የሳይንስ መምህር ሲሆን ላለፉት ሁለት ዓመታት ለእኔ መልካም የሥራ ጓደኛ፣ ታማኝ እና እምነት የሚጣልበት ዓይነት ሰው ነበር:: በት/ቤቱ በሚገኙ ክርስቲያኖች ላይ የምፈጽመው ክፉ ነገር ሁሉ እንዳለ ሆኖ እርሱ ግን ለእኔ ምንጊዜም የማይለወጥ መልካም ሰው ነበር:: በንግግሬ ባበሳጨውም፣ ጥቃት ባደርስበትም፣ ከእርሱ አልፌ በት/ቤቱ በሚገኘው የክርስቲያን ማኅበረሰብ ላይ የማይገባ ተግባር ብፈጽምም እርሱ ግን ቻይ ሰው ነበር:: ከእኔ ክፉ ጠባይ በተቃራኒው ለእኔ በጎ አመለካከት ነበረው:: ምንጊዜም ደግሞ ለእኔ መልካም ነገር ከማድረግ አይቆጠብም::

ቢሮዬ ስገባ የዕለቱን ጋዜጣ እያነበበ አገኘሁት:: አጠገቡ ስደርስ «ምን ተከሠተ?» ሲል ጠየቀኝ:: ከወንበሬ የወደቅኩ ያህል ነው የተሰማኝ:: እንደምንም ችዬ በራእይ ያየሁትን ተረክሁለት::

ያየኋትን እያንዳንዷን ነጥብ እንዳስታውስ ጠየቀኝ:: አሁንም በልዩ ስሜት ውስጥ ነበርኩ:: ራሴን መቆጣጠር አቃተኝና አለቀስኩ:: ሞፊድ ሰማይ ምድሩ ዞሮበት ያየኛል:: ያየሁትን ሁሉ ተርኬለት ስጨርስ «ይቅር በይኝ፤ ቅድም የነገርሽኝን እንደገና ልትነግሪኝ ትችያለሽ?» ሲል ለመነኝ:: ደግሜ እንደዚያው ተረክሁለት:: አሁንም እንድደግምለት ጠየቀኝና ደገምኩለት:: ለሦስተኛ ጊዜ ነግሬው ስጨርስ ራሱን ቀና አድርጎ «ተመስገን ጌታ ሆይ» አለና አመሰገነ:: ከዚያም ወደ እኔ ዘወር ብሎ «ማን እንደሆነ በርግጥ ማወቅ ትፈልጊያለሽ?» ሲል ጠየቀኝ:: እኔም «ምን ጥርጥር አለው፤ እፈልጋለሁ እንጂ» ስል መለስኩለት:: ረጋ ብሎ «እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» አለኝ:: ምንም እንኳን አስቀድሜ ያ ያየሁት ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ርግጠኛ ብሆንም እርሱ ሲደግምልኝ ግን የበለጠ ተደሰትኩ::

ውስጤን አንዳች ኃይል ያተራምሰዋል:: እናም እየተንቀጠቀጥኩ አለቀስኩ:: ሞፊድ እንድረጋጋ ሊረዳኝ ሞከረ:: ነገር ግን በቀላሉ ማረጋጋት እንዳልተቻለው ሲያውቅ በሩን ዘጋውና ክፍሉን ትቶልኝ ወጣ:: አሁንም አሁንም መረጋጋቴን ለማረጋገጥ ብቅ እያለ ያየኝ ነበር:: መረጋጋቴን ሲያረጋግጥ ወደ ቢሮዬ ገብቶ ተቀመጠ:: እኔም እርሱን እርሱን ማየት ጀመርኩ:: የሆነውን ነገር ሁሉ እያሰብኩ «ክርስቶስን አየው ዘንድ እኔ ማነኝ? ክርስቶስ በዚህ መልኩ ያናግረኝስ ዘንድ እኔ ማነኝ? እርሱ በለስላሳ፣ በተረጋጋ፣ እና በትኁት ድምፁ ይለምነኝ ነበር:: «ይበቃል ናህድ?» ሲለኝ ምን ማለቱ ነው? አሁንም ሩኄን የሳትኩ መሰለ:: ይህ ሁሉ ፍቅር እና ደግነት ለእኔ አይገባኝም ነበርኩ::

በመኝታ ክፍሌ ውስጥ አልጋዬ ላይ እንዳልነበርኩ ርግጠኛ ነኝ:: ችዬ ለመግለጥ በማልሞክረው አንድ ሌላ የተለየ ቦታ ውስጥ ነበርኩ:: ያየሁትን ነገር አሟልተው ሊገልጡ የሚቻላቸው ቃላት የሉም:: ሞፌድ እየደጋገመ «ርግጥ ነው የእግዚአብሔርን ስጦታ ለመቀበል የበቃን አይደለንም፤ ከታላቁ ቸርነቱ ብዛት የተነሣ እንጂ» ይለኛል:: «በኃጢአቴ የተነሣ አፈርኩ፤ በትከሻዬ ላይ ተራራ የተጫነኝ መሰለኝ፤ ይህ ሁሉ ቢሆንም እርሱ ግን ከቃላት በላይ የሆነ ፍቅሩን ገልጦልኛል::» አልኩት::

ሞፌድ ጨዋነት በተሞላ መልኩ «እርሱ ኃጢአተኞችን ይወድዳል፣ በኃጢአታቸው ንስሐ ሲገቡ ደግሞ "ኃጢአታችሁን ሁሉ ይቅር ብያለሁ፤ ከእንግዲህም ደግሜ አላስብባችሁም" ይላል:: ደጉ እና ሩኅሩኁ ጌታችን ማለት ይህ ነው» አለኝ:: «ምን ማድረግ አለብኝ?» ስል ሞፌድን ጠየቅኩት:: ሞፌድም «ምንም፤ ብቻ በትዕግሥት ጠብቂው፤ በአንቺ የሚሠራውን ሥራ እስኪፈጽም እና እርሱ ራሱ እስኪመራሽ ድረስ፤ ተረጋጊ፤ እናም በተለመደው መንገድ እየኖርሽ ጠብቂው» ሲል መለሰልኝ:: ከዚያም ወጥቶ ሄደ::

ቀናት ከቀናት በኋላ እየመጡ ተከታትለው አለፉ:: የማስበው ነገር ቢኖር እነዚያን ብሩኃን ዓይኖቹን ነው:: የሰማሁት ነገር ቢኖር ትኁት የሆነውን ድምፁን ነው፤ ጌታ ሆይ ለእኛ ለኃጢአተኞች ፍቅርህ እንዴት ታላቅ ነው? አንድ ቀን እንዲህ ስል ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ጀመርኩ:: ልክ ከፊቴ የቆመ ያህል ነበር የሚሰማኝ:: «መፍቀሬ ኃጥኣን እግዚአብሔር ሆይ፣ እኔ በራሴ አፈርኩ፤ እንዲህ በብዙ በረከቶች ያጥለቀለቅከኝ ለምንድን ነው? ይህንን ጸጋ ያደልከኝስ ምን አድርጌልህ ነው? ከኃጢአቴ ብዛት የተነሣ ቀና ብዬ መሄድ አልተቻለኝም::

አቤቱ አንተን ለማወቅ በማደርገው ፍለጋ እባክህ ምራኝ፤ ድካሜን ተረድተህ አበርታኝ፤ እርዳኝም:: ለመሆኑ አንተን አይ ዘንድ፣ ካንተስ ጋር እነጋገር ዘንድ እኔ ማን ነኝ?» እያልኩ በልቤ ስጸልይ ድንገት እንዲህ የሚል ድምፅ ሰማሁ

«አንድ ተልዕኮ አለሽ» የሰማሁትን ማመን አልቻልኩም::

ነገር ግን ያው መልስ ዳግም ተሰማኝ::

-«አንድ ተልዕኮ አለሽ»- አለኝ::

እኔም ተገርሜ «እኔ! ጌታ ሆይ» አልኩኝ::





ለሦስተኛ ጊዜ ያው ድምፅ

«አዎን አንድ ተልዕኮ አለሽ፤ ተረጋጊ፣ በጽንዐት ቁሚ፣ አትቸኩይ፣ በነገሮችም አትደናገጭ» አለኝ::

ሰላም እና መረጋጋት በውስጤ ሰፈነ:: «እግዚአብሔር ሆይ ሁለመናዬ ያንተ ነው፣ እንደ አንተ ፈቃድ እንጂ እንደ እኔ አይሁን፤ ለምትፈልገኝ ዓላማ ሁሉ ይሄው ተጠቀምብኝ፤ ምንም ነገር አልልግም፤ የምፈልገው ከአንተ ጋር መሆን ብቻ ነው:: ገና ከመጀመርያው ምን ያህል እንደምትወደኝ ተረድቻለሁ፤ እኔም የምትወድደኝን ያህል እወድህ ዘንድ እሻለሁ:: አንተን ማገልገል እንዴት ያለ ክብር ነው ! እንዴት ያለስ ብኩርና ነው! እንዴትስ ያለ ደስታ ነው!

እባክህ ርዳኝ፤ ጌታ ሆይ ለአንተ ፈቃድ መገዛት እንድችል አጽናኝ፤ በልቡናዬ ውስጥ አንተ ብቻ ኑር፤ እስከ መጨረሻው ያንተ ነኝ፤ እስከ መጨረሻዋ ሕቅታ ድረስ ላንተ የታመንኩ እንድሆን እርዳኝ»

እናም ከክብር ጌታ ጋር ከተገናኘች በኋላ ለናህድ ዓለሙ ሁሉ ከንቱ ሆነባት:: ከዓይኖቹ ከፈሰሰችው ከአንዲቷ ዘለላ ዕንባ በላይ ዋጋ ያለው አንዳች ነገር በዓለም ላይ የለም:: ከእርሱ በተጨማሪ ምንም አልፈልግም:: በርሱ ፍቅር፣ ደኅንነት፣ ሰላም አሉ:: ሙሉነት ከእርሱ ይገኛል:: ያውም ምንም የማይጎድለው ሙሉነት::

# ምዕራፍ አራት

# የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ

አያሌ አስጨናቂ እና የተወጣጠሩ ቀናት አለፉ:: በየዕለቱ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ይበልጥ ለማወቅ ጉጉቴ ይጨምራል:: እርሱን የበለጠ ለማወቅ እና ክርስትናን ለመረዳት ፍላጎቴ ወሰን አልነበረ ውም:: መጽሐፍ ቅዱስ ለማንበብ፣ ቅዳሴ ለማስቀደስ፣ ወደ ቤተ ክር ስቲያን ለመሄድ እፈልጋለሁ:: ግን እንዴት ተደርጎ! ከካህን ጋር ለመ ገናኘት ፍላጎት ነበረኝ:: ነገር ግን ካህናቱ ሁሉ ከእኔ ጋር ላለመገ ናኘት እንደሚፈልጉ ጥርጥር የለኝም:: ላለፉት ዓመታት ወደ ት/ቤቴ ለጉዳይ ለሚመጡ ክርስቲያኖች ሁሉ ፤መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች የስቃያቸው ምንጭ እንደነበርኩ የታወቀ ነው:: ዛሬ ግን እኔ ራሴ ክርስቲያን ሆንኩ::

ሳሚያን ከካህን ጋር መነጋገር እንደምፈልግ እና መጽሐፍ ቅዱስ ይኖረኝም ዘንድ እንድትረዳኝ ነገርኳት:: እርሷም ለካህኑ እንደ ነገራቻቸውና ከእኔ ጋር ለመገናኘት እጅግ ደስተኛ እንደሆኑ ገለጠ ችልኝ:: ነገር ግን የምንገናኝባቸውን መንገዶች ለማመቻቸት ጥቂት ጊዜ እንደሚወስድ አስረዳችኝ:: መጽሐፍ ቅዱሱን በተመለከተ ግን «የት ታነቢዋለሽ?» የሚል ጥያቄ ነበር ያቀረበችልኝ:: «ት/ቤት እንዳ ታነቢው ቢሮሽ ሰው የማይጠፋበት ነው፤ ቤትሽ ደግሞ ልጆችሽና ባለቤትሽ አሉ» አለችኝ:: ልክ ይህንን ስትነግረኝ ከጥቂት ወራት በፊት ቁልፉን የገዛሁትን አፓርትመንት አስታወስኩትና «በአፓርት መንቴ ውስጥ አነበዋለሁ» አልኳት:: ያንን አፓርትመንት ቁልፉን በገዛሁበት ጊዜ የግድ የሚያስፈልገኝ ሆኖ አልነበረም የገዛሁት:: ሌላው ቀርቶ በዚያ ወቅት ለመግዛት የሚያጓጓ ነገር እንኳን አልነበ ረኝም:: እንዲሁ ብሩን ስላገኘሁ ብቻ ነበር የገዛሁት:: አሁን ግን የገዛሁበትን ምክንያት ዐወቅኩት::

የፖሊስ ጄኔራል የነበረው አባቴ በአባሲያ[11] በሚገኘው የመኮን ኖች ሕንፃ ትልቅ አፓርትመንት ነበረው:: እርሱ ሲያርፍ አፓርት መንቱን ልንሸጠው ወሰንን:: ከሽያጩ ገቢ ለኔ የደረሰኝ ውርስ 7000 ፓውንድ ያህል ነበር:: ያንን አፓርትመንት የገዛሁት በዚህ ብር ነው:: በወቅቱ አፓርትመንቱን መግዛቴን ልጆቼ አልደገፉትም ነበር:: እኔ ግን የግድ ተጭኛቸው ነው የገዛሁት:: ውስጡን አስተ

11.አባሲያ ካይሮ አጠገብ የሚገኝ ቦታ ነው::





ካክዬ የሚያስፈልጉትን ነገሮች ባሟላለትም እስካሁን ግን አንድም ቀን ተቀምጬበት አላውቅም::

አንድ ቀን በሃሳብ ውስጥ ገብቼ ወደ ት/ቤት ስጓዝ በመንገዱ ላይ ለሚተራመሱት መኪኖች ትኩረት አልሰጠሁም ነበር:: መኪና ሊገጨኝ ለጥቂት ነው ያመለጥኩት:: ብሩኅ ዓይኖች፣ ሰላማዊ እና ረጋ ያለ ድምፅ- ጌታዬ ከእኔ ጋር በራእይ ሲነጋገር ያየኋቸው እና የሰማኋቸው ነገሮች – ውስጤን እያስደመሙኝ ነበር የምጓዘው:: ከሁ ሉም በላይ ደግሞ በሕይወቴ የምወጣው ተልዕኮ እንዳለኝ እያሰብኩ ነበር:: መኪናው ሊገጨኝ ሲል ሳላስበው «በስመ አብ ወወልድ ወመ ንፈስ ቅዱስ» አልኩኝ:: በጣም የጮኽኩ ስለመሰለኝ ማን ሰምቶኝ ይሆን? ብዬ አካባቢዬን ቃኘሁት:: ነገር ግን ማንም አልሰማኝም ነበር:: እንዲህ ባለ ሁኔታ እየተንቀጠቀጥኩ ት/ቤት ደረስኩ::

የሆነውን ሁሉ ለሳሚያ ደጋግሜ ነገርኳት:: ከዚያም ብዙዎቹ ክርስቲያኖች እንደሚያደርጉት በትእምርተ መስቀል አማተብኩ:: እርሷም «ይህንን ማን አስተማረሽ» ስትል ተደንቃ ጠየቀችኝ:: መኪ ናው ሊገጨኝ ሲል አንድ ሰው አስተማረኝ» አልኳት:: እርሷም «መልካም ነው፤ በይ እስከ ፍጻሜው እንበለው» አለችና «አሐዱ አም ላክ፤ አሜን» ብላ ደመደመች:: ቀጥላም የማማተብን ትርጉም ነገረ ችኝ:: «ከግንባራችን ወደ ደረታችን ስናማትብ እግዚአብሔር ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወለደ ማለታችን ነው:: ከግራ ወደ ቀኝ ስናማትብ ደግሞ እኛን ከጨለማ ወደ ብርሃን መለሰን ማለ ታችን ነው» አለችና አከል አድርጋ «ስትሸበሪ፣ መረጋጋት ሲሳንሽ፣ ምን ጊዜም በጠዋት ስትነሺ፣ እንዲሁም ወደ አልጋሽ ስታመሪ እግዚ አብሔር በዚህ ቀን ያስተማረሽን አስታውሺ፤ እርሱ እንደ መሻትሽ ይመልስልሻል፤ ነገር ግን ተጠንቀቂ፤ ይህንን ስታደርጊ ማንም እንዳ ያይሽ» አለችኝ::

ምንኛ ደስተኛ ሆንኩ መሰላችሁ:: የእግዚአብሔር ሥራስ ምንኛ ድንቅ ነው::

«ጌታ ሆይ ተመስገን፤ በፍቅርህ ዕቅፍ ውስጥ ልዩ የሆነ ቦታ አግኝቻለሁና:: አንተው ራስህ ልቤን ሰብረህዋል:: ጌታ ሆይ ክብር እና ምስጋና ላንተ ይሁን:: ቀሪውን ዘመኔን ሙሉ እንኳን ከእግርህ ሥር ተንበርክኬ ባሳልፈው፣ ውለታህን ለመክፈል አይቻለኝም:: አን ዷን ቅንጣት እንኳን መክፈል አልችልም:: ስጦታህ ምሉዕ ነውና::»

ወደ ቢሮዬ ሳመራ እንደተለመደው ሞፌድ ቢሮዬ ውስጥ ተቀ ምጦ የዕለቱን ጋዜጣ ሲያነብ አገኘሁት:: «በስመ አብ ወወልድ ወመ ንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን» ብየ በማማተብ ሰላምታ ሰጠ

ሁት። ሞፈድም ፈገግ አለና «እግዚአብሔር ራሱ ይመራሻል፣ ያስተምርሻልም አላልኩሽም» አለኝ። ከዚያም «ጌታ ሆይ ዛሬም ዘወትርም የተመሰገንክ ሁን፤ አሁን ስለ አንተ ርግጠኛ ሆንኩ፤ እነሆ አሁን አንቺ በመልካም እጆች ውስጥ ነሽ፤ መፍቀሬ ሰብእ በሆነው በእግዚአብሔር እጆች ውስጥ ነሽ» አለኝ።

ወንበሬ ላይ ተቀመጥኩና ሲጋራ ላጤስ መለኮሻውን አወጣሁ። የለየልኝ አጫሽ ነኝ። ታድያ ልክ ልለኩሰው ስል ሞፈድ በዘዴ «አሁንማ ይህ አያስፈልግሽም» አለኝ። እኔም በባኮ ያለውን ሲጋራ የቆሻሻው ቅርጫት ውስጥ ከተትኩት። ደግሜ እንደማልመለስበትም ቃል ገባሁለት። እነሆ እግዚአብሔር ረዳኝና ከዚያ በኋላ አልተመለስኩበትም።

ቀናት ቀናትን እየተኩ አለፉ። በውስጤ ደስታ ነግሦአል። ጌታዬ በፍቅር፣ በሐሴት እና በበረከት ከብቦኛል። እነዚህ ሁሉ ደግሞ ከማስበው እና ከሚገባኝ በላይ ናቸው።

ጌታ ሆይ እወድሃለሁ፤ ነገር ግን ካንተ ርቄ ነው ያለሁት። መንገዱን ገና በሚገባ አላወቅኩትም። በአንተ እና በእኔ መካከል ያለው የመከለያ ግንብም ገና አልፈረሰም።

ከፍተኛ የሆነ የደም ግፊት ነበረብኝ። አንዳንድ ጊዜ 200/100 ይደርሳል። አንድ ቀን ታድያ አልጋዬ ላይ ተኝቼ በልቤ ከእግዚአብሔር ጋር እነጋገር ነበር። ያኔ «እባክህ ከዚህ ሕመም ገላግለኝ» እያልኩ እለምነው ነበር። ወዲያውኑ አንድ ሰው ፊቴን የነካኝ ያህል ተሰማኝ፤ እኔም ፈጠን ብዬ መብራቱን አበራሁት። ነገር ግን ማንም በአካባቢው አልነበረም። እና በዚያ ሌሊት ገጥሞኝ የማያውቅ ድብን ያለ እንቅልፍ ወሰደኝ አደረ።

*ሕይወቴን በሰላም እና በእርጋታ የሚሞላ እግዚአብሔር*
*የተመሰገነ ይሁን።*

አንድ ቀን ደግሞ በራእይ ራሴን ሥጋጃ በተነጠፈበት ክፍል ውስጥ አገኘሁት። ከፊት ለፊቴ ውኃ የተሞላ ሰፊ ኩሬ ይታየኛል። የሚደንቀው የሌሊት ልብሴን ለብሼ ባዶ እግሬን ነበርኩ። «ይህ ቤተ ክርስቲያን መሆን አለበት» ብዬ አሰብኩ። ግን ደግሞ እንዴት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደዚህ ለብሼ ልገኝ እችላለሁ? ከዚህ ጊዜ በፊት ይህንን የመሰለ ኩሬ አይቼ አላውቅም። በዚህ መካከል አንድ ሰው የክፍሉን በር ከፈተው። እኔም እርሱን ማየት ስለፈራሁ ልብሴን ሰብሰብ አድርጌ መሬት መሬት አይ ነበር። ያ ሰው እኔን ፊት ለፊት እያየ ሰውነቴን በዘይት መቅባት ጀመረ። እኔም በጸጥታ ቆሜ





ያለሁ። አንዳች ተቃውሞ አልነበረኝም። ከዚያ ክፍል ወጥቶ ሲሄድ ተከተልኩትና ከአሥር እስከ አሥራ ሁለት የሚደርሱ ካህናት ተሰልፈው መዝሙር የሚዘምሩበት ቦታ አደረሰኝ። በእጃቸው ሻማ አብርተው ልረዳው ያልቻልኩትን ልዩ ዝማሬ ይዘምራሉ። ወደፊት ስሄድ ልክ በሰልፍ እንዳሉ ሆነው በረዥም ጎዳና ተከተሉኝ። መንገዱ ሲያልቅ ሁለት ደረጃዎችን ወጣንና ጠረጴዛ በሚመስል ነገር ዙርያ መዞር ጀመርን። ከዚያም እንደገና በመጣንበት መንገድ ተመለስንና ከቤተ ክርስቲያን ወጣሁ።

ስነቃ ያየኋቸውን ነገሮች ማስታወስ ጀመርኩ። ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላወቅኩም። እንደዚያ ዓይነት ልብስ ለብሼ ቤተ ክርስቲያን ስገባ የመጀመርያዬ ነው። የእነዚያ ያየኋቸው ነገሮች፣ የዚያስ የተቀባሁት ነገር ትርጉሙ ምንድን ነው? ከነቃሁ በኋላ ለብዙ ጊዜ ቅባቱ በአካሌ ላይ ያለ ያህል ይሰማኛል። ሳሚያን ለመጠየቅ እየበረርኩ ወደ ት/ቤት ሄድኩ። ያየሁትን ስተርክላት አቋረጠችኝና በአድናቆት እያየችኝ በደስታ ተውጣ «ወደ ኩሬው ውስጥ ገባሽ» ስትል ጠየቀችኝ። እኔም «አልገባሁም፤ ግን ለምን?» ስል መለስኩላት። «ይህ የመጠመቂያ ገንዳ ነው፤ እዚያ የምትገቢው ምሥጢረ ጥምቀትን ለመፈጸም ብቻ ነው» አለችኝ ሳሚያ። ቀጥላም ምሥጢረ ጥምቀት ምን እንደሆነ ልታብራራልኝ ጀመረች።

*ጌታ ሆይ በአንተ ዘንድ እንዴት ያለ ቦታ አገኘሁኝ፤*
*መንገዴንም አሳየኸኝ።*

ሳሚያ ከካህኑ ጋር በጉዳዩ ላይ ተነጋግራ ቀጠሮ ልትይዝልኝ ቃል ገባች። እንደተለመደው በቢሮዬ የሚጠብቀኝን ሞፈድን ለማግኘት አመራሁ። አየት አደረገኝና ፈገግ ብሎ በዚያ ረጋ ባለው ድምፁ «እስቲ እንዲህ ደስተኛ ለምን እንደ ሆንሽ ፈጠን ብለሽ ንገሪኝ» አለኝ። አጠገቡ ተቀመጥኩና የሆነውን ሁሉ ነገር ዘረዘርኩለት። እርሱም እግዚአብሔርን ያመሰግን ጀምር። ስጨርስ ፊቱን ቀና አድርጎ እኔን እኔን እያየ «ጌታዬ ሆይ የተመሰገንክ ሁን። ትናንትና፣ ዛሬም፣ ለዘለዓለምም እንደማትለወጥ ዐውቃለሁ፤ ለዓለም ወለዓለም ወለትውልደ ትውልድ ክብር እና ምስጋና ላንተ ይገባል። እግዚአብሔር የስሙ ምስክር ትሆኝ ዘንድ መርጦሻል። እንደሚጠብቅሽ፣ እንደ ሚያድንሽ፣ በአንቺ የጀመረውን ሥራውን እንደሚፈጽም ከሃሌ ኩሉ በሆነው ጌታ አምናለሁ። ለዘለዓለም አመስግኘው፤ አክብሪውም» አለኝ።

እንደ ተለመደው የደም ግፊት ምርመራዬን ለማድረግ በቀጠሮዬ ቀን ወደ ሐኪሜ ዘንድ ሄድኩ። ሐኪሜም አንዳች የሕመም

ስሜት ይሰማኝ እንደሆነ ለማወቅ ፈለገ። ከዚህ በፊት በነገረኝ መሠረት አልጋ ላይ ረዥም ጊዜ ማሳለፍ አለማሳለፌን ጠየቀኝ። እኔም «ፈጽሞ» ስል መለስኩለት። እርሱም እየተገረመ «መሞት ትፈልጊያለሽ?» አለኝ። «ኧረ በጭራሽ አልፈልግም» አልኩት። ቀጠል አድርጌም «ለምን መጀመርያ ምርመራውን አናደርገውም» አልኩት። ከመረመረኝ በኋላ የደም ብዛቴን የሚያመለክት አንዳች ምልክት አጣ። ምናልባት መሣርያው ተበላሽቶ ይሆናል አለና ሌላ መሣርያ ቀይሮ አመጣ። ነገር ግን ውጤቱ ተመሳሳይ ነበር። በአግራሞት ፍጥጥ ብሎ አየኝ። አዎ ሁሉን ቻይ የሆነው እግዚአብሔር ዳስሶ ፈውሶኛል፤ ሌላ ምንም አያስፈልገኝም።

በዚህ ሁኔታ ጥቂት ቀናት አለፉ። በመድኃኔዓለም ጥበቃ ሥር በመሆኔ ደስ ብሎኛል። ከእርሱ ጋር መሆን እንዴት ያጽናናል መሰላችሁ። ይህ ሁሉ ቢሆንም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እና ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የበለጠ ለማወቅ አሁንም እሻለሁ። አንድ ቀን ሳሚያ ቢሮዬ መጥታ ካህኑ ሊያገኙኝ እንደሚፈልጉ ነገረችኝ። ገረመኝና «ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው?» ስል ጠየቅኋት። «አይደለም እኛ ቤት ውስጥ ነው፤ አባቴ ስለታመመ ለእርሱ ለመጸለይ ካህኑ እኛ ቤት ይመጣሉ። አንቺም እኛን ለማየት ትመጭና በዚያው ከካህኑ ጋር ትገናኛላችሁ» አለችኝ። እኔም ቀኑ መቼ እንደሆነ ጠየቅኋት። «ነገ እሑድ ከቅዳሴ በኋላ ነው» ስትለኝ ደስ አለኝ።

ነገ ካህኑን አገኛቸዋለሁ ማለት ነው። ከዚያ ቀን በፊት በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች ከካህናት ጋር ተገናኝተናል። የነገው ግን ፈጽሞ የተለየ ነው። በእግዚአብሔር ቸርነት ዛሬ የተለየሁ ሰው ሆኛለሁና። በዚያ ምሽት በጊዜ ነበር የተኛሁት። በሕልሜ አንድ ሰው በበረሃ ውስጥ የሚገኝ አንድ ገዳም እንድ ጎበኝ ሲጋብዘኝ አየሁ። በዚያ ገዳም ዙርያ ከአሸዋ በስተቀር ምንም ነገር አይታየኝም ነበር። ገዳሙ ትልቅ በር አለው፤ በበሩ ላይ ሦስት ቅስቶች ይታያሉ። መካከለኛው ቅስት ከሁሉም ሰፋ ያለ ነው። በአናቱም ላይ መስቀል ተሰቅሎበታል።

ወደ በሩ ስጠጋ ጥቁር ቀሚስ የለበሰ ሰው በሩን ከፈተው። ሰውየው በራሱ ላይ መስቀሎች የተጠለፉበት መሸፈኛ አድርጓል። የግቢውን በር ሲሻገሩ ቀጭን እና ዛፎች በመሥመር የተተከሉበት መንገድ አለ። በመንገዱ መጨረሻ አንድ አዲስ ቤተ ክርስቲያን፣ ከዚያ ጀርባም ዕድሜ የጠገበ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ይገኛል። እኛም ወደ ጥንቱ ቤተ ክርስቲያን ገባን። ዐጽማቸው በክብር ያረፉ ቅዱሳን በዕንቅልፍ ላይ ያሉ መስለው ይታያሉ። ጠዋት ስነቃ ደስ በሚል ስሜት ውስጥ ነበርኩ። ካህኑ ያንን ገዳም ሳያውቁት አይቀሩም ብዬ





አሰብኩ። ምናልባትም ያየሁትን በዝርዝር ስነግራቸው ከእኔ ጋር የመነጋገርያ ነገር ያገኙ ይሆናል ብዬ አሰብኩ።

ካህኑ ከሚመጡበት ሰዓት ትንሽ ቀደም ብለን ከሳሚያ ጋር ወደ እነርሱ ቤት ሄድን። ካህኑ እንደመጡ ሰላምታ ከሰጡኋቸው በኋላ እጃቸውን ተሳለምኩት። ከዚያም ፊት ለፊታቸው ተቀምጬ ያየኋቸውን ነገሮች አንድ በአንድ መተረክ ቀጠልኩ። ኢየሱስ ክርስቶስን እንዴት እንዳየሁት፣ ምን እንዳለኝ ስተርክላቸው ጥልቅ የሆነ ስሜት ውስጥ ነበርኩ። አነጋገሩን፣ ፍቅሩን፣ ርኅራኄውን፣ ተረክሁላቸው። ነገሩን ሁሉ አሁን የማየው ያህል ነበር የሚሰማኝ። ካህኑ በጥሞና ያዳምጡኝ ነበር። በመጨረሻ ትናንት ያየሁትን ገዳም ዘርዝሬ ስጨርስ «ይህ ገለጻ የኤል- ባራሞስ ገዳምን ይመስላል፤ ይህን ገዳም የምትጎበኝበትን መንገድ አመቻቻለሁ» አሉኝ።

«አብረሽኝ ወደዚያ ገዳም ለመሄድ ፈቃደኛ ነሽ?» ሲሉ ጠየቁኝ። እኔም በጉጉት «እንዴ ምን ጥርጥር አለው» ብዬ መለስኩላቸው። እርሳቸውም «እኔ በቀጣዩ ማክሰኞ ወደ ገዳሙ ሄጄ ነሙስ እመለሳለሁ፤ በሉ ማክሰኞ ጠዋት ሁለታችሁም አሥራ አንድ ሰዓት እኔ ቤት አጠገብ ጠብቁኝና አብረን እንሄዳለን» አሉ። ያኔ ያንን አፓርትመንቴን አስታወስኩት። ከካህኑ ቤት አምስት ደቂቃ ያህል ቢያስኬድ ነው። እግዚአብሔር በዚያ ቦታ ያንን አፓርትመንት የሰጠኝ ለዚህ ነው ማለት ነው ብዬ አሰብኩ።

ካህኑ ምሥጢረ ሥጋዌን እና አምላክ በሥጋ መገለጥን ለምን እንደወደደ አስረዱኝ። እኔም «አባት ሆይ እነዚህን ነገሮች በዝርዝር ለማስረዳት አይድከሙ፤ እኔ ራሴ በዓይኔ አይቻቸዋለሁና፤ እኔ ራሴ ሰውም አምላክም ሆኖ አይቼዋለሁና፤ አንደበት ሊገልጠው የማይቻለውን ዓይኔ አይታለች፤ ምን አለ ሁሉም ሰው እግዚአብሔር ምን ያህል እንደሚወደው ማወቅ ቢችል። ያየሁትን በትክክል ሊገልጡ የሚችሉ ቃላት አንድ ቀን እንደማገኝ ተስፋ አደርጋለሁ» አልኳቸው።

የነበረኝ ቆይታ ከቀኑ ስምንት ሰዓት እስከ ምሽቱ አንድ ሰዓት ለአምስት ሰዓታት ነበር። ሰዓቱ እንዴት ይሮጣል እባካችሁ። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ስለነበር ሁላችንም ደስ ብሎን ነበር የተለያየነው። ወደ ቤቴ ስመለስ መንገድ ላይ «ከቤተሰቦቼ ተለይቼ ለሦስት ቀናት እንዴት ነው ልቆይ የምችለው? ደግሞስ ከልጆቼ አንዱ ቢጠይቀኝ ምን ብዬ እመልሳለሁ?» የሚሉትን ሃሳቦች እያወጣሁና እያወረድኩ ነበር። ማክሰኞ ጠዋት ከካህኑ ጋር ወደ ገዳሙ ለመሄድ ሰኞ ቀን አዲሱ አፓርትመንቴ መግባት አለብኝ። ሰኞ ማታ ደግሞ ለጉዞው

መዘጋጀት አለብኝ። ግን እንዴት አድርጌ ከልጆቼ እለያለሁ። ወንዱ ልጄ ከጥቂት ቀናት በኋላ በኤይን ሻምስ ዩኒቨርሲቲ ከኢንጂነሪንግ ፋኩልቲ የመመረቂያ ፈተና ይወስዳል። እስከዛሬ በነበረው የትምህርት ጉዞው ከእርሱ ሳልለይ አብሬው ነበርኩ፤ ውስጤ ተፈተነ። ለመሆኑ ከልጆቼ የመለየቱን ነገር ልቋቋመው እችላለሁ? ወንዱ ልጄ የመጀመርያ ልጄ ሲሆን አሁን 23 ዓመቱ ነው። ሁለተኛዋ ልጄ 22፣ የመጨረሻዋም 20 ዓመቷ ነው። በሕይወቴ ስለያቸው ይህ የመጀመሪያዬ ነው። ምንም እንኳን አባታቸው እና እኔ በሕግ የተፋታነው በ1982 ዓም ቢሆንም ለልጆቻችን ስንል ግን በአንድ ጣራ ሥር ነበር የምንኖረው። በዚያ ሁኔታ ያልተወኳቸውን ልጆቼን አሁን እንዴት ልተዋቸው? ደግሞስ ዝም ብለው ይለቁኛል? ጌታ ሆይ እባክህን እርዳኝ፤

ለልጆቼ ነግሬያቸው ነገ ወደ አዲሱ አፓርታማዬ እገባለሁ ብዬ ወሰንኩ።

ቤት ገብቼ ትንሽ እንደቆየሁ አባታቸው ቴሌቪዥን ሲመለከት አጋጣሚውን ተጠቀምኩና ድምፄን ቀንሼ ጉዳዩን ለልጆቼ አነሣሁባቸው። «በነገራችን ላይ ነገ ወደ አዲሱ አፓርትመንት እዛወራለሁ» አልኳቸውና ምላሻቸውን መጠባበቅ ጀመርኩ። የሚገርመው ግን ሁሉም ዝም አሉ። በጸጥታ እኔን እኔን ያዩኛል። ፈጠን አልኩና «ይህንን የማደርገው ለእናንተ ስለማላስብ አይደለም፤» አልኳቸው። ከዚያም ወደ መኝታ ክፍሌ ገብቼ ዕቃዎቼን ማዘጋጀት ጀመርኩ። ይህ ሁኔታዬም በጉዳዩ ላይ ክርክር እንዳይከፈትና ለሚያነሷቸው ጥያቄዎች ምላሽ በመስጠት እንዳልደክም አደረገኝ። ደስ አለኝና አምላኬን አመሰገንኩት። በነጋታው ገና በማለዳ ወደ ት/ቤት ሄድኩ። ከዚያም ማታውኑ የት/ቤቱ ሁለት የጉልበት ሠራተኞች አንዲት የዕቃ መጫኛ መኪና አምጥተው ዕቃዬን እንዲያጓጉዙልኝ አደረግኩ።

መቼም ድንቅ ነው። ወደ አዲሱ ጎጆዋ የምትሄድ ሙሽራ ነውኮ የመሰልኩት። እንደ እውነቱ ከሆነኮ እኔም አዲስ ሙሽራ ነኝ፤ ከምወደው ጌታ ጋር የምኖርበት ቦታ ያስፈልገኛል። ፍቅሩ ከማናቸውም ፍቅር፣ ከማንኛውም ዓይነት ስሜት በላይ ነው። ነገሮች ሁሉ እንዳሰብኳቸው ተከናወኑልኝ። አምላክ ሆይ ይህ የአንተ ሥራ መሆኑን አምናለሁ። ምንም እንኳን አፓርትመንቱ ጠባብ ቢሆንም ለእኔ ግን ከቤተ መንግሥት በላይ ሰፊ ሆኖ ነበር የተሰማኝ።

ምን ያህል እንደምትወደን ባወቅን ቁጥር አንተን ለማግኘት ያለን ናፍቆት እንደበት ሊገልጠው ከሚችለው በላይ ይጨምራል። አንተ





አስቀድመህ ወድደህናልና እኛም እንወድሃለን። ካንተ ሌላ የምፈልገው ነገር የለም። ልቤ ያንተ ነው፤ አመሰግንሃለሁ፤ አከብርህማለሁ፡ ለአንተም እዘምርልሃለሁ። አንተን ወደማወቅ መርተህኛልና፤ ረድተህኝማልና።

ሌሊቱን አፓርትመንቱን በማጽዳት እና ቤቱን በማስተካከል አሳለፍኩት። ሊነጋ ሲያቅላላ ደግሞ ወደ ቀጠሮዬ ሥፍራ አመራሁ። ካህኑ እየጠበቁኝ ነበር። ሦስታችንም ተያይዘን በካይሮ/እስክንድርያ በረሃማ መንገድ ላይ መንዳት ጀመርን። ልክ ገዳሙ ጋር ስንደርስ በራእይ ያየሁትን ነገር አስታወሰኝ። የሚገርም እኮ ነው፤ ሁሉም ነገር ልክ በራእይ እንዳየሁት ነው።

የብረቱ በር፣ ዛፎቹ፣ በአጠገቡ የሚገኘው ረዥሙ መንገድ፣ አዲሱ እና ጥንታዊው ቤተ ክርስቲያን፣ ሁሉም በራእይ እንዳየሁት ሆኖ አገኘሁት። በጥንታዊው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቅዳሴ አስቀደስን፤ በሕይወቴ ለመጀመርያ ጊዜ ያስቀደስኩት ቅዳሴ ነበረ። የሚነገረው ነገር ለእኔ አይገባኝም፤ ነገር ግን ነፍሴ እየተረዳችው ስትደሰት ይሰማኛል። የሚባለው ነገር ምን እንደ ሆነና ትርጉሙስ ምን ማለት እንደሆነ የማወቅ ጉጉት አደረብኝ። አንድ መነኩሴ መጡና አንድ መጽሐፍ ሰጡኝ። «ኤል-ኮላጊ»[12] ይላል። የውስጤን ፍላጎት ተረድቶ ሳልጠይቀው የሚያስፈልገኝን ስለ ሰጠኝ አምላኬን አመሰገንኩት(ማቴ.6÷7-8)።

በቅዳሴ ጊዜ ደስ የሚል ለየት ያለ የትኩስ ደም ሽታ ሸተተኝ። አፍንጫዬን ሸፍኜ ከየት የሚመጣ መዓዛ እንደሆነ ለማወቅ አንገቴን መለስ ቀለስ አደረግኩት። ካህኑ ሁኔታዬን ስላዩ «ምን ሆነሽ ነው?» ብለው ጠየቁኝ። ባለማቋረጥ የደም ሽታ እንደሚሸተኝና ከየት እንደ መጣ ማወቅ እንዳልቻልኩ ነገርኳቸው። ካህኑ በአፍንጫቸው አየሩን ሳቡት። ከዚያም ቀስ ብለው «ከቅዳሴ በኋላ እነግርሻለሁ» አሉኝ።

ቅዳሴው እንዳለቀ አስቀዳሾቹ ሁሉ ወደ ቀደሱት ካህን ሄደው የሆነ ነገር ከእጃቸው ሲቀበሉ አየሁ። የቀረሁት እኔ ብቻ ነበርኩ። አብረውኝ የመጡትን ካህን «ሊገባኝ አልቻለም፤ ምን እያደረጉ ነው? እኔም እንደነርሱ መቀበል እፈልጋለሁ» ስል ጠየቅኳቸው። ካህኑም «ሁሉንም ነገር በኋላ አስረዳሻለሁ፤ በቅዳሴ ጊዜ የጌታን ሞት እና ትንሣኤ እያሰብን እናስቀድሳለን፤ ከዚያም ሥጋውን እና ደሙን እንቀበላለን፤ ኅብስቱ ሥጋው፣ ወይኑም ደሙ ነው። እግዚአብሔር ስለሚወድሽ የስሜት ሕዋሶችሽን በመጠቀም ይህንን እውነታ እንድ

12. የቅዱስ ባስልዮስን እና የቅዱስ ጎርጎርዮስን ቅዳሴ፤ እንዲሁም መዝሙር እና ጸሎቶችን የያዘ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ነው።

ትረጅው አድርጓል» ሲሉ አስረዱኝ:: እኔም ቀጠል አድርጌ «ይህ የእርሱ የከበረ ሥጋው እና የተቀደሰ ደሙ መሆኑን እምናለሁ» አልኳቸው::

እግዚአብሔር ሆይ ክብር ምስጋና ላንተ ይሁን:: እኔም ከዚህ ቁርባን መሳተፍ ፈለግኩና ካህኑን «እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ማን ነው?» አልኳቸው:: እርሳቸውም «ቀላል ነገርኮ አይደለም፤ ለተወሰነ ጊዜ መቆየት አለብሽ» አሉኝ:: ርግጥ ነው በትዕግሥት መቆየት አለብኝ:: ካህኑ መጽሐፍ ቅዱስና የጸሎት መጽሐፍ ሰጡኝና እንዴት መጸለይ እንዳለብኝ አስተማሩኝ:: የቅዳሴ መጽሐፉን እና ካሴቱን በቃሌ ለመያዝ ብዬ ገዛሁት::

የገዳሙን ቆይታዬን ፈጽሜ ወደ ቤቴ ተመለስኩ:: በእኔ እና በቤተ ክርስቲያን መካከል ለያይቶን የነበረው ግንብ ሲፈራርስ ተሰማኝ:: የትምህርቱ ዓመት የሚያልቅበትም ጊዜ እየተዳረሰ ነበር:: ለእኔ ጥሩ አጋጣሚ ነው:: አሁን በየቀኑ ቤተ ክርስቲያን መሄድ እችላለሁ ማለት ነው:: ካህኑ ባስተማሩኝ መሠረትም በየጊዜው መጸለይና ሐዲስ ኪዳንን ማንበብ እችላለሁ ማለት ነው:: የወንጌላት አጻጻፍ ቀላል፣ያልተወሳሰበ እና ተከታታይ ነው:: ለመረዳትም ብዙም አላስቸገረኝም:: ከእኔ በስተቀር ያስቀደሱት ሁሉ ከሥጋው በሉ፣ ከደሙም ጠጡ፤ እኔ ብቻ ተነጥዬ ቀረሁ:: ጌታ ሆይ እባክህን እንድ ጠመቅ እርዳኝ::

ልጆቼን በየጊዜው እየሄድኩ እጠይቃቸዋለሁ:: ወንዱ ልጄን የፈተናው ሁኔታ እንዴት እንደነበር ጠየቅኩት:: እርሱ ግን በፈተናው እንዳልተደሰተ እና ውጤቱንም በበጎ እንደማይጠብቀው ጆሮዬን ጭው ያደረገ መርዶ አረዳኝ:: ኀዘን እና ፀፀት በውስጤ መላ:: ከቤተሰቤ ከመለየቴ በፊት ልጄ ፈተናውን እስኪጨርስ መጠበቅ ነበረብኝ ብዬ ተፀፀትኩ::

ወደ ካህኑ ሄድኩና የሆነውን ነገር ነገርኳቸው:: እንድረጋጋ ከመከሩኝ በኋላ ከልጃቸው እና ከልጃቸው ጓደኛ ጋር በድጋሚ ወደዚያ ገዳም እንድንሄድ ጋበዙኝ:: እንደተባለውም በተቀጣጠርንበት ቀን እና ሰዓት ተገናኘንና ወደ ገዳሙ አመራን:: ካህኑ ፓትርያርክ ቄርሎስ[13] ይጸልዩበት በነበረው ዋሻ ውስጥ የሠርክ ጸሎት እንድናደርግ ወሰዱን:: ዋሻው ጠባብ ነው:: አስጎብኚው መነኩሴ ከውጭ ሆነው ሲጠብቁኝ እኔ ወደ ዋሻው ውስጥ ዘለቅኩ:: በዚያ ቦታ ቆሜ እግዚአብሔር ልጄን በፈተናው እንዲረዳው በጸሎት ጠየቅኩት:: በሥዕሉ

13. ከ 1959 -1971 ድረስ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን 116ኛ ፓትርያርክ የነበሩ::





ላይ ያለውን የፓትርያርክ ቄርሎስን ዓይን በተመለከትኩ ቁጥር ሲንቀሳቀሱ ይታዩኛል:: እኔም ምናልባት ዓይኖቼ በዕንባ ስለተሞሉ ይሆናል ብዬ አሰብኩ::

እዚያ ቦታ እያለሁ ፀሐይዋ ዞራ በጀርባችን በኩል መጣች:: ቀኑ አልጨለመም፤ ከኋላዬ የሆነ ሰው የቆመ መሰለኝ:: ያ ሰው እጁን በሥስታችን ላይ ዘርግቷል:: ከዚያም የፀሐይዋን ብርሃን ከለለው:: አንዳች ነገር ውስጤን ዘልቆ ገብቶ አጥንቴን ስንጥቅ ሲያደርገው ይሰማኛል:: ለካህኑ ልጅ «እንሂድ» ብዬ አንሾካሾክሁላት:: ዋሻውን ለቅቀን ስንወጣ ዙርያ ገባዬን አማተርኩት:: ነገር ግን ከሦስታችን ውጭ ማንም አልነበረም::

እንግዳ ነገር ነው የገጠመኝ:: ከእኛ ጋር አብረውን የነበሩት አራተኛ ሰው ፓትርያርክ ቄርሎስ መሆናቸውን ተረዳሁ:: በእርሳቸው አድሮ እግዚአብሔር ብዙ ተአምራት ማድረጉን ሰምቻለሁ:: በፍርሃት ስለተዋጥኩ ወደ ቤት መመለስ እንችል እንደሆነ ካህኑን ጠየቅኳቸው:: በነጋታው ጠዋት ወደ ቤታችን ተመለስን:: አቡነ ቄርሎስ በእጃቸው ያቀፉኝ ያህል እየተሰማኝ ነበር ቤቴ የገባሁት:: እንዴት ያለ ኃይል መሰላችሁ:: ያኔ የተሰማኝ ስሜት ዛሬም እንኳን ይሰማኛል::

ዕንቅልፍ እስኪወስደኝ ድረስ ያንን ውሎየን በልቤ እያሰላሰልኩ ነበር:: ወዲያውም በት/ቤቱ በሚገኘው ቢሮዬ ውስጥ ራሴን በራእይ አየሁት:: ወንዱ ልጄ ሐፃን መስሎ ወደ እኔ እየመጣ ነበር:: ፊቱ በደስታ ተሞልቷል:: ወደ እኔ ሮጦ መጣና «እማዬ ተጠመቅኩ» አለኝ:: እኔም ዓይኔን የደስታ ዕንባ ሞልቶት «እንዴት ተደርጎ? በጭራሽ የሚሆን ነገር አይደለም» አልኩት:: እርሱም እየደጋገመ «እማዬ ይህ የጸሎትሽ ፍሬ ነው» ይለኝ ነበር:: እኔም አለቅስ ነበር:: እርሱም እየደጋገመ ያንኑ ይነግረኝ ነበር:: ስነቃ በእውን የሆነ ይመስል በዕንባ ተሞልቼ ነበር:: ምናልባት ሁኔታውን አብዝቼ ከመፈለጌ የተነሣ የመጣ የቀኑ ጉዞዬ ውጤት ነው ብዬ ነገሩን ቸል አልኩት::

ካህኑን ያጠምቁኝ ዘንደ እየደጋገምኩ እጎተጉታቸው ነበር:: እርሳቸው ግን «ታገሺ» የሚለው መልሳቸው አይለወጥም:: አንድ ቀን በሲና በረሃ የሚገኘውን የቅድስት ካትሪናን ገዳም ለመጎብኘት ካህኑ ጋብዘውኝ ነበር:: እንዳጋጣሚ ሆኖ የተጓዝኩት ጽኑ ሃይማኖተኛ እና ኢየሱስ ክርስቶስን በደንብ ከምታውቅ እኅት ጋር ነበር:: በሙሴ ተራራ ላይ መልካም ጊዜ አሳለፍኩ:: እግዚአብሔር በዕፀ ጳጦስ ላይ ይነድድ በነበረው እሳት በኩል ለሙሴ የተገለጠበትን ቦታ አየሁት:: በዚያ ዐለት ላይ ተቀምጠን የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ እንነጋገር ነበር:: የመጠመቁ ሃሳብ በልቡናዬ እየተደጋገመ ይመጣብኛል:: ማን

ይሆን ይህንን ታላቅ ምስጢር ለእኔ የሚፈጽምልኝ? እያልኩ ራሴን እጠይቅ ነበር። ያን ጊዜ «ቄስ ቡትሮስ ናቸው» የሚል ድምፅ ሰማሁ። እኔም ደንገጥ ብዬ አጠገቤ የነበረችውን እኅት «ቄስ ቡትሮስ ማናቸው?» ብዬ ጠየቅኳት።

በአውቶቡሱ እየተጓዝን እያለ መንገድ ላይ መኪናው ቆመ። ከዚያም አጠገቤ የነበረችው እኅት ከአውቶቡሱ ለወረዱት አንድ አባት ሮጣ ሰላምታ ሰጠቻቸው። እኔም እርሷን ተከትዬ ሰላም አልኳቸው። «ከዚያም ማናቸው?» ስል ጠየቅኳት። እርሷም «አታውቂያቸውም እንዴ፤ ሰው ሁሉ እኮ ያውቃቸዋል» አለችኝ። በኋላም ስለ እርሳቸው እና እግዚአብሔር በእርሳቸው በኩል ስለሚሠራው ድንቅ ሥራ በዝርዝር ነገረችኝ። እኚህ አባት ዘወትር ቅዳሜ የሚያካሂዱት ጉባኤ አላቸው። የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ቤታቸው ለቤቴ ቅርብ ነበር።

ከቅድስት ካትሪና ገዳም ስመለስ ለጥምቀት እና ለቅዱስ ቁርባን እንደምበቃ ባለሙሉ ተስፋ ሆኜ ነበር። ጥምቀትን በተመለከተ የካህኑን ሃሳብ አሁንም ለማወቅ ፈለግኩ። እናም እርሳቸውን ለማግኘት ወጣሁ። መንገድ ላይ ስለ እምነቴ አወጣና አወርድ ነበር። «አሁን በዚህ ሁኔታ ብሞት እግዚአብሔር ክርስቲያን ናት ብሎ ይቀበለኛል» እያልኩ ራሴን እጠይቅ ነበር። ከዚያም «ጌታ ሆይ ለመጠመቅ ያለኝን ጉጉት ታውቃለህ፤ እስካሁን ግን ምንም አላደረግኩም፤ አሁን የምሥጢረ ጥምቀትን ጥቅም ተረድቻለሁ፤ በሙሉ ልቤ እንደምፈልገውም ታውቃለህ፤ እባክህን እንድፈጽመው እርዳኝ» እያልኩ እጸልይ ነበር።

መንገድ ላይ እየተጓዝኩ እያለ በአንድ እጇ በትር ፣በሌላ እጇ ደግሞ ቲማቲም የተሞላ ቦርሳ የያዘች በዕድሜ ገፋ ያለች አንዲት ሴት አየሁ። የቲማቲሞቹ ትልቅነታቸው እና ቀላታቸው ሳበኝ። ያን ጊዜ ያች ሴትዮ አስቆመችኝና " ቅዳሴው አበቃ እንዴ" ስትል ጠየቀችኝ። "ቅዳሴ? የምን ቅዳሴ? " ስል መልሼ ጠየቅኳት። እርሷም "በቅድስት ድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን የነበረው ቅዳሴ" ስትል መለሰችልኝ። "አላወቅኩም" አልኳት። ሴትዮዋም "እዚያ አልነበርሽም እንዴ?" ስትል ተገርማ ጠየቀችኝ። "አዎን አልነበርኩም! ብኖርማ ኖሮ መቼ እንዲህ ትይኝ ነበር" አልኳት። ቀጠል አድርጋም "ክርስቲያን አይደለሽም እንዴ? " ስትል ጠየቀችኝ። እኔም "ታድያ በራሴ





ላይ ያለው ይህ መሸፈኛ[14] ምን ይመስልሻል " አልኳት። እርሷ ግን "ቢሆንም ክርስቲያን ነሺ" አለችኝ።

እኔ ክርስቲያን መሆን አለመሆኔን ለመመርመር የተላከች ሰላይ ትሆናለች ብዬ አሰብኩና "ክርስቲያን ናት ብሎ ማን ነው የነገረሽ?" ብዬ ጠየቅኳት። እርሷም ወደ ሰማይ እያመለከተች "እርሱ" አለችኝ። ቀጠል አድርጋም "እኔም እንዳንቺ ክርስቲያን ነኝ" አለችኝ። ከዚያም እጇን ወጣ አድርጋ የተነቀሰችውን መስቀል[15] አሳየችኝ።

እንድታጽናናኝ የተላከች መሆንዋን ሳረጋግጥ እፎይታ ተሰማኝ። «ጌታ ሆይ የተመሰገንክ ሁን» አልኩና መራመድ ስጀምር ያች ሴትዮ ስታለቅስ ሰማኋት። እኔም መለስ ብዬ ለምን እንደምታለቅስ ጠየቅኳት። «ጊዜው ክፉ፣ ሕይወትም አስቸጋሪ ነው፤ የሰዎች ልቦችም ጨካኞች ሆነዋል» ስትል መለሰችልኝ። ሁለት ሳንቲሞች ሰጠኋትና ጉዞዬን ቀጠልኩ። ነገር ግን አንድ ሁለት እርምጃ ከተራመድኩ በኋላ ይህንን የመሰለ መልካም ዜና ለነገረችኝ ሴት ተገቢ ነገር አላደረግኩም ብዬ በመፀፀት በዛ ያለ ገንዘብ ለመስጠት ዘወር ስል በአካባቢው አጣኋት። ሮጥ ብዬ መንገዱን ይገፔ ልትሄድበት በምትችለው አቅጣጫ ፈለግኳት። ላገኛት ግን አልቻልኩም። ያን ጊዜ ታጽናናኝ ዘንድ ከእግዚአብሔር የተላከች መሆንዋን አመንኩ። እግዚአብሔርም ሊገባኝ በሚችል መንገድ ጥያቄዬን መለሰልኝ።

ወደ ካህኑ ቤት መንገዴን ተያያዝኩት። ተጠምቄ አማናዊቱ ክርስቲያን መሆን እንዳለብኝ ራሴን አሳመንኩት። ቤት ገብቼ ከካህኑ ፊት ተቀምጬ «አያጠምቁኝም ወይ?» ስለ ጠየቅኳቸው። «ይህንን ጉዳይ ደግመሽ አትጠይቂኝ፣ ከመጠመቅሽ በፊትኮ ቢያንስ አንድ ዓመት መቆየት አለብሽ» ሲሉ መለሱልኝ። እኔም በልቤ ለመሆኑ እኚህ ካህን በቀጣዩ አንድ ዓመት በሕይወት ልቆይ እንደምችል ዋስትና ሊሰጡኝ ይችላሉ? ሌላው ቀርቶ ለአንዲት ሰዓት እንኳን ዋስትና መስጠት ይቻላቸዋልን? ፈጽሞ! ስለዚህም ይህንን ምሥጢር ልሳተፍ የምችልበትን ሌላ መንገድ መፈለግ አለብኝ ብዬ አሰብኩ።

14. መሸፈኛው ሙስሊም ሴቶች የሚለብሱት መሸፈኛ ነው

15. ግብጻውያን ክርስቲያኖች እኛ ማተብ እንደምናሥረው እነርሱ ደግሞ ክርስቲያንነታቸውን ለመግለጥ በቀኝ እጃቸው ላይ የመስቀል ምልክት ይነቀሳሉ /Otto F.A. Meinardus. Two thousand years Coptic Christianity 266/

የቄስ ቡትሮስን ጉባኤ አብረን ለመካፈል ከተቀጣጠርነው ጓደኛዬ ጋር ተገናኘንና ቀደም ብለን ገብተን ሦስተኛው መደዳ ላይ ተቀመጥን:: የዕለቱ የትምህርት ርእስ «*ንስሐ እና ወደ እግዚአብሔር መመለስ*» የሚል ነበር:: እጅግ ልብን የሚያረካ ትምህርት ነበር:: የመምህሩ ቃላት ዘልቀው ገብተው ልቡናን ይመረምራሉ:: እናም ከዚያን ቀን ጀምሮ የዘወትር የትምህርቱ ተከታታይ ለመሆን ወሰንኩ:: ከትምህርቱ በኋላ ቄስ ቡትሮስን አገኘናቸውና ጓደኛዬ «ከሌላ በረት የመጣች በግ ናት» ብላ ነገረቻቸው:: እርሳቸውም እኔን በመተዋወቃቸው እጅግ ደስ አላቸው:: እንዴት ባለ ሁኔታ ያዩኝ እንደ ነበር ዛሬ ድረስ ዓይኔ ላይ ይመጣብኛል:: ፈገግታቸውና ዓይን ዓይኔን እንዴት ያዩኝ እንደነበረ አሁንም አስታውሰዋለሁ::

በዚያ ቀን ጉባኤ ላይ በትምህርት ቤታችን የምትሠራ አንዲት ሴት ከቄስ ቡትሮስ ጸሐፊ ጋር ስትነጋገር አገኘኋት:: የሚገርመው ነገር ግን የቄስ ቡትሮስ ጸሐፊ ባለፉት አምስት ዓመታት በትምህርት ቤታችን ውስጥ ተማሪ ነበረች:: በተለይ በአንድ ወቅት ለእርሷ መጥፎ ሰው ሆኜባት ነበር:: ያኔ ታድያ እንደዚያ የሆንኩባት ሌላ ጥፋት ተገኝቶባት አልነበረም:: ክርስቲያን ስለሆነች ብቻ ነበር ችግሩ::

እኔን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስታየኝ በድንጋጤ ልትወድቅ ትንሽ ነበር የቀራት:: በዚህ መልኩ እንገናኛለን ብላ መቼም አስባ አታውቅም:: ይህ ከሃሌ ኩሉ የሆነው የእርሱ በጎ ፈቃድ ነው:: ከቄስ ቡትሮስ ጋር ለመገናኘት እንድችል ለቀጣዩ ረቡዕ ቀጠሮ ያዘችልኝ::

ረቡዕ ደረሰና ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄድኩ:: የቄስ ቡትሮስ ቢሮ በሕንፃው ላይ ሁለተኛ ፎቅ ነው:: ጓደኛዬ መንገዱን እየመራችኝ እኔ እየተከተልኳት ወደ ውስጥ ገባን:: ከዚያም በጥበበ ዕድ በተጌጠ ክፍል ፊት ለፊት ደረስን:: እኔም ያ ክፍል የመጠመቂያ ቤት መሆኑን ገመትኩ:: ፊት ለፊቱ ቆምኩና «እዚህ ክፍል ውስጥ የምገባው መቼ ይሆን?» ስል እግዚአብሔርን ጠየቅኩት:: ወዲያውኑ በሩ ተከፈተና አዲስ የተጠመቀች ሕፃን ልጅ የያዙ ሁለት ልጃገረዶች ወጡ::

ወደ ውስጥ ዓይኔን ላክ አደረግኩ:: የሚገርመው ያ ክፍል በራእይ ያየሁትን ክፍል ነበር የሚመስለው:: ተጽናናሁና «በእውነት የምጠመቅበት ክፍል ይህ ነው» ብዬ አመንኩ::

ምንጊዜም የምታጽናናኝ ጌታ ሆይ ምስጋና ይግባህ አልኩና ፈጠን ብዬ ጓደኛዬን በመከተል ወደ ቄስ ቡትሮስ ቢሮ ገባሁ:: ያየኋቸውን ራእዮች ሁሉ ለቄስ ቡትሮስ በዝርዝር ነገርኳቸው:: በእርጋታ እና በጥሞና ካዳመጡኝ በኋላ በሰኔ 1988 መጨረሻ በድጋሚ ወደ





እርሳቸው እንድመጣ ቀጠሮ ሰጡኝ::

ቄስ ቡትሮስን ከዚያ በኋላም ቢሆን በተደጋጋሚ አግኝቻቼዋለሁ:: ለሰው ትኩረት መስጠት፣ ትዕግሥት፣ አባታዊ ርኅራኄ፣ ከጠንካራ እና ወሳኝ ከሆነ ስብእና ጋር የተላበሱ አባት ናቸው:: በእርሳቸው ፊት እኔን እንደ ሕፃን ልጃቸው ነበር የሚያዩኝ:: እኔም ደግሞ ይህንን ነበር የምፈልገው::

የበጋው የዕረፍት ወራት ተጠናቀቀ:: መምህራኑ ሁሉ ለአዲሱ የትምህርት ዘመን ለመዘጋጀት ወደ ት/ቤቱ መጡ:: «ጌታ ሆይ ወደ ሥራዬ ስመለስ በቀድሞው ሁኔታዬ እንድመለስ ርዳኝ!» ስል ለመንኩት:: ግን እንዴት? አሁንኮ ፈጽሞ ተለውጫለሁ:: ያ አስደንጋጩ ድምፄ የታለ? በአስተዳደሩ ሕንፃ ውስጥ ድምፄን የሚሰማ ሁሉ አንድም ስጨቃጨቅ ያለበለዚያም ስስቅ ነበር የሚሰማኝ:: እንደ ተለከፈ ሰው ያለማቋረጥ ነበር የማጤሰው:: በዚያ ማንነቴ አፈርኩ:: በምቀባባው ቀለማ ቀለም፣ በኃይለኛው ሽቶዬ እንዲሁም አባካኝ በነበረው አለባበሴ አፈርኩበት::

አሁን ቀለል ያለውን እና ሰላማዊ የሆነውን አኗኗር መርጫለሁ:: ከዚህ በፊት እንደነበርኩት ዛሬ መሆን አልችልም:: በዙሪያዬ የሚገኝ ማንኛውም ሰው አኳኋኔን ተመልክቶ አንዳች ለውጥ እንዳለኝ መረዳት ይችላል:: ሰው ሁሉ ምን እንደዚያ እንዳደረገኝ ይገርመዋል:: አሁን ሰውን ሁሉ እወዳለሁ:: ያለ ልዩነት ሁሉንም ሰው አገለግላለሁ:: ጌታ ሆይ ያንተን ስም የተሸከሙትን ሁሉ ያቀፍኳቸው ያህል ይሰማኛል:: አሁን በፍቅርህ የተነሣ ልቤ ብሩኅ ሆኗል:: ባለፉት ዘመናት ያሳዘንኳቸውን ሁሉ አሁን ይቅርታ መጠየቅ አለብኝ:: እስካሁን ድረስ በእያንዳንዱ ጉዞዬ ጠብቀህኛል፤ አሁንም ርዳኝ እባክህ::

ሥራዬን ለመልቀቅ አሰብኩ:: እንደ ጥንቱ መሆን አይቻለኝምና:: አሁን ሙሉ በሙሉ ያንተ ሆኛለሁ:: በት/ቤቱ የሚገኙ ክርስቲያኖች ሁሉ መለወጤ ገብቷቸዋል:: ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አይተውኛልና:: እርግጥ ለእነርሱ ሊደንቃቸው ይችል ይሆናል:: ነገር ግን ለሰው የማይቻል ለእግዚአብሔር ይቻላል::

አንድ ቀን ወንዱ ልጄ ሊጠይቀኝ ቢሮዬ መጣ:: ፊቱ በደስታ በርቷል:: ልክ ሲያየኝ ወደ እኔ ሮጠና «እማዬ አለፍኩኝ፤ ፈተናውን አልፌ ዲግሪዬን አገኘሁ» እያለ ጮኸ:: የምሰማውን ማመን አቃተኝና «ፈተናው እንደከበደህና በደንብ እንዳልሠራህ ነበርኮ የነገርከኝ» አልኩት:: እርሱም እጄን አገላብጦ እየሳመ «ይህማ ያንቺ የጸሎትሽ ውጤት ነው» አለኝ:: ፊቱ ብሩኅ ሆኖ ያየሁበትን ራእይ አስታወ

ስኩና «ሰውን ሁሉ የምትወድድ ጌታ ሆይ ምስጋና ይግባህ» አልኩት::

ቀናት አልፈው ቀናት ተተኩ:: የቄስ ቡትሮስን ጉባኤ ባለማሰለስ እከታተላለሁ:: በእምነቴ በፍጥነት ማደጌን እያሰብኩ ለመጠመቅ ያለኝ ጉጉት ይበልጥ ጨመረ:: ቄስ ቡትሮስን ባገኘኋቸው ቁጥር «መጠመቅ እፈልጋለሁ» የሚለውን ጥያቄዬን ሳላቀርብ ቀርቼ አላውቅም:: እናም ረቡዕ ታኅሣሥ 13 ቀን 1988 ዓም ከቄስ ቡትሮስ ጋር ቀጠሮ ያዝን::

በቀጠሮው ቀን ቄስ ቡትሮስን ሳገኛቸው ረጋ ባለ ድምፅ «ለመጠመቅ ዝግጁ ነሽ?» ሲሉ ጠየቁኝ:: እኔም ተደንቄ «አዎና!» አልኳቸው:: ከዚያም ፈገግ ብለው «የዛሬ ሳምንት ረቡዕ ታኅሳስ 20 ቀን አጠምቅሻለሁ» አሉኝ:: ከዚያም ከመሳቢያቸው ውስጥ ቁራጭ ወረቀት አወጡና «ከሰይጣን የሚመጣ ከባድ ጦርነት ይጠብቅሻል፤ በጽንዐት ለማለፍ እንድትችይ መጽሐፍ ቅዱስን አንብቢ፣ በጸሎትም ትጊ» ብለው ጻፉና ሰጡኝ:: ወረቀቱን ስቀበላቸውም «ይህንን ነገር ከጓደኛሽ በስተቀር ለማንም አትንገሪ፤ እርሷ የክርስትና እናትሽ ትሆናለች» ሲሉኝ እኔ በፍጥነት ከክፍላቸው በመውጣት ላይ ነበርኩ::

ጸሎቴን በየጊዜው አላቋረጥኩም:: «መፍቀሬ ሰብእ የሆንከው ጌታ ሆይ፣ እባክህን የመልካም ጸጋ ጠላት መጠመቄን እንዲያስተጓጉልብኝ አትፍቀድለት፤ ይህ ነገር የስጦታህ መጨረሻ ቢሆን እንኳን ይህንን ጸጋ ግን አትንፈገኝ:: ይህ ብቻውን ለእኔ በቂዬ ነው:: በጥምቀት ካንተ ጋር ሞቼ ከአንተ ጋር እነሣለሁና:: በእያንዳንዱ ርምጃዬ ሁሉ ካንተ ጋር ለመሆን ቃል እገባልሃለሁ:: ነፍሴንም ላንተ ለማስገዛት እነሆ ቃል እገባለሁ:: ምንጊዜም ካንተ ጋር እሆናለሁ::

ታኅሣሥ 20 ቀን 1988 ዓም እስኪደርስ ድረስ ቀናቱ ከወትሯቸው በባሰ ቀርፈፍ እያሉ ነበር የሚመሹና የሚነጉት:: በዚያ ዕለት ከቤቴ የወጣሁት ከጠዋቱ 12 ሰዓት ላይ ነበር:: ከፍጥነቴ የተነሣ ወደ ቤተ ክርስቲያን ስሄድ እየተራመድኩ ሳይሆን እየበረርኩ ነበር የሚመስለው:: ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ቤተ ክርስቲያን ከች አልኩ:: የክርስትና እናቴም እዚያው ነበረች:: እንዴት የሚያስደስት ፀሐያማ ጠዋት መሰላችሁ:: እውነተኛው የልደት ቀኔ ዛሬ ነው:: ወደ ፎቁ ወጣንና ቄስ ቡትሮስን በቢሯቸው መጠበቅ ጀመርን:: በዙርያዬ ያለው ነገር ሁሉ በደስታ ለመዘመር የተዘጋጀ ይመስላል:: በደረጃዎቹ እየወጡ ሲመጡ የቄስ ቡትሮስ የጫማቸው የኮቴ ድምፅ ተሰማን:: አዎን እርሳቸው ናቸው:: ገጻቸው ያበራል:: ያንን ብሩኅ ገጽ መቼም አልረሳውም:: ሰላም አሉንና እጃችንን እየወዘወዙ ጨበጡን::





በፍቅር፣ በደግነት፣ በስስት ነበር የሚያዩኝ::

ተያይዘን ወደ ማጥመቂያው ቤት ሄድን:: ሁላችንም ወደ ምዕራብ ዞርንና ጠላታችን ሰይጣንን እንክድሃለን አልን:: ከዚያም ወደ ምሥራቅ ዞረን በኢየሱስ ክርስቶስ ስላለኝ እምነት ምስክርነት ሰጠሁ:: እኔ የዘወትር ልብሴን እስከማወልቅ ድረስ ቄስ ቡትሮስ ውጭ ወጥተው ጠበቁን:: ስጨርስም ወደ መጠመቂያው ገንዳ ገባሁ:: የመጠመቂያው ውኃ ሰውነቴን ሲነካው ልዩ እና ደስ የሚል ስሜት ተሰማኝ:: ይህን ስሜት በበቂ ሁኔታ ልገልጸው አልችልም:: እንዲህ ያለ የደስታ ስሜት ከዚያ በፊት ተሰምቶኝ አያውቅም:: ወደፊት ግን በሚገባ ለመግለጽ እንደምችል ተስፋ አደርጋለሁ:: የኤሌክትሪክ ኃይል በሰውነቴ ውስጥ ያለፈ ነው የመሰለኝ:: አሁን የሚሰማኝን ደስ የሚልና ሰላማዊ ስሜት ያን ጊዜ በራእይ በጌታዬ እግር ሥር ተንበርክኬ ካልሆነ በቀር ሌላ ጊዜ አግኝቼው አላውቅም:: መቼም ይህንን ስሜት እንደያዝኩት ለረዥም ጊዜ መኖር እንደምችል ተስፋ አደርጋለሁ::

ያዘጋጀሁት የክርስትና ስም እንዳለ ብለው ቄስ ቡትሮስ ጠየቁኝ:: «የለኝም፣ እባክዎን እርስዎ ይምረጡልኝ» አልኳቸው:: እርሳቸውም «እግዚአብሔር ይመርጥልሻል» አሉኝ:: ከዚያም ትንሽ ቆዩና «ፌቤን[16] ቢሆንስ» አሉኝ:: «ይሁን» ብዬ ተስማማሁ:: እጃቸውን በራሴ ላይ ጫኑና «ፌቤን ሆይ በአብ ስም አጠምቅሻለሁ» ብለው እናቴን ጫን ሲሉኝ ወደ ውኃው ውስጥ ገባሁ:: ዓይኖቼን ከፈትኳቸው:: በአንድ የመስተዋት ኳስ ውስጥ ተቀምጦ ደስ የሚሉ ድምፆችን የመስማት ያህል ነው:: የማየው ነገር ሁሉ የሚማርክ ነው:: ተመልሼ ወጣሁ:: ከዚያም በረዥሙ ተነፈስኩ:: ቄስ ቡትሮስም «በወልድ ስም አጠምቅሻለሁ» ብለው እናቴን እንደገና ጫን አደረጉት:: ከዚያም በድጋሜ ወደ ውኃው ውስጥ ገባሁ:: ተመሳሳይ ርእይ አየሁ፤ ተመሳሳይ ድምፅም ሰማሁ:: ለረዥም ጊዜ ያህል በውኃው ውስጥ ለመቆየት ከራሴ ጋር ታገልኩ:: ከዚያም ተመልሼ ወጣሁ:: በመጠመቂያው ገንዳ ውስጥ ረዥም ሰዓት ለመቆየት ስለፈለግኩ በረዥሙ አየር ሳብኩ:: ቄስ ቡትሮስም «በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠምቅሻለሁ» ብለው ራሴን ጫን ሲያደርጉኝ ለሦስተኛ ጊዜ ገባሁ:: ያንን የሚያስደንቅ ራእይ ማየት፣ ያንንም የሚያስደምም ድምፅ ለረዥም ጊዜ ያህል ማስማት ተመኘሁ::

ከውኃው ብቅ ስል ቄስ ቡትሮስ «እግዚአብሔር ጸጋ መንፈስ

16. ፌቤን ቅዱስ ጳውሎስን ያገለግሉ ከነበሩት እናቶች አንዷ ናት:: ሐዋርያው ወደ ሮሜ የላከውን መልእክት ያደረሰች እርሷ መሆንዋ ይታመናል:: የስሙ ትርጓሜ "ንጹሕ" ማለት ነው::ሮሜ. 16÷ 1

ቅዱስን ያድልሽ ዘንድ ጸልዩ» አሉኝ:: እኔም በዚያው በመጠመቂያ ገንዳው ውስጥ እንደ ቆምኩ «መፍቀሬ ሰብእ የሆንከው ሩኅሩኅ እና ደጉ እግዚአብሔር ሆይ፣ ለክቡራን ሐዋርያትህ እንዳደልካቸው ሁሉ ለእኔም ጸጋ መንፈስ ቅዱስን እባክህ አድለኝ፤» ብዬ ጸለይኩ:: ወዲያውም የእግዚአብሔር እጅ የነካኝ ያህል ተሰማኝ:: «ጌታ ሆይ ራሴን መሥዋዕት አድርጌ አቀርብልሃለሁ:: የእኔ የሆነው ሁሉ ያንተ ነው:: ሕይወቴን ላንተ ለማስረከብ ቃል እገባልሃለሁ:: እነሆ አሁን ሕይወቴን እና በምድር ላይ የምቆይባቸውን እያንዳንዶቹን ቀናት ላንተ መባ አድርጌ ሰጥቼሃለሁ:: እኔ ያንተ ካልሆንኩ ሁሉስ ምን ይበጀኛል::»

ቄስ ቡትሮስ ፊቴን እና መዳፎቼን ሜሮን[17] ቀቡኝ:: ምሥጢረ ሜሮን የተጠመቁ ክርስቲያኖች ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ለማግኘት የሚቀቡት ነው ::

ቄስ ቡትሮስ ከመጠመቂያ ቤቱ እንደወጡ እኔ ልብሴን ለበስኩ:: ውስጤን የሚሞላ ደስ የሚል ስሜት ውስጥ ነበርኩ:: ጌታ ሆይ አሁን ጥምቀት ማለት ምን እንደሆነ ተረዳሁት:: ሊገለጥ የማይችል ድንቅ ምሥጢር ነው:: አሁን እንግዲህ እኔ ማነኝ? ፈጽሞ የተለየሁ ሆኛለሁኮ! ከአንተ ጋር ሞቼ ከአንተ ጋር ተነሣሁ[18]፤ ላንተ-ባንተ፤ እነሆ በአንተ ማመን ከጀመርኩ አንድ ዓመት አለፈ:: ነገር ግን የዛሬው ቀን ከሁሉም የተለየ ነው:: ከመጽሐፍ ቅዱስ ደጋግሜ እንደ ተረዳሁት ከሆነ እያንዳንዱ ቃል በየዕለቱ የራሱ ምሥጢር አለው::

እግዚአብሔር ቸር እንደሆነ ቅመሱ፣ እዩም (መዝ.33÷8)

እነሆ እግዚአብሔር ሲናገረኝ ተሰማኝ:: «አሁን ድምፅሽን ከፍ አድርገሽ መናገር ትቺያለሽ፤» አለኝ:: እንዴት ያለ ፈቃድ ነው:: አሥረውኝ የነበሩ ሠንሠለቶች ሁሉ ሲበጣጠሱ ተሰማኝ:: አሁን ሙስሊሞች ቢገድሉኝ እንኳን ምንም አይመስለኝም:: አሁን ካንተ ጋር ነኝና፤ ከዚህ ሌላ ምንም አልፈልግም:: ስላንተ እመሰክራለሁ፤ ፈጽሞ መናገር አላቆምም፤ እናገራለሁ - እናገራለሁ - እናገራለሁ:: የትም ቦታ፣ መቼም ቢሆን፣ በማናቸውም አጋጣሚ እመሰክራለሁ::

እንደገና ከተወለድኩበት ከዚያ የመጠመቂያ ቤት ወጥቼ ቅዱስ

17.በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት ቅዱስ ሜሮን ልዩ በሆነ መንገድ የሚዘጋጅ ዘይት ነው:: በግብፅ ቤተ ክርስቲያን ትውፊት በየሰባት ዓመቱ ሜሮን ሲፈላ ከጥንቱ ሜሮን ጋር አዲሱ ይዋሐዳል:: ይህም አዲሱን ሜሮን ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ ሲፈላ ከነበረው ሜሮን ጋር ለማገናኘት ነው::

18. ሮሜ.6÷5





ቁርባንን ለመቀበል ወደ ቤተ ክርስቲያን ገባሁ:: ይህ ቀን እንዴት የተቀደሰ ቀን መሰላችሁ:: ይህንን ቀን ለማየት ስናፍቅ ነው የኖርኩት:: ሙሽራ በሰርጓ ቀን የሚሰማት ስሜት ነው አሁን የሚሰማኝ:: መሬቱን በረገጥኩ ቁጥር በአየር ላይ የምሄድ ይመስለኛል:: የበረርኩ ያህል ይሰማኛል::

አሁን በካህኑ ፊት ቅዱስ ቁርባን ለመቀበል ቆሜያለሁ:: ያኔ ሳየው ደስ የሚል ራእይ ነበር፤አሁን ግን እውን ሆነ:: እነሆ የምስጢረ ቁርባን ተካፋይ ሆንኩ:: እንዴት ድንቅ ነው:: ቁርባኑን ስቀበል ሥጋ የተቀበልኩ ያህል ነው የተሰማኝ::

ምንድን ነው ያደረግኩት? መዋጥ አለብኝ አልኩና ዋጥኩት::

ከዚያም ክቡር ደሙን ተቀበልኩ::

ይህን ለመቀበል የሚቻለው ምን አፍ ነው!

ይህ የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ ነው::

በፍጹም ልባቸው ለሚወዱት በአማን ቃል ኪዳኑ
ይፈጽምላቸዋል::

# ምዕራፍ አምስት

# በመስቀሉ ሥር

ከክርስቶስ ጋር መኖር እንዴት ውብ እና አስደሳች ኑሮ ነው! ከቄስ ቡትሮስ የኖላዊነት ጥበቃን እና ፍቅርን አግኝቻለሁ:: ከተጠመቅኩ በኋላ በየጊዜው ወደ ቤተ ክርስቲያን እየሄድኩ ሥጋወደሙ እቀበላለሁ:: ሥራዬ ከባድ ሸክም መስሎ ይሰማኝ ነበር:: በሥራ ገበታዬ እንደ ቀድሞው መስዬ ለመታየት የማደርገው ሁሉ ጭንቀት ሆኖብኛል:: ግን እንዴት አድርጌ በውስጤ የተፈጠረውን አዲሱን ማንነቴን ለረዥም ጊዜ ልደብቀው እችላለሁ?

ሰው ሁሉ «ምን አዲስ ነገር ገጠመሽ?» እያለ ባገኘኝ ቁጥር ይጠይቀኛል:: አንዳንዶቹም «ተለውጠሻልኮ» ይሉኛል:: ልክ ናቸውኮ! መለወጤን እንዴት አድርጌ መደበቅ እችላለሁ:: ጌታ ሆይ አንተ በውስጤ በሚያስደንቀው ብርሃንህ ትኖራለህ፤ ለውጠህኛል:: አቀራረቤ ተለወጧል:: ድምፄ ተለውጧል:: ጠባዬም ተለውጧል:: አሁን ኀሊናዬ እና ልቡናዬ ያንተ ናቸው:: ይህ የትምህርት ዘመን እስከሚያልቅ ድረስ ርጋታዬን እንድ ዘልቅበት እባክህን ርዳኝ::

በመንፈሳዊ ልደት የተወለድኩበት 1988 ዓም ተጠናቀቀ:: አዲሱ ዘመን 1989 መጣ:: አዲሱን ዓመት የተቀበልኩት በቤተ ክርስቲያን ነው:: ታኅሳስ 29 ቀን 1989 ዓም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በፊትህ ቆሜ አንተን እያመሰገንኩ ነበር:: ያ ያለቀው ዓመት ለእኔ ልዩ ዓመት ነበር:: አንተን ካየሁበት ከዚያ ከመጀመርያው ቀን ጀምሮ ያ ዓመት ልዩ ነበር:: ቀጣዩም ዓመት የተባረከ እንደሚሆን አምናለሁ:: ዓይኖቼን ከደንኳቸውና «እግዚአ መሐረነ ክርስቶስ» አልኩ::

ያን ጊዜም የተሰቀልከውን እና የተቸነከርከውን አንተን በራእይ አየሁህ:: የእሾህ አክሊል በራስህ ላይ ተደፍቷል:: ከእሾህ አክሊሉ የደም ነጠብጣብ ይወርዳል:: ፀጉርህ እና ጢምህ በደም ተነክሯል:: የሕመምህን ብርታት ከገጽታህ ላይ አየው ነበር:: ከስቃይህ ብዛት የደም ሥሮችህ የፈነዱ ነበር የሚመስሉት::

ይህ ሁሉ በዓይኔ ላይ እንደ ፊልም አለፈ:: ያን ጊዜም ልቤ በሕመም ተመታ:: አንደበቴን አልፎ ሊወጣ የነበረውን ጩኸት እንደ ምንም አፈንኩት:: ዓይኔን ስገልጠው የሥነ ስቅለቱ ሥዕል ፊት





ለፊቴ ነበር:: «ጌታ ሆይ ይህንን ሁሉ መከራ የተቀበልከው ለኛ አይደል? ያየሁትን ነገር ማንም ሊሸከመው ወይም ሊገልጠው አይቻለውም:: ይህንን ሁሉ ለኛ ስትል ተቀ በልክ?»

በነጋታው ወደ ቄስ ቡትሮስ ሄጄ ያየሁትን ነገርኳቸው:: ከአስተያየታቸው ያየሁት ነገር ምን እንደሆነ ተረዳሁት:: መምህረ ትኅትና የሆኑት ቄስ ቡትሮስ ረጋ ብለው «ኢየሱስ ክርስቶስ ላንቺ ሲል ምን ያህል መከራ እንደተቀበለ እንድታውቂ ይፈልጋል::» አሉኝ:: «እኔም ለርሱ ስል መከራን መቀበል አለብኝ፤ መስቀሉን መሸከም አለብኝ:: እግዚአብሔር ሆይ እባክህ አበርታኝ፤ በድካሜም ጊዜ ጽንዐትን አድለኝ» አልኩ::

ከተወለድኩ ጀምሮ ያለ ብርቱ ሕመም፣ ወይም ያለ አፕሬሽን፣ ወይም ያለ አደጋ ያሳለፍኩት ዓመት አልነበረም:: በየጊዜው ለሞት የሚያደርስ አደጋ ያጋጥመኝና እግዚአብሔር በተአምራት ከሞት አፋፍ ይመልሰኛል:: 1988 ዓም ግን ያለ አንዳች ችግር ነው ያለፈው:: ጌታ ሆይ ስለ ጥበቃህ በፊትህ ሰግጄ አመሰግንሃለሁ:: እግዚአብሔርም «ይህ ሁሉ የመጣብሽ አንቺን ለማሰቃየት ሳይሆን ትዕግሥትን እና ጽንዐትን ገንዘብ ታደርጊ ዘንድ ነው» አለኝ:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የተናገረውን አሰብኩት:: "ይህ ስለ ክርስቶስ ተሰጥቷችኋል:: ስለ እርሱ መከራን ደግሞ ልትቀበሉ እንጂ ልታምኑ ብቻ አይደለም[19]" ከዚህ ቃል አንተ መካሪ፣ አስተማሪ እና አጽናኝ መሆንክን ተረድቻለሁ:: እኔን ለቀጣዩ ጉዞ እያዘጋጀህኝ ነው::

ያገባሁና የሦስት ልጆች እናት ነኝ:: ኑሮዬም በቤተሰቦቼ ዙርያ የታጠረ ነው:: ሥራዬ እና ት/ቤቴ ለእኔ የመንግሥቴ ግዛቶች ነበሩ:: እዚያ ራሴን ንግሥት አድርጌ ኖሬያለሁ:: ከዚህ በላይ ልወደው የምችል ነገር አገኛለሁ ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር:: አሁን ግን ለእኔ ስትል ስታነባ ካየሁት ዕንባ በላይ ምንም ዋጋ ያለው ነገር እንደሌለ ተረዳሁ:: እነሆ ቸርነትህ በእኔ ላይ ይሥራ፤ ሁሉን ቻይነትህ በእኔ ይገለጥ፤ ሊደረስበት የማይቻለው ታላቅነትህም ይነገርለት::

ከ1964-1983 ድረስ በትዳር ኖሬያለሁ:: የትዳር ቆይታዬ አጭር የሆነውና በቀላሉ ሊያበቃ የቻለው ያለ ምክንያት አልነበረም:: የእግዚአብሔር ዕቅድ በውስጡ ነበረበት:: በሚያዝያ 1980 ከባድ የሆነ ዕጢ ይዞኝ እንቴ በምትሠራበት ኤይን ሻምስ ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል ተኝቼ ነበር:: ዕጢው የማኅፀን ካንሠር ነው ተባልኩኝ:: በዚያም ምክንያት አፕሬሽን ተደረግኩ:: የአፕሬሽኑን ሕመም መቋቋም

19. ፊልጵ.1÷29

ተሰኖኝ ራሴን ሳትኩ:: ጥልቅ በሆነ የጨለማ ገደል የወደቅኩ ነበር የመሰለኝ:: በሽታው ከባድ የሆነ ጥንቃቄ ስለሚያስፈልገው ባለቤቴ አስፈላጊ በሆነው ጊዜ መጠራት እንዲችል የስልክ ቁጥሩን በሆስፒ ታሉ እንዲያስቀምጥና በተጠራም ጊዜ ፈጥኖ እንዲደርስ ተነገረው::

ከሁለት ቀናት በኋላ ዶክተሩ እየመረመረኝ እያለ አፈፍ ብዬ ነቃሁ:: ከዚያም ራሱን የሳተ ሰው የሚያሰማውን ዓይነት ጩኸት አሰ ምቼ እንደገና ወደቅኩ:: በዙርያዬ የነበሩት ሁሉ በሕይወት መኖር ያለመኖሬን ለማረጋገጥ ይጥሩ ጀመር:: በመጨረሻም ተስፋ ስለቆ ረጡ ቀጥሎ ሊመጣ የሚችለውን የባሰ ነገር መጠባበቅ ያዙ:: ራሴን ከሳትኩበት ስነቃ ባለቤቴን አጣሁት:: የጤንነቴን ሁኔታ መጀመርያ ለእርሱ መንገር ነበር የፈለግኩት:: ሰዎችን ልከ ባስፈልገውም ላገ ኘው አልቻልኩም:: በመጨረሻም በእኔ ጤንነት ምክንያት የተፈጠረ በትን ጭንቀት ለመርሳት ቢሮው ገብቶ ነበር የተገኘው:: ሊመጣ ይችላል ብሎ የገመተውን መጥፎ ዜና ለመስማት ስለ ሠጋ ነበር ይህ ንን ያደረገው:: ከፊቱ ላይ ይሄው ይነበብ ነበር:: በቀዶ ጥገናው ምክ ንያት ከደረሰብኝ ሕመም ይልቅ ይህ የርሱ ተግባር አመመኝ:: የጤን ነቴን ሁኔታ አየት እንኳን ሳያደርግ እንዲያ በአደገኛ ሁኔታ መሆኔን እያወቀ እንዴት ቢሮው ሊገባ እንደቻለ ሊገባኝ አልቻለም:: ይህ ሁኔታ በጣም ነበር የተሰማኝ:: በዚህ የተነሣም ከእርሱ ለመለየት ወሰንኩ::

እናም ሊታመን በማይችል መንገድ በ1983 ዓም ተለያየን[20]::

አንድ ቀን መልከ መልካም እና ረዥም ከሆነው ወንድ ልጄ ጋር በእግራችን እየተጓዝን እያለን የተፈጸመውን ነገር አልረሳውም:: ከእርሱ ጋር ጎን ለጎን ሆነን በመንገዱ ዳር እያወራን ስንጓዝ ብስ ክሌት የሚነዳ አንድ ሕፃን ልጅ ትከሻዬ ላይ ገጨኝ:: ልጁ ሆን ብሎ ሳይሆን ከመኪና ሲሸሽ ነበር የገጨኝ:: ሚዛኔን ስቼ እግሬ ላይ ስለ ወደቅኩበት ቁርጭምጭሚቴን ወለም አለኝ:: ልጄም ወዲያውኑ ወደ ሆስፒታል ወሰደኝ::

አጥንቴ ከመሠበሩም በላይ በውስጤ ደም ይፈስሰኝ ነበር:: ከታከምኩ በኋላ ወደ ወንድሜ ቤት ተወሰድኩ:: በዚያም ሁለት አስጨናቂ የሆኑ ቀናት አሳለፍኩ:: ከሕመሙ በላይ ያሳሰበኝ መጽ

20. እንደ እስልምና ሕግ አንዲት ሴት ባለ ትዳር ከሆነች ሃሳቧን የመግለጥም ሆነ በፈለገችው መንገድ ሃይማኖታዊ መብቷን የመገልገል ዕድል የላትም:: ሌላው ቀርቶ ብቻዋን ከሀገር መውጣትም አትችልም::ፓስፖርት ለማግኘት የባሏ ፈቃድ የግድ አስፈላጊ ነው:: ከሦስት ቀን በላይ ከቤቷ ርቃ ለመጓዝም ቢያንስ ባለ አደራ የሆነ ወንድ ጠባቂ ያስፈልጋታል::





ሐፍ ቅዱስን ለማንበብ እና ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ አለመቻሌ ነበር::

በሁለተኛው ቀን ሌሊት እርፍ ጨብጬ እንዴት ወደ ኋላ እመለ ሳለሁ? እያልኩ እጨነቅ ነበር:: ከዚያም አምላኬን «እባክህ ፈውሰኝ» ብዬ ከልቤ ለመንኩት:: በነጋታው ጠዋት የወንድሜ ሚስት ቀሰቀ ሰችኝና «ዛሬኮ ድብን ብለሽ ነበር የተኛሽው» አለችኝ:: እግሬን አየሁት:: ድኗል:: ከአልጋ ወረድኩና መሬት ላይ ቆምኩ:: የሕመሙ ስሜት አይሰማኝም:: ምንም የተለየ ነገር አላደረግኩም:: በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ጸለይኩ:: በስሙ የሚለመን ነገር ሁሉ ይፈጸማልና ፈወሰኝ:: የኢየሱስ ክርስቶስ አባት እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው[21]::

ልጆቼ ሊጠይቁኝ መጡ:: ወንዱ ልጄ የዶክተሩን ትእዛዝ ጥሼ በእግሬ ቆሜ ስላየኝ ደስ አላለውም:: «ለመቆም ገና አሥር ቀን ይቀ ርሻልኮ» አለኝ:: እኔም «ወደ ቤቴ እመለሳለሁ» አልኳቸው:: ይህንን ሃሳቤን ሁሉም አንድ ሆነው ተቃወሙኝ:: በዚያም ተብሎ በዚህ ግን መሄድ አለብኝ:: ገላዬን ልታጠብ ልብሴን ሳወልቅ በውስጥ ደም ይፈ ስሰኝ ከነበረው ቦታ ላይ የመስቀል ምልክት በትንሹ ታየኝ:: እናም እርፍ ጨብጦ ወደ ኋላ መመለስ እንደማይገባ ተረዳሁ::

አቤቱ ይቅር በለኝ:: ከማንም በላይ አንተን እወዳለሁ፤ ፍቅርህ ከምንም ነገር ጋር ሊያነጻጽሩት የማይቻል ነው:: ያንተ ብቻ ነኝ:: ወደፊትም ያንተ ብቻ እሆናለሁ:: ያ የመስቀል ምልክት እግሬ ፈጽሞ እስኪድን ድረስ ለሦስት ሳምንታት ያህል እዚያ ነበር:: እግሬ ሲድን መስቀሉም ተሠወረ::

የትምህርት ዘመኑ እያለቀ ነው:: የመዝጊያ ፈተና የመስጫ ጊዜው ተዳርሷል:: በተቻለኝ መጠን ምንም ያልተፈጠረባት ሰው መስዬ ለመታየት ሞከርኩ:: ሥራዬን መልቀቅ እንዳለብኝ ይገባኛል:: እግዚአብሔር በዚህ ጉዳይ ይረዳኝ ዘንድ ለምኜዋለሁ:: በት/ቤቱ ያለው ሰው ሁሉ አሁን በተለየ መንገድ ነው የሚያየኝ:: በእኔ ላይ የሚያዩትን አስገራሚ ለውጥ ሁሉም በንቃት ነው የሚከታተሉት:: በጣም የምትቀርበኝ ጓደኛዬ የነበረችው የት/ቤቱ ርእሰ መምህርት እንኳን አሁን እየሸሸችኝ ነው:: ሁሉም ነገር እየተለየ፣ እየተለየ መጥ ቷል:: አንድ ቀን የት/ቤቱ የማኅበራዊ አገልግሎት ባለሞያ ወደ ቢሮዬ መጣች:: ምን አልባት የሥነ ልቡና ችግር ገጥሞኝ ይሆን እንዴ ብላ አዝና ነበር:: «ምንድን ነው የሆንሺው? ዛሬ ዛሬ ድምፅ ሺን ሰምቶ የሚያውቅ አንድም ሰው የለም፤ ያቺ የምናውቃት ናሀድ

21. ዮሐ.14÷13-14፤16÷23-24፤የሐዋ.3÷6-8

ወዴት ሄደች?» ስትል ጠየቀችኝ:: ያቺ የምታውቃት ናህድ መሞቷን ልነግራት ፈልጌ ነበር:: አሁን የምታያት ናህድ አዲሷ የኢየሱስ ክርስቶስ ልጅ የሆነቺው ናህድ መሆንዋን ላበስራት ፈልጌ ነበር::

ረጋ አልኩና «አሁን ስለ አምላኬ በሚገባ ስላወቅኩ ይሆናል የተለወጥኩት:: የድሮውማ ድሮ አለፈ:: አሁን አዲስ ኑሮ መኖር እፈልጋለሁ» አልኳት:: በርግጥ ምላሼ ሊያረካት እንደማይችል ገብቶኛል:: እርሷም «የሚያስጨንቅሽ ነገር አለ?» ስትል ጠየቀችኝ:: እኔም ፈገግ ብዬ «ስታይኝ ችግር ያለብኝ እመስላለሁ እንዴ?» ስል መለስኩላት:: ነገሬ እንዳልጣማት እየታወቀባት «እረ በጭራሽ፣ ገጽታሽ ብሩኅ ነው፤ ሁኔታሽም በመልካም ጤንነት ላይ ያለሽ መሆኑን ያሳያል:: ነገር ግን እንዲህ በአንድ ጊዜ ልውጥ ያደረገሽ አንድ ነገር መኖር አለበት» አለች:: እኔም መልሼ «በዚህ መልኩ ስለተረዳሽኝ አመሰግንሻለሁ፤ ምንም ችግር እንደሌለብኝም ላረጋግጥልሽ እወዳለሁ:: ምንም ችግር የለብኝም፤ ስለ ተጨነቅሽልኝ ግን አመሰግንሻለሁ» አልኩና ሸኘኋት::

አያሌ ረገኝዥምና አስጨናቂ ዕለታት ነጎዱ:: ለእግዚአብሔር ምስጋና ይግባውና የትምህርት ዘመኑም ተጠናቀቀ:: ት/ቤቱም ለበጋው የዕረፍት ጊዜ ተዘጋ:: እኔም ከጓደኞቼ ጋር ልዩ ልዩ ቅዱሳት መካናትን ለመሳለም ዕቅድ ነደፍኩ:: ክርስቲያን ጓደኞቼ በየጊዜው ቤቴ እየመጡ ይጠይቁኝ ነበር:: መዝሙር በመዘመር እና ጸሎት በመጸለይ አብረን እናሳልፋለን::

ያ ጊዜ ማለት ብዙ ዓይኖች ይከታተሉኝ የነበሩበት ጊዜ ነው:: የሕንፃው ባለቤት መግባት እና መውጣቴን ሁሉ በንቃት ይከታተል ነበር:: ወደ እኔ የሚመጡትንም እነማን እንደሆኑ ማወቅ ይፈልጋል:: እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ሊጠይቁኝ የሚመጡትን «ማን እንደሆናችሁ ዐውቃለሁ፤ ብዙ የእናንተ ዓይነቶች በየጊዜው እየመጡ የትእንዳላችሁ ይጠይቁኛል» እያለ መናገርም ጀምሯል::

ከዚህ አፓርትመንት መልቀቅ እንዳለብኝ አሰብኩ:: ነገር ግን ሌላ አፓርትመንት ማግኘት ቀላል አይሆንም[22]:: ችግሩን ችላ ብዬ ከእግዚአብሔር ጋር ባለኝ ሕይወት መደሰቱን ቀጠልኩ::

ሰኔ ሰባት ቀን 1989 ዓም ቅዳሜ ቀን ከአንዳንድ ጓደኞቼ ጋር የአባ ብሶይን ገዳም[23] ለመጎብኘት ሄድኩ:: በዚያ የሚገኙ አንዳንድ

22. በዚያ ጊዜ ግብፅ ውስጥ የመኖርያ አፓርትመንት ከፍተኛ ችግር ነበረ:: ለመጋባት የሚፈልጉ እጮኛሞች እንኳን በቤት እጥረት ምክንያት ለመጋባት ከወሰኑበት ጊዜ እጅግ ይዘገዩ ነበር::

23. የአባ ብሶይ ገዳም ከካይሮ ወደ እስክንድርያ በሚወስደው በረሃማ መንገድ ዳር ከሚገኙት አራት ገዳማት አንዱ ነው:: ገዳሙ የተቆረቆረው በንጥራን ሸለቆ ውስጥ ነው::





አበው ያየሁትን ራእይ እና እግዚአብሔር የሠራውን ድንቅ ሥራ ምሥክርነቱን በቴፕ እንድቀዳ ጠየቁኝ:: ስቀዳውም ሙሉ ስሜን እና በዚህ ሥራ ውስጥ የተሳተፉትን ሁሉ በዝርዝር እንድጠቅሳቸው መከሩኝ:: እኔም በነገሩ ተስማማሁ:: እነዚያ አበው ይህ ነገር ምሥጢር ሆኖ እንደሚጠበቅና ከዚያ ገዳምም በምንም ዓይነት እንደማይወጣ ቃል ገቡልኝ:: እኔም ምሥክርነቱን ቀዳሁት::

የበጋው የዕረፍት ወራት አለቀና ት/ቤት ተከፈተ:: ወደ ት/ቤቱ ለመግባት ከበሩ ስደርስ አካባቢው አፈነኝ:: መተንፈስ አልቻልኩም ነበር:: መረጋጋት አቃተኝ:: ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አብረውኝ የሚሠሩት ሙስሊሞች ሁሉ በአሽሙርና በንቀት ተቀበሉኝ:: ደነገጥኩ:: እንዴት ነው በእኔ ላይ እንዲህ ሊሆኑ የቻሉት? ከዚያ በፊትኮ ቢሮዬ ፊት እንኳን ሊቆሙ ይፈሩ ነበር:: ዛሬ ግን በሽሙጥ ያዩኛል:: እንዲያውም አንዳንዶቹ በንቀት «ይህንን ዓለም እና የሚመጣውን ዓለም አጣች፣ ምናልባትም እስከዓለም ፍጻሜ የተረገመች ሆና ትኖር ይሆናል፤መቼም እርሷን መግደል መታደል ነው» ይላሉ::

እንዲህ የሆኑት ለምን ይሆን? ብዬ ለራሴ ምክንያቶችን ማሰብ ጀመርኩ:: ከዚያም ምክትል ርእሰ መምህርቷን ለመጠየቅ ሄድኩ:: ሙስሊም ናት:: ገና ስታየኝ ፊቷን አዞረች:: እኔም «ምን ተፈጠረ? እንዲህ የምትሆኝውስ ለምንድን ነው?» ስል ጠየቅኳት:: በንዴት እና በተጠራጣሪነት ስሜት ውስጥ ሆና «ደግሞ ምን ችግር አለ ትያለሺ? አሁን ምን እንደተፈጠረ አታውቂምና ነው?» አለችኝ:: «እመኝኝ ምንም አላውቅም» ስል መለስኩላት:: «ላምንሽማ አልችልም፤ መጀመርያ እንደማታውቂ ማይልኝ» አለችኝ:: «አልምልልሽም ፤የአምላኬንም ስም በከንቱ አልጠራም» ስል መለስኩላት:: እርሷም «ወይጉድ!ለመሆኑ አንቺ ፈጣሪን ታውቂዋለሽ?» አለችኝ:: «ያለ ጥርጥር አምላኬንማ አውቀዋለሁ፤ ያለ እግዚአብሔር በቀር ሌላ አምላክ የለም» አልኳት:: ጮኸችብኝና «በያ ይህንን ቃል ጨርሺው፣ ጨርሺው» ስትል አፋጠጠችኝ:: ምን ማለት እንደፈለገች ያልገባኝ መስዬ ለማለፍ ፈለግኩ:: «መልእክተኛው መሐመድ ነው» የሚለውን እንድጨምር እንደፈለገች ገብቶኛል:: የተናደድኩ መሰልኩና «እንዴት ብትንቂኝ ነው፤ አዝናለሁ፤ አንቺ ሳትይኝኮ መናገር የምችል ሰው ነኝ» ብያት ጥያት ወደ ቢሮዬ ተመለስኩ:: መቼም የለወጠኝን ምክንያት ሳያውቁት አይቀሩም::

ግን እንዴት ሊያውቁ ቻሉ?

ጥቂት ቆይቶ አንዲት ክርስቲያን የሥራ ባልደረባዬ መጣችና የእኔን ስም፣ የሳሚያን ስም፣ የሞፌድን ስም እና የሌሎችንም ስም

የጠቀስኩበትና ምስክርነት የሰጠሁበት ካሴት ተባዝቶ በየሰው እጅ መግባቱን ነገረችኝ:: ያንን ካሴት ለካ ሙስሊሙም ክርስቲያኑም እየተቀባበለ ይሰማው ጀምሯል:: የዛሬ ሃያ አንድ ቀን የተቀዳ ካሴት እንዴት ይህንን ያህል በአንድ ጊዜ ሊዳረስ ቻለ? ደግሞስ በጥብቅ ምሥጢር እንደሚጠበቅ ቃል ተገብቶልኝ አልነበረም እንዴ? ራሴን ልስት ትንሽ ነበር የቀረኝ:: እንዴት በሙስሊሞች እጅ ሊገባ ቻለ? ቀዝቃዛ ውኃ በላዬ ላይ የተቸለሰብኝ መሰለኝ:: አሁን ምን ማድረግ ነው ያለብኝ? በዚህ ሁኔታ እዚህ ት/ቤት አንዲት ደቂቃም ቢሆን መቀመጥ የለብኝም:: እናም ቶሎ ብዬ ወደ ቤቴ ተመለስኩ::

ቆስያለሁ:: በኃይል እንደተመታ ሰው ነው የቆሰልኩት:: ግራ ነው የገባኝ:: መድኃኒት በሆኑት የእግዚአብሔር እጆች ላይ ራሴን ብጥል ይሻለኛል አልኩና «አምላኬ ሆይ ምን ማድረግ ይሻለኛል:: ት/ቤት ውስጥ ሊገድሉኝ እንደደረሱ አይተሃል፤ የሚናገሯቸውን ቃላት እና የሚያዩኝን አስተያየት መሸከም አልችልም:: እባክህ ድካሜን አበርታ» እያልኩ መጸለይ ጀመርኩ:: ያን ጊዜ «ተነሽና መኖርያ ቀይሪ፤ ማንም ሊያጠቃሽና ሊነካሽ አይቻለውም» የሚል የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰማሁ::

ተመስገን ጌታዬ ዘወትር ትመራኛለህና::

ሥራዬን መልቀቁ ቀላል ነበር:: ቤቴን ለቅቄ ሌላ ቤት ማግኘት ግን አስቸጋሪ ነው:: የለም፣ የለም እንዲህ ብዬ መጨነቅ የለብኝም:: በአንተ ጥበቃ እተማመናለሁና:: ልብሶቼን ሰብስብ አድርጌ በዚያን ዕለት በቤተ ክርስቲያን ጉባኤ መኖሩን አስታወስኩ:: «እዚያ መሄድ አለብኝ፣ ምናልባትም የሚያጽናና ነገር አገኝ ይሆናል» አልኩና ወጣሁ::

ቤተ ክርስቲያን ስደርስ አንዷን ጓደኛዬን አገኘኋት:: እርሷም አያድ ከተባለ ኢንጅነር ዘመዷ ጋር አስተዋወቀችኝ:: እርሱም «አሁን ባለሽበት ቤት መኖሩ ተስማምቶሻል?» ሲል እንዳጋጣሚ ጠየቀኝ:: እኔም እግዚአብሔር ለምን ወደ ጉባኤው እንደጠራኝ አስተዋልኩ:: «ከዚያ አካባቢ ወጥቼ ክርስቲያኖች በብዛት በሚኖሩበት አካባቢ መኖር እንደምፈልግ ገለጥኩለት:: እርሱም ሃሳቤን በመቀበል አንድ ሕንፃ የሚገነቡ ሁለት ወንድማማቾች እንደሚያውቅና በሚገነቡትም ሕንፃ ላይ አንዲት ትንሽ ክፍል ለኪራይ ማዘጋጀታቸውን ገለጠልኝ:: «ከጥቂት ቀናት በኋላ አነጋግሬያቸው እነግርሻለሁ» አለኝ::

በቀጣዩ ቀን ት/ቤት ሄጄ መልቀቂያዬን አስገባሁ:: ርእሰ መምህርቷ መልቀቂያዬን በፍጥነት ነበር ያጸደቀችልኝ:: የወረዳው የትምህርት ቢሮም በፍጥነት ነበር መልቀቂያዬን ያጸደቀው:: በዚያው ዕለ





ትም መልቀቂያዬ ለትምህርት ምክትል ሚኒስትሩ ቢሮ ተላከልኝ:: የእግዚአብሔር ኃይል ነገሮችን ሁሉ በፍጥነት እያስኬደልኝ ነበር፡ «ጌታ ሆይ ላንተ ምስጋና ይድረስህ፤ አቤቱ ደካማነቴን ተመልክተህ ብርታትን አድለኝ:: ከእነርሱ የሚመጣብኝን አስፈሪውን ነገር ሁሉ ለመቋቋም እችል ዘንደ በፊትህ ሞገስን ስጠኝ:: እንዳያዩኝ ዓይናቸውን፣ እንዳይናገሩኝም አንደበታቸውን ያዝ፤ በትምህርት ሚኒስቴር የመጨረሻው መልቀቂያ እስኪሰጠኝ ድረስ ባንተ ኃይል እና ርዳታ በፊታቸው በጽናት እቆም ዘንድ አበርታኝ::

በማግሥቱ ቀን አያድ ደወለልኝና ሁለቱ ተቋራጭ ወንድማማቾች በሠሩት ሕንፃ ጣራ ላይ ያለውን አንድ ክፍል ሊያከራዩኝ መስማማታቸውን ገለጠልኝ:: ቀጠሮ ይዘን አብረን በመሄድ ቤቱን አየነው:: ገና በደንብ ባይጠናቀቅም ክፍሉ ግን በጣም ያምራል:: ወር በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ሊያጠናቅቁት ቃል ገቡልኝ:: አካባቢውን ዘወርወር ብዬ ሳማትር ከመንገዱ ባሻገር የእመቤታችን ቤተ ክርስቲያን መኖሩን ተመለከትኩ:: ሃሳቤን ሰብሰብ አድርጌ ጸሎት በልቤ አደረስኩ:: ወዲያውኑ ሁለት ሰዎች ከጣራው ላይ ሊወረውሩኝ ሲታገሉ በራእይ አየሁ:: ዘወር ስል ማንም በአካባቢዬ የለም:: እንዴት አስፈሪ ነገር ነው? ምን ሊደርስብኝ ይሆን? ደስታዬ ፍጹም እንዳይሆን የመጣ ነገር ይሆን እንዴ? ስሜቴን ተጭኜ ወደ ቤቴ ተመለስኩ::

የቤቱን ግንባታ መጠናቀቅ አለመጠናቀቁን የምመለከት መስዬ ደግሜ ወደ አካባቢው አመራሁ:: ያው ስሜት እንደገና ረበሸኝ:: እንዲያውም አሁን ከበፊቱ ይልቅ ባሰብኝ:: ምን ማድረግ እንዳለብኝ ግራ ተጋባሁ:: ወደ ቤቴ ስመለስ በልቡናዬ በጸሎት ላይ ነበርኩ «ጌታ ሆይ ይህንን ስሜት መረዳት አልቻልኩም፤ የነገርከኝ መልእክት ምንድን ነው?» ይህንን ነገር ለቄስ ቡትሮስ ለመንገር አሰብኩ::

ቄስ ቡትሮስን ለማነጋገር ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄድኩ:: ነገር ግን የት እንዳሉ በትክክል ሊነግረኝ የሚችል ሰው አጣሁ:: ሰዎቹ የሚመልሱልኝ ነገር እርስ በርሱ የሚጣረስ ነው:: አንዳንዶች ዕረፍት ላይ ናቸው፣ ሌሎቹ ታምመው ተኝተዋል፣ ሌሎቹም ሌላ ነገር ይነግሩኛል:: ጉዳዩ ለእኔ ሊገልጡልኝ ከሚችሉት በላይ ምሥጢራዊ መሆኑን ተረዳሁ:: በዚህ ሁኔታ ጥቂት እንደቆየሁ አንዱ የቤተ ክርስቲያኑ ዲያቆን መጣና አስደንጋጩን መርዶ አረዳኝ:: «ከሁለት ቀናት በፊት የመንግሥት የደኅንነት ኃይሎች ቄስ ቡትሮስን ይዘዋቸው ሄደዋል»

ስቅስቅ ብዬ አለቀስኩ:: ለእኔ የሚወዱኝ አባቴ ነበሩ:: ጥያቄዬን ሁሉ ልረዳው በምችለው መንገድ የሚመልሱልኝ አባት ነበሩ::

የሚያጋጥሙኝን ችግሮች እና ፈተናዎች ሁሉ የማማክራቸው አማካሪዬ ነበሩ። ኢየሱስ ክርስቶስ በእርሳቸው አድሮ ሥራ ሲሠራ እመለከት ነበር። «እባክህ ደጉ እና ሩኅሩኅ ጌታ ሆይ እርዳቸው፣ አጽናቸውም፤ ኃይልህንም ስጣቸው፤ ባደልካቸው ጸጋ የተነሣ ጽኑዕ አባት መሆናቸውን ዐውቃለሁና። እኔም ይህንን መርዶ ሰምቼ እንዳልናወጥ ርዳኝ» ብዬ ጸለይኩ።

ከቤተ ክርስቲያኑ ልወጣ ስል ቄስ ቡትሮስ ተለቅቀው በአንዱ ገዳም ውስጥ እንዳሉ ሰማሁ።

ወደ አዲሱ አፓርትመንት የምዛወርበት ቀን ደረሰ። ቀኑ እየቀረበ በሄደ ቁጥር ፍርሃቴም እየጨመረ መጣ። ደግሞ አሁን ያለሁበትን ቤት እንደምለቅቅ ለባለቤቱ ነግሬዋለሁ። ስለሆነም ወደ ኋላ ማለት አልችልም። ይህንን እያሰብኩ ዕቃዬን በማዘጋጀት ላይ እያለሁ አስቸኳይ መልእክት አለ ብሎ ኢንጅነር አያድ ደወለልኝ። በቶሎ መገናኘት አለብን ስላለኝ ወደ ተቀጣጠርንበት ቦታ ሄድኩ።

እንደተገናኘን የሕንፃው ባለቤቶች ሊያገኙኝ እንደሚፈልጉ ነገረኝ። ሁለቱን ወንድማማች ተቋራጮች ስናገኛቸው የነገሩን ነገር አስደንጋጭ ነበር። አንደኛው «ክፍሉን ልናከራይሽ ባለመቻላችን እናዝናለን» አለኝ። «ለምን?» ስል ጠየቅኩት። «በመንግሥት የደኅንነት ቢሮ ለሚሠራ ጓደኛዬ አንቺ ወደዚህ ሕንጻ እንደምትገቢ ስነግረው በማናቸውም መንገድ ናህድን ለመርዳት እንዳትሞክር፤ በመንግሥት የደኅንነት አካል እጅግ የምትፈለግ ሴት ናትና፤ እርሷን ሲረዳ የተገኘ ሁሉ አስፈላጊው ርምጃ ይወሰድበታል" ሲል አስጠነቀቀኝ» በማለት አስረዳኝ።

መርዶው አጥንት የሚሠብር ነበር። ያንን አፓርትመንት በጎበኘሁ ቁጥር ይሰማኝ የነበረውን ያንን የሚዘገንን ስሜት አስታወስኩት። አሁን ከሆንኩት ነገር ይልቅ ከጣራው ላይ ቢወረውሩኝ የተሻለ ነበር። አዝኜና ተስፋ ቆርጬ ወደ ቤቴ ተመለስኩ። ጉዳቴ ከባድ ሆነ፤ ልሸከመውም አልተቻለኝም። «እባክህን ረድኤትህን አሁኑኑ ላክልኝ፤ ይህንን መከራ እንዳልፈው እባክህን ርዳኝ» ብዬ ጸለይኩ። ወዲያውም «የሆነው ሁሉ ላንቺ መልካም ነው። ይህንንም በኋላ ትረጂ ዋለሽ። እባክሽን ተረጋጊ፣ ነገ ገዳሙን ስትጎበኚ መፍትሔ ታገኛ ለሽ» የሚል የእግዚአብሔርን መልስ ሰማሁ።

በነጋታው በናጥራን ሸለቆ የሚገኙትን ገዳማት ለመሳለም ሄድኩ። በዚያ ጉዞ ሳሚር የተባለ አንድ ጨዋ ክርስቲያን አገኘሁ። የደረሰብኝን ሁሉ በሰማ ጊዜ «መዲናት ናስር በሚባለው የካይሮ ክፍለ





ከተማ የሚገኝ የአጎቴ አፓርትመንት አለ። ሊያከራየው ስለሚፈልግ በጋዜጣ ላይ ማስታወቂያ አውጥቷል።» አለኝ። ለጉዳዩ ቀጠሮ ይዘን ተለያየን።

ያንን የወንድማማቾቹን ሕንፃ ስጎበኝ ለምን የሥጋት ስሜት ይሰማኝ እንደነበር ገብቶኛል። ያንን ሕንፃ ብከራየው ኖሮ ሰው ሁሉ ወዴት እንደምሄድ እና ከየት እንደምመጣ ሊከታተለኝ ይችል ነበር። ስለዚህም እግዚአብሔር ከዚያ ችግር ጠበቀኝ። አሁን ግን ሰው የማያውቀውን ቦታ አዘጋጀልኝ። ኮንትራቱን ተፈራርሜ ቁልፉን ተቀበልኩ። በቪክቶሪ ከተማ፣ አሥረኛው መንገድ ዳር የሚገኝ ባለ አንድ መኝታ ክፍል ቤት ነው። ዋጋውም ርካሽ ነበር።

ለእኛ መልካም የሆነውን ሁሉ የምታዘጋጅ ጌታ ሆይ ምስጋና ላንተ ይሁን። ይህንንም ቦታ ያዘጋጀህልኝ አንተ ነህ። ሕዝብ ከሚበዛበት ቦታ የራቀ፣ ብቻዬን ለመሆን የሚያስችል፣ ቦታ ነው። ሳሚር ቤቱን ጠጋገነልኝ። የኤሌክትሪክ መሥመሩንም ዘረጋ።

የትምህርት ቢሮው አሁን ካለሁበት ቦታ ስለሚርቅ በየጊዜው ጉዳዩን ለማስጨረስ መመላለስ አዳጋች ነበር። እናም የትምህርት ሚኒስትሩ መልቀቂያዬን በቶሎ ያጸድቁልኝ ዘንድ እንዲረዳኝ እግዚአብሔርን ለመንኩት። እርሱም «የጠየቅሽውን ነገር በነሐሴ 1989 ታገኝ ዋለሽ» ሲል መለሰልኝ።

ልቤ ተረጋግቶ ተጽናናሁ። ወደ አዲሱ ቤቴም ለመግባት በሙሉ ልቤ ወሰንኩ። ሞፌድ የዕቃ መጫኛ መኪና ይዞልኝ መጣ። ሳሚር እና ጓደኛውም አገዙኝ። «አቤቱ ሞፌድን ከክፉ ነገር ሁሉ ጠብቀው» ስል ጸለይኩ። በኤይን ሻምስ የሚገኘውን አፓርትመንቴን ቀስ ብዬ ለቅቄ ወደ አዲሱ ቤቴ ገባሁ። በዚህ በለቀቅኩት ቤት ውስጥ ላለፉት 15 ወራት ኖሬበታለሁ።

በቀጣዩ ቀን ወደ ት/ቢሮው አመራሁ። የምክትል ሚኒስትሩ ቢሮ ኃላፊ ሰላም አለኝና «እንኳን ደስ ያለሽ ሚኒስትሩ አጽድቀውልሻል» አለኝ። ከዚህ በፊት መልቀቂያ አቅርቤ ስለ ተፈቀደልኝ በሚል ተደስቼ አላውቅም። «ይህ ሁሉ የሆነው በአንተ ነው» ብዬ አምላኬን አመሰገንኩት። መልቀቂያዬን ራሴ ወስጄ ለትምህርት አስተዳደሩ አስረከብኩ። እግዚአብሔር ስለተጨመረበት ሁሉም ነገር በፍጥነት ይከናወን ነበር።

ከዚያ ስወጣ ሞፌድን እና ሳሚያን ስለሁኔታው ልነግራቸው ወደ ት/ቤት እግረ መንገዴን ጎራ አልኩ። ቢሮዬን ለመጨረሻ ጊዜ ገባሁበት። መሬቱ በአረንጓዴ ምንጣፍ አሸብርቋል። መስኮቱን ከምንጣፉ

ጋር የሚስማሙ ሻተሮች አሽብርቀውታል:: ሥዕሎችም ግድግዳውን አሳምረውታል:: ክፍሉ በውስጡ ሦስት ጠረጴዛዎችን ይይዛል:: የእኔን እና የሁለቱ ረዳቶቼን:: የትምህርት ቤቱ ፈተናዎች የሚቀመጡበት እና የፈተና ማባዣው ማሽን ያለበት ክፍል በመሆኑ ልዩ ጥበቃ ይደረግለታል::

ለመጨረሻ ጊዜ የቢሮዬን ዙርያ ገባ ማተርኩት:: እንዴት ባለ ዕብሪት እና ትዕቢት በዚያ ቢሮ ውስጥ እሠራ እንደነበር አስታወስኩ:: በት/ቤቱ ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና ኃላፊነቶችን ለመውሰድ ያደረግኩትን ትግል እና የት/ቤቱ አድራጊ ፍጣሪ ለመሆን እንድችል የተጠቀምኩባቸውን ዘዴዎች ሁሉ አስታወስኳቸው:: እንዴት ያለሁ ከንቱ ነበርኩ:: አሁን ግን ጌታ ሆይ አንተን ለመከተል ስል ሁሉንም ተውኳቸው:: ሁሉም ነገሮች ከንቱዎች ናቸው፤ የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ ቃል ምን ያህል ጥልቅ ምሥጢር እንደያዘ አሁን ገባኝ:: መፍቀሬ ሰብእ እግዚአብሔር ሆይ በአንተ ፍቅር ውስጥ ስንኖርና ምን ያህልም እንደምትወደን ስናውቅ ሁሉም ነገር ለኛ ዋጋ ቢስ ይሆናል:: አንተ ለኛ ሁሉም ነገራችን ነህና::

ሞፊድ ቀድሞም ያደርገው እንደነበረው ወደ ቢሮዬ መጣና አጠገቤ ተቀመጠ:: ልጄ መስሎ ነው የሚሰማኝ:: ቀና ብዬ አየሁትና «ግን ሞፊድ የሌሎችን ስሜት ስረግጥና እንዲያ ያልተገባ ነገር ሁሉ ስናገርህ ለምን ነበር የምትታገሠኝ?» ስል ጠየቅኩ:: እንዲህ ሲል ነበር የመለሰልኝ «ከሁለት ዓመት በፊት አራቱን ክርስቲያን ተማሪዎች እና ሁለቱን ክርስቲያን መምህራንን ፖስተር ለጥፈዋል ብለሽ መርማሪ እንዲጠራ ስታደርጊ እያነባሁ በእግዚአብሔር ፊት ቆሜ «ልጆችህን እንድታስጨንቅና እንድታስፈራራ ይህችን ሴት ለምን ዕድል ትሰጣታለህ» ብዬ ጠየቅኩት:: በሕልሜም በአንድ በዛፎች በተሞላ ጫካ ውስጥ ራሴን አገኘሁት:: ዛፎቹ ግንድ እና ቅጠል እንጂ ፍሬ አልነበራቸውም:: መሬቱ በድርቅ ምክንያት በትልቁ ተገምሷል:: የማየው ነገር ሁሉ አሳዛኝ ነገር ነው:: በመካከል ግን አንድ ታላቅ ዛፍ ብቅ አለ:: ቅርንጫፎቹም እስከ ሰማይ ደረሱ:: አያሌ ለምለም ቅጠሎችንም አወጣ:: የዛፉን ውበት እያደነቅኩ ፊት ለፊት ቆሜ ነበር:: ነገር ግን የዚህ ዛፍ ትርጉሙ ሊገባኝ ስላልቻለ "አምላክ ሆይ ሥራህ ታላቅ ነው፤ ነገር ግን በእነዚህ ዛፎች አማካኝነት ልታስተምረኝ የፈቀድከውን ነገር ልረዳው አልቻልኩም" ስል ጠየቅኩት:: አንድ ኃላ ያለ ድምፅም «ከናህድ አትለይ፤ በቀጣዩ ጊዜም እግዚአብሔርን በናህድ ውስጥ ታገኘዋለህ» አለኝ:: ባየሁት እና በሰማሁት ነገር እየተገረምኩ ከዕንቅልፌ ነቃሁ::





«ናህድ የእግዚአብሔርን ሥራ ልናይባት የምንችል ፍሬያማዋ ዛፍ ትሆናለች ማለት ነው? የማይታመን ነገር ቢመስልም እግዚአብሔር ግን እንዲህ እንዲሆን ፈቅዷል:: እናም ልቀበለው ይገባኛል ብዬ አሰብኩ:: ስለዚህም ካንቺ አልለይም ነበር:: ክርስቲያን የሆነችውን ርእሰ መምህርት እስከታባርሪያት ድረስ ከሚደርስብሽ ጥቃት እና ችግር ሁሉ አንቺን ለመከላከል እተጋ ነበር:: ያንን ነገር ስትፈጽሚ ግን «አሃ ያየሁት ሕልም ከሰይጣን የመጣ እንጂ ከእግዚአብሔር አልነበረም ማለት ነው» ብዬ አመንኩ:: ይህች ሴትኮ ችግር ፈጣሪ ናት አልኩና ወደ ቤቴ ገብቼ ላንቺ ባደረግኩት ነገር በመፀፀት አለቀስኩ::

«በዚያ ሌሊት አስደናቂ ሕልም አየሁ:: ሰፊ እና ንጹሕ በሆነ ጎዳና ላይ በመጓዝ ላይ ነበርኩ:: በሰማዩ ላይ ብርሃናቱ ፈክተዋል:: ዓይኖቼን ወደ ሰማይ ሳነሣ ብልጭ ድርግም በሚሉ ከዋክብት የታጀበ አንድ የሚያበራ ትልቅ መስቀል አየሁ:: ቀጥሎም እንዲሁ በተመሳሳይ ሁኔታ የታጀበ የሚያበራ ትንሽ መስቀል ተመለከትኩ:: በልቤም "የማየውን ነገር ትርጉም አልተረዳሁትም" ስል ጌታዬን ጠየቅኩት:: ከዚያም ትልቁ መስቀል ተሠወረና ያንቺን መልክ አየሁት፤ ቀጥሎም ትንሹ መስቀል ሲሠወር የልጅሽ መልክ መጣ:: እኔም ድምፄን ከፍ አድርጌ «ይህ ሊታመን የማይችል ነገር ነው፣ በእውኑ ናህድ እና ልጇ በሰማይ የሚያበሩ መስቀሎች ናቸውን? የማይታመን ነው፤» አልኩ:: ነገሩ ግን እየተደጋገመ ሦስት ጊዜ ሲፈጸም አየሁት::

በሦስተኛውም ጊዜ «ጌታ ሆይ ሁሉን ቻይ እንደ ሆንክ፣ የሚሣንህም ነገር እንደሌለ አምናለሁ፤» አልኩኝ:: ስነቃ አንቺ ወደ ርትዕት ሃይማኖት የተጠራሽ ሰው መሆንሽን ርግጠኛ ሆኜ ነበር:: እግዚአብሔር በአንቺና በልጅሽ ሊሠራ ስለ ፈቀደው ሥራ አመሰገንኩት:: ያ ቀን ደርሶ እግዚአብሔርን የማመሰግንበትን ቀን ስናፈቀው ኖርኩ:: እናም ይሄው ዘወትር አመሰግነዋለሁ::

«ለእኔ የገለጠልኝን ሁሉንም እስኪፈጽም ድረስ ላለፉት ሁለት ዓመታት ያንን በሕልሜ ያየሁትን ነገር ከማየው ነገር ጋር ሁሉ ሳዛምደው ኖርኩ::» ነበር ያለኝ::

ሞፊድን አየሁት:: ለእኔ ተወዳጅ ልጄ ነው:: ያንን ኢየሱስ ክርስቶስን ያየሁበትን ራእይ ለሞፊድ ስነግረው የሆነውን ነገር አስታወስኩት:: እግዚአብሔር ላለፉት ሁለት ዓመታት በብርሃን እኔን የከበበበትን ዘመናት አሰብኳቸው:: እያንዳንዱ ቀን ካመጣው ነገር ጋር በፍጥነት አለፈ:: ዛሬ ምርጫዬን መፈጸም እችላለሁና አምላኬን አመሰግነዋለሁ:: እርሱን እንድመርጥ እና በዚያም እንድጸና አደርጎኛልና::

ተወዳጇ ሳሚያ መጣችና አቅፋ ሳመችኝ። እርሷ ለእኔ እና
ቴም እንቴም ናት። ከዚያ በፊት ተሰምቶኝ የማያወቅ አንዳች የደ
ስታ ስሜት ተሰማኝ። ከልቤ እወዳታለሁ። እርሷንም «እንደ ሌሎቹ
ለምን ነበር የማትፈሪኝ? ደግሞምኮ እኔን ስትቀርቢኝ በሙሉ ጥንካሬ
እና በራስሽ በመተማመን ነበር፤ ክርስቲያኖች እኔን እንዳትቀርቢኝ
ሲያስፈራሩሽ አንቺ ግን ቸል አልሺው፤ ይህንን ሁሉ ጀግንነት ከየት
አገኘሽው» ስል ጠየቅኳት።

ሳሚያ የደስ ደስ ባለው ዓይኗ እያየችኝ «ወደ ሄልሜት ኤል
ዘይቱን ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የመዛወርያው ደብዳቤ ሲደ
ርሰኝ በጣም ነበር የደነገጥኩት። ክርስቲያኖችን ከመጉዳት ፈጽማ
ከማትመለስ፣ ትዕግሥት የሚባል ካልተፈጠረባት፣ እንደ ናህድ ካለች
ዲን ጋር እንዴት መሥራት እችላለሁ? ዋናዋ ርእሰ መምህር ትም
ብትሆን ክርስቲያኖችን የምትጠላ ናት። ጉዳዩ ስላሳሰበኝ ለመጸለይ
በእግዚአብሔር ፊት ቆምኩ። «እባክህ በዚህ ት/ቤት በሚኖረኝ
ቆይታ እርዳኝ» ብዬ ለመንኩት። የማታ ጸሎቴን ጨርሼ ወደ አል
ጋዬ አመራሁ። በሕልሜም ዕብነ በረድ በሚመስል ተዳፋት ላይ ቆሜ
ነበር። የቆመኩበት ቦታ ንጹሕ ቢሆንም ዙርያው ግን ቆሻሻ ነበር።
የቆምኩት ከፍታ ቦታ ላይ በመሆኑ ቆሻሻው ሊደርስብኝ አልቻለም።
አጠገቤ የውኃ ቧንቧ ነበር። ቀጥሎም ንጹሕ ኩሬ ይታያል። ከዚያም
ፓትርያርክ ቄርሎስ መጡ።

አቡነ ቄርሎስ እጅግ የምወዳቸው ቅዱስ ናቸው። ከማረፋቸው
በፊት ብዙ ጊዜ እየሄድኩ እጠየቃቸው ነበር። እርሳቸውም «ሳሚያ
እጅሽን ታጠቢ» አሉኝ። እኔም «እጄኮ ንፁሕ ነው» ስል መለስ
ኩላቸው። እርሳቸው ግን ደግመው «ሂጂና እጅሺን ታጠቢ» አሉኝ።
እኔም እጄን ታጠብኩና ወደ እርሳቸው ተመለስኩ። ይህ ነገርም
ሦስት ጊዜ ተደጋገመብኝ።

ከዚያም ፓትርያርክ ቄርሎስ እጃቸውን አነሡና «ወደ ሄልሜት
ኤል ዘይቱን ት/ቤት ሂጂ፤ በዚያ አንድ የተለየ ተልዕኮ ተሰጥቶሻል»
አሉኝ። ከዕንቅልፌ ስነቃ ጸሐፊ የሆንኩ ይመስለኝ ነበር። እናም ሥራ
ውን ተቀበልኩት። አሁን ልረዳው ያልቻለኩትና በኋላ የሚገለጥልኝ
አንድ ተልዕኮ ይኖረኝ ይሆናል ብዬ አመንኩ። ከአንቺ ጋራ ተቀራ
ርበን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መነጋገር ስንጀምር ወደዚህ ት/ቤት
የተላክሁበት ተልዕኮ አንቺ መሆንሺን ዐወቅኩ። እኔ ፊት በክርስቲ
ያኖች ላይ ትፈጽሚው የነበረውን ክፉ ነገር እና ስላንቺ የሰማሁትን
መጥፎ ወሬ ሁሉ ወደ ጎን ትቼ እወድሽ ነበር።

በመካከላችን ጠንካራ ወዳጅነት ተፈጠረ። ለምን እንደወደድ





ኩሽ አሁን ገብቶኛል። በክርስቶስ ከሚኖር ፍቅር በላይ ጠንካራ ወዳ
ጅነት ወዴት አለ?» አለችና ደግማ አቀፈችኝ። «ልጄ ነሽ፤ ዳግም
ልደትሽን የተቀበልሺው በእኔ እጅ ነው። ይህንን በዓይኔ ለማየት
በመቻሌ ዕድለኛ ነኝ። እንዳንቺ ያለውን ሰው ለማዳን እግዚአብሔር
እኔን በመሣርያነት በመጠቀሙ በረከትን አግኝቻለሁ።» አለች።

ቁልፎቼን ለርእሰ መምህርቷ አስረከብኳት። ከሳሚያ እና ከሞ
ፌድ ጋር ከነበረኝ በጎ ቆይታ በቀር ከዚያ በመውጣቴ የሚፀፀተኝ
ነገር የለም። የፍቅር እመቤት የሆነችውን ድንግል ማርያምን በዚያ
ክፍሌ ውስጥ ማየቴ እና ስሟ በተጠራ ቁጥር በክፍሉ ውስጥ ያውደኝ
የነበረውን ያንን ልዩ መዓዛ አልዘነጋውም። አዲሱ ልደቴ የተጀ
መረው እዚህ ክፍል ውስጥ ነው።

ቢሆንም የትም ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር እንዳለህ አምናለሁ።
ጭቅጭቅ የማታውቀው ንጉሥ ከእኔ ጋር ነህ። ምን ያህል ጠንቃቃ
እንደነበርኩና የነበረኝንም ሀብት ሁሉ አንተ ታውቃለህ። ሁሉን ትቼ
ተከተልኩህ ለማለት አልችልም። ያንን ማለት ብችልማ ኖሮ ምንኛ
ደስ ባለኝ ነበር።

እነሆ የልቤን በር መታህ፤ ድምፅህንም ሰማሁ፤ ላንተ በሬን
ለመክፈት እንድችልም ረዳኸኝ። ወደ ቤቴ ገባህና ከእኔ ጋር ራት
በላህ[24]፤ በልቤ፣ በአእምሮዬ እና በሃሳቤ ለእኔ ሁሉንም ነገር ሆንክ
ልኝ። ስለ እኔ ቆመህልኛል፤ ስለ እኔ ታስባለህ፤ ስለ እኔም ትወስ
ናለህ። እውነታው ይህ ነው። ራሱን ከልቡ ለእግዚአብሔር አሳልፎ
የሰጠ ቢኖር እግዚአብሔር ስለ እርሱ ይቆምለታል። የሚያይበት
ዓይኑ፣ የሚናገርበት አንደበቱ፣ የሚሰማበትም ጆሮው ይሆንለታል።

ከሥራ ለመልቀቅ የሚሟሉትን አንዳንድ ነገሮች ለማጠናቀቅ
ከአሥር ቀናት በኋላ ለመመለስ ተነጋግሬ ከት/ቤቱ ወጣሁ። «ጌታ
ሆይ አንተ ለቃልህ ታማኝ መሆንህን አምናለሁ። ከቀድሞው መኖር
ያዬ ከኤይን ሻምስ ወደ አዲሱ መኖርያዬ ወደ ናስር ከተማ የተዛወ
ረኩት በነሐሴ 1989 ነው። የመልቀቂያ ደብዳቤዬም ቃል በገባህልኝ
መሠረት በነሐሴ 20 ቀን 1989 ዓም ተጠናቀቀ። ምሥጋና ላንተ
ይሁን። በአሥረኛው መንገድ ያለው መኖርያዬ ብዙ ሕዝብ በማይበ
ዛበት አካባቢ የሚገኝ ነው። ብዙዎቹ ቤቶች ባዶዎች ናቸው። እዚህ
እንቅስቃሴዬን ማንም አይከታተልም። ማንም ማን እንደሆንኩ አያ
ውቅም። ከጎረቤቶቼ ጋር ስለማልቀራረብ ማንም አያውቀኝም።

እግዚአብሔር በእኔ አድሮ የሠራውን ሥራ በየቦታው መመስ
ከር ጀመርኩ። በየቤተ ክርስቲያኑ፣ በየገዳማቱ፣ እንዲሁም ሁኔታው

24. ራእይ. 3÷20

በፈቀደበት ቦታ ሁሉ።

በጳጉሜ አራት ቀን 1989 የመልቀቂያ ሂደቱን ለማጠናቀቅ ወደ ት/ቤቱ አመራሁ። ይህ ቀን ለመጨረሻ ጊዜ እዚያ ግቢ ውስጥ የገባሁበት ነው። ወደ ግቢው ስጠጋ ልቤ በጣም ይመታ ነበር። አንተ ግን ጌታ ሆይ መንገዴን ትመራኝ ዘንድ ከእኔ ጋር ነበርክ። ከሥራ የመሰናበቻውን ቅጽ ለመፈረም ወደ ርእሰ መምህሯ ቢሮ ገባሁ። ልክ መግባቴን ስታረጋግጥ በፍጥነት ወጥታ ቢሮውን በላዬ ላይ ቆለፈችና ሙስሊሟን ምክትል ርእሰ መምህርት እና ረዳት ዲኑን ጠርታ ማንም እንዳይገባ በሩን እንዲጠብቁ ነገረቻቸው። ተመልሳ ስትመጣ ልታወርድብኝ ያሰበችው መከራ ከፊቷ ላይ ይነበባል። «መልቀቂያሽን ከመፈረሜ በፊት ስላንቺ የሰማሁት እውነት መሆኑን እና አለመሆኑን ማረጋገጥ እፈልጋለሁ» አለችኝ። እኔም ረጋ ብዬ «ምንድን ነው ስለ እኔ ለማወቅ የምትፈልጊው?» ስል መለስኩላት። «አሁን ክርስቲያን ሆነሻል ወይስ አልሆንሽም?» ስትል ጠየቀችኝ። «ይህንን ነገር የነገረሺን ሰው ራሱን ለምን አትጠይቂውም» አልኳት። ምክትሏም ድምጿን ከፍ አድርጋ «ዙርያ ጥምጥም መሄዱን ትተሽ በቀጥታ መልሽልን» አለችኝ። ከእርሷ በላይ ጮኽ ብዬ «እኔ 47 ዓመቴ ነው፣ የተማርኩና ባለ ዲግሪ ነኝ፣ እናም ማንም በእኔ ሕይወት ውስጥ ጣልቃ እንዲገባ አልፈቅድም» ስል ተናገርኳት።

ምክትል ርእሰ መምህርቷ ወደ እኔ ሮጥ ብላ መጥታ በሁለት እጆቿ እየናጠችኝ «አንቺ በእስልምና እኅቴ ነሽ። እስልምና ደግሞ "ማንም ስሕተትን የተመለከተ ያርመው" ይላል። በመሆኑም በማናቸውም መንገድ አንቺን ማስተካከል አለብኝ» አለች። በዚህ ጊዜ እደ ልቡናዬን ዘርግቼ እግዚአብሔርን «ወደ እኔ ተመልከት፤ እርዳኝም፤ አቤቱ እኔን ለመርዳት ፍጠን»[25] አልኩ። ከዚያም ወደ እርሷ መለስ ብዬ በረጋ መንፈስ «ማነው ይህንን ያለሽ?» ብዬ ጠየቅኳት። ርእሰ መምህርቷ ፈጠን ብላ ወደ እኔ በመቅረብ ነገሩን ልታበርደው ፈለገችና «እስልምናን ከክርስትና ጋር እያነፃፀርሽ በማጥናት ክርስትና ትክክለኛ መሆኑን አረጋገጥሽ ማለት ነው?» ብላ ጠየቀችኝ። እኔም ፈርጠም ብዬ «ፈጽሞ! እኔ እንደዚያ አላልኩም።» አልኳት። እርሷም ቀጠል አድርጋ «ወይስ ቅድስት ድንግል ማርያም ክርስቲያኖችን ማሳደድ እንድታቆሚ ነገረችሽ?» አለችኝ። አሁንም ጠንከር አድርጌ «እኔ እንደዚያ አልተናገርኩም» አልኳት።

በሰጠሁት ምላሽ እግዚአብሔርን ክጄው ይሆን እንዴ? ብዬ

25.መዝ. 69÷2





በማሰብ «በሕልሜ አየሁ ነው ያልኩት» አልኩና ያየሁትን ነገር በዝርዝር ነገርኳት። «ነጭ፣ የሚስብ፣ በትከሻው የወረደ ወርቃማ ፀጉር ያለው፣ ዓይኖቹ እንደ ባሕር ውኃ ሰማያውያን የሆኑ፣ እኔን አነጋገረኝ፤ እኔም ቃል ገባሁለት። እናም በእያንዳንዱ ጉዞዬ ቃሉን በመጠበቅ ላይ ነኝ» ስል አብራራሁላት።

ርእሰ መምህርቷ «እና ማን ነው ልትይ ነው?» ብላ አፈጠጠች። እኔም «መልአከ እግዚአብሔር» አልኳት። ተያይተው ግራ ተጋቡና «አሁን ርግጠኛ ሆንን፣ አነጋገርሽ ግራ የሚያጋባ ነው፤ መልስሽ ጥርጣሬያችንን ግልጽ አደረገልን። በሕይወት መቆየት አይገባሽም፤ ከመንግሥትም ጡረታ ማግኘት አይገባሽም፤ ለሠራሽው ሥራ ዋጋሽን ማግኘት አለብሽ» አሉኝ።

ያን ጊዜ ጥንካሬዬ ጨመረልኝና «ፈርሚ፤ እዚህ ወረቀት ላይ ፈርሚ» ብዬ በርእሰ መምህርቷ ላይ ጮህኩባት። ደንግጣ ወንበሯ ላይ ዘፍ አለች። ከዚያም በፍጥነት መልቀቂያዬን ፈርማ ሰጠችኝ። እኔም ተቀብያት ወደ በሩ ፈጠን ብዬ አመራሁ። እንዳልወጣ ለማገድ ከበሩ ጀርባ አንድ አግዳሚ ወንበር ተጋድሟል። ወንበሩን አሽቀንጥሬ ጣልኩት። ይህንን ዐቅም ከየት እንዳገኘሁት ይገርመኛል። ቀጥዬ ወደ ግቢው በር በሩጫ ተጓዝኩ። ርእሰ መምህርቷ እና ምክትሏ እየሮጡ ይከተሉኝ ነበር። ሊይዙኝ ግን አልቻሉም።

በጥርጣሬ እና በሥጋት ስሜት ተውጬ በመንገድ ላይ ስጓዝ ከርእሰ መምህርቷ እና ከምክትሏ ጋር የነበረኝን ሁኔታ እያሰብኩት ነበር። ያንን ከበባ እንዴት ላመልጠው ቻልኩ? በመንገድ ስጓዝ እያለቀስኩ እና ሕመም እየተሰማኝ ነበር።

ዓይነ ልቡናዬን ወደ እግዚአብሔር አነሣሁና «ጌታ ሆይ ይቅር በለኝ። ደካማ መሆኔን ታውቃለህና። ወደ አንተ እለምንሃለሁና እርዳኝ። ደካማነቴን ይቅር ብለህ ብርታትን አድለኝ።» ብዬ ጸለይኩና ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄድኩ። እዚያ ስደርስ በእግዚአብሔር ዕቅፍ ውስጥ የገባሁ ያህል ተሰማኝ። ያገኘኋቸው ጓደኞቼ «የሆኑ ሰዎች መጥተው ስለ አንቺ ሲጠይቁ ነበር» ብለው ነገሩኝ። ከንግግራቸው የመጣው ሰው ባለሥልጣን እና ክርስቲያን ያልሆነ መሆኑን ገመትኩ። ውስጥ ገብተው እየጠበቁኝ መሆኑንም ነገሩኝ። እኔም ፈጠን ብዬ ወደ ቤቴ ተመለስኩ። ርእሰ መምህርቷና ምክትሏ ያቆሰሉኝ አሁንም ያመኛል። እናም አሁን ደግሞ ሌላ ቁስል የምሸከምበት ዐቅም የለኝም።

በእቅፉ ውስጥ መሆኔን ስለማምን «ምን ማድረግ አለብኝ?» ስል እግዚአብሔርን ጠየቅኩት። እርሱም «ቤትሽን አሁኑኑ ለቀቅሽ

ውጭ» ሲል መለሰልኝ:: ልቤ በሕመም ተመታ:: የት መሄድ እችላለሁ? ሁሉም ሰው ሊያስጠጋኝ ፈቃደኛ አይደለም:: ሁሉም ሲያየኝ ይሸሻል:: ከእኔ ጋር መታየትን ሁሉም ይፈራዋል::

በነጋታው ለሞፌድ ልደውልለት ብዬ ወጣሁ:: የእግዚአብሔር መንፈስ ያደረበት ሰው ስለሆነ እንደተለመደው ሊረዳኝ ፈቃደኛ እንደሚሆን አምናለሁ:: ነገር ግን ምን ያደርጋል ከራስ ፀጉሬ እስከ እግር ጥፍሬ የሚጠዘጥዝ መርዶ ነበር የሰማሁት:: ሞፌድ ተይዞ ታሥሯል:: ሞፌድ ታሠረ? ለምን? ምን ወንጀል ሠርቶ ነው? አቤቱ በምሕረትህ እባክህ ጐብኘው:: ልጅህ መሆኑን ዐውቃለሁ:: ልቤ በስቃይ ተመታ:: ሞፌድ የታሠረው በእኔ ምክንያት ነው ብዬ አዘንኩ:: መልሼ ደግሞ አይ አይደለም ጌታ ሆይ የአንተ ፈቃድ ስለሆነ ነው:: እባክህ አሁንም ያንተ ፈቃድ እንጂ የእኔ አይሁን:: ሁሉም ነገር በእጅህ ነው:: ወደ ቤቴ ብመለስኮ ልቀቂው ነው ያልከኝ::»

በዚህ ዓይነቱ ሃሳብ ስዋኝ ሴቷ ልጄ ልትጠይቀኝ መጣች:: «ፖሊስ ትናንትና ቤታችን መጥቶ ሲፈልግሽ ነበር» አለችኝ:: «ስላንቺ የምናውቀው ምንም ነገር እንደሌለ፣ አድራሻሽንም እንደማናውቅ ነገርናቸው:: ከዚያም ወደ ት/ቤትሽ ሲሄዱ ከሁለት ቀናት በፊት መልቀቅሽ ተነገራቸው:: የት እንደምትኖሪ ማንም እንደማያውቅ ርእሰ መምህርቷ ነገረቻቸው» አለቺኝ::

አዎን ጌታ ሆይ ጥበቃህ እና እረኝነትህ በዙርያዬ ናቸው:: ብርቱው ክንድህ እንደሚደግፈኝ አምናለሁ:: ፖሊሶቹ ት/ቤት የሄዱት ሥራዬን ከለቀቅኩ ሁለት ቀናት እና ቤቴን ከለቀቅኩ በኋላ መሆኑ ያንተን ሥራ ይናገራል:: በዘይቱን የነበረኝን ቤት «ተይው» ስትለኝ «ላንቺ ደኅንነት ሲባል ነው» ያልከኝ ትክክል ነበር:: በት/ቤቱ ያሉት ሁሉ ወደ ዘይቱን መዘዋወሬን ያውቁ ነበር:: ሁሉን ቻይ የሆነው ጌታ ዕቅድ ግን እኔን ጠበቀኝ::

ቄስ ቡትሮስ በቁራጭ ወረቀት ጽፈው የሰጡኝን ቃል አስታወስኩት:: እነዚያ ዘወትር እንዳልረሳቸው የነገሩኝን ቃላት አሰብኩ «ጌታ ያላዘዘውን የሚልና የሚፈጽም ማነው?[26]»

ወደ እስክንድርያ ለመጓዝ ወሰንኩ:: መጀመርያ ግን በትምህርት ሚኒስቴር የሚከናወነውን የጡረታ ሂደት ማጠናቀቅ አለብኝ:: ወደ ትምህርት ቢሮው ልደርስ ስል ደስ የማይል ስሜት ተሰማኝ:: ውስጤ ሰላም ሊኖረው አልቻለም:: ራሴን ለማረጋጋት ሞከርኩና «አንተ ግን አቤቱ ከእኔ አትራቅ፣ አቤቱ ጉልበቴ እኔን ለመርዳት

26. ሰቆ. 3÷37



ከአክራሪ እስልምና ወደ ክርስትና

ፍጠን» የሚለውን የዳዊት መዝሙር[27] በልቤ እየደጋገምኩ መጸለይ ቀጠልኩ:: ነገሮቹ ሁሉ ባልታሰበ ሁኔታ አለቁልኝ:: የቀረኝ ነገር ቢኖር የአገልግሎት ክፍያ ቼክ መቀበል ብቻ ነው[28]:: ገንዘቡ ጊዜ ስለሚወስድ ከሳምንት በኋላ እመለሳለሁ ብዬ ወጣሁ::

ወደ እስክንድርያ ሄጄ ከሳምንት በኋላ እመለሳለሁ ወይም ሴቷ ልጄን እልካትና ትቀበልልኛለች:: ለጉዞው ለመዘጋጀት ወደ ቤቴ ስመለስ ይህ ቀን በዚያ ቤት ለመኖር የመጨረሻዬ ቀን ይሆናል ብዬ አላሰብኩም ነበር:: ይህንን አፓርትመንት ቁልፉን ገዝቼ ለመግባትና ውስጡን ለማስተካከል ብዙ ገንዘብ አውጥቻለሁ:: ተራ ቤት ቢሆንም ለእኔ ግን ተመችቶኝ ነበር:: አሁንም ቢሆን ጌታ ሆይ ያንተ ፈቃድ እንጂ የእኔ አይሁን::

በነጋታው ጠዋት አሥራ ሁለት ሰዓት ላይ ተገናኝተን ከጓደኛዬ ጋር ወደ እስክንድርያ ሄድን:: መንገድ ላይ የአባ ብሶይን ገዳም ለመሳለም ቆም አልን:: ከዚህ በፊት ይህንን ገዳም ለመሳለም መጥቼ ነበር:: በምሥጢር እንደሚጠብቁት ቃል ገብተውልኝ እዚህ ገዳም ለሚኖሩ መነኮሳት ምሥክርነቴን ቀድቼ ሰጥቻቸው ነበር:: ግን ምን ያደርጋል ያ ቴፕ በመላዋ ግብጽ ተባዝቶ ተበተነ:: ያንን ካሴት የሰጠሁትን መነኩሴ በቁጣ ዓይን ተመለከትኩት:: አሁን በእሥር ላይ ያለውን ሞፌድን አሰብኩት:: ሳሚያንስ ምን አድርገዋት ይሆን? ጌታ ሆይ በርግጥ ይህ ሁሉ ያንተ ፈቃድ እንደሆነ አምናለሁ:: ስለዚህም ለምን ሆነ ብዬ ጣልቃ አልገባም:: ሕይወቴን እና ያለኝን ሁሉ ላንተ ሰጥቻለሁ:: በዚያም አንተን ደስ የሚያሰኝህን ሁሉ አድርግ:: አንተ ሩኅሩኅ አባቴ ነህና ላንተ መልካም የሆነውን ነገር ሁሉ እፈጽማለሁ::

እስክንድርያ ስደርስ የተወሰኑ ጓደኞቼ ተቀበሉኝና አጋሚ[29] ውስጥ ወደሚገኝ ቪላ ወሰዱኝ:: አካባቢው ጸጥታ የነገሠበት ነው:: ለዕረፍት መጥተው የነበሩት ተከራዮች በሙሉ ለቅቀውት ስለሄዱ እኔ ብቻ ነበርኩ ያለሁት:: ጓደኞቼ ወደ እስክንድርያ ሲመለሱ እኔ እዚያው ቀረሁ:: ለልጄ ደውዬ ወደ ትምህርት ቢሮው ሄዳ ገንዘቡን እንድትቀበልልኝ ነገርኳት:: አሁን የቀረኝ ነገር ቢኖር እርሱ ብቻ ነው:: እግዚአብሔር ሆይ አሁን ሁለመናዬን በእግርህ ሥር ጥያለሁ: በመከራ ውስጥ ነኝ:: ከባዱን ሸክምም እየተሸከምኩ ነው:: እባክህ እርዳኝ፣ እነሆ ሸክሜን እግርህ ሥር አሳርፌያለሁ:: እባክህን ወደ ዕቅፍህ አስገባኝ:: የዓይኔን ዕንባ የቁስሌንም ደም እባክህ ጥረግ::

ላንተ ክብር ምስጋና ይግባህ:: በችግራችን ወቅት መደገፊያችን

27. መዝ. 21÷19
28. በዚያ ጊዜ ግብፅ ውስጥ የአገልግሎት ክፍያ ማለት የሦስት ወር ደመወዝ ያህል ነው
29. ከእስክንድርያ ከተማ ሃያ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ከሜዲትራንያን ባሕር አጠገብ የሚገኝ መንደር

ነህ:: በዚያች ምሽት በእስክንደርያ ከተማ ያየሁትን ራእይ አልረሳውም:: እኔን በርኅራኄ እያየህኝ ከፊትህ ደም ሲወርድ አየሁህ:: ይህንን ሁሉ የተቀበልከው ለእኔ ብለህ ነው:: ያንን ስቃይህን ዘወትር አስበዋለሁ:: ይቅር በለኝ:: ለእኔ ስትል ምን ያህል መከራ እንደተቀበልክ አውቃለሁ:: እኔም ላንተ ስል መከራን መቀበል ይገባኛል:: እርዳኝ፣ መስቀሉን ተሸክሜ አንተን መከተል እችል ዘንድ ኃይል እና ጽናትን ስጠኝ::

በሳምንቱ ማለቂያ ሴቷ ልጄ ከጓደኞቿ ጋር መጣች:: የአገልግሎት ገንዘቤን ለመውሰድ ወደ ትምህርት ቢሮው ስትሄድ ለእርሷ እንደማይሰጣትና እኔ ራሴ መውሰድ እንዳለብኝ ፐርሶኔሉ የነገራት መሆኑን ገለጠችልኝ:: በትምህርት ቢሮው የሕዝብ ግንኙነት ሥራ አስኪያጅ የሆነችውን እኅቴን እንድትቀበልልኝ ልኬያት ነበር:: ነገር ግን «ናህድ በአገሪቱ የደኅንነት መሥሪያ ቤት ስለምትፈለግና የአስተዳደሩ ዋና ሥራ አስኪያጅም በሰጠው መመርያ መሠረት ገንዘቡን ራስዋ ናህድ እንጂ አንቺ መውሰድ አትችይም» ብሎ እንደመለሳት ነገረችኝ::

እኅቴም ሦስት አማራጮች ያሉት መልእክት በልጄ በኩል ላከችብኝ::

የስለላው ቢሮ ሹም ከሆነው የእኅቴ ባል ጋር ወደ ደኅንነት ቢሮ እሄዳለሁ:: ከዚያም የቤተ መንግሥቱ ፓይለት ከሆነው ከሌላዋ እኅቴ ባል ጋር ሆነን በተሠራጨው ቴፕ ውስጥ ያለው ቃል ውሸት መሆኑን እና ይህንን ለመናገር የቻልኩትም በቄስ ቡትሮስ መሪነት ካህናቱ ጫና ስላሳደሩብኝ መሆኑን መግለጥ፤ ካህናቱ በቴፕ እንድቀዳ ያታለሉኝ መሆኑን ማስረዳት ነው:: ከዚህም በተጨማሪ የመጀመሪያውን የቴፕ ምስክርነት የሚያስተባብል ሌላ ቴፕ እቀዳለሁ:: በዚህ ከተስማማሁ ሰላማዊ መንገድ የሚከፈትልኝ ሲሆን ምንም ዓይነት ችግርም አያጋጥመኝም::

በመጀመርያው ሃሳብ ካልተስማማሁ ደግሞ ሁለተኛው አማራጭ አእምሮዬ ንክ እንደሆነ ተቆጥሬ እኔን ወደ ሥነ አእምሮ ሐኪም ዘንድ በመውሰድ ቤተሰቦቼ ከልጅነቴ ጀምሮ የአእምሮ ችግር እንዳለብኝ ምስክርነት ይሰጣሉ:: በመንግሥት ካድሬዎች ዘንድ ያላቸውን ከፍተኛ ሥልጣን በመጠቀምም ምስክርነታቸው እንዲታመን ያደርጋሉ::

ከእኅቶቼ የአንደኛዋ ባል የአካባቢው መስተዳድር ምክትል አስተዳዳሪ ነው:: የሌላኛዋ ባል ደግሞ በቋንቋ እና ሥነ ልሳን ኮሌጅ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ፕሮፌሰር ነው:: ከእነዚህም በተጨማሪ አንደኛው





ወንድሜ የአደረጃጀት እና ጠቅላላ ሥርዓት ቢሮ ዋና ሥራ አስኪያጅ ነው:: እነዚህ ናቸው እንግዲህ ስለ እኔ የአእምሮ ችግር የሚመሰክሩት::

የመጨረሻው አማራጭ ደግሞ ቤተሰቦቼ ማንም ሳያያቸው እኔን ጠልፈው በመግደል ሊቀብሩኝ ይችላሉ:: ምክንያቱም መጀመርያውኑ ጠፍታለች ብለው ለሚመለከታቸው አካላት ሁሉ በመናገር እያስፈለጉኝ ስለሆነ አላገኘናትም ማለት ብቻ ይበቃቸዋል:: ከዚህም ሌላ ደግሞ በማናቸውም የአውሮፕላን ማረፊያዎች፣ ኬላዎች እና የሕዝብ መሰብሰቢያዎች ሁሉ ፎቶግራፌ ስለተለጠፈ ከሀገር መውጣትም ሆነ ከቦታ ወደ ቦታ መንቀሳቀስ የማይታሰብ መሆኑን አረዳችኝ::

ሃሳቡን ማወጣት ማውረድ ያዝኩ:: እኅቴ ያለችው ሁሉ የምሯን አልመሰለኝ አለኝ:: ርግጠኛ ናት? ወይስ ልታታልለኝ ፈልጋ ነው? አግኝቻት ነገሮችን ሁሉ ላረጋግጥ ፈለግኩ:: እውነትም በስልክ ስንገናኝ የመጀመርያዎቹን ሁለት ዕድሎች ካልተጠቀምኩ የሚጠብቀኝ ሦስተኛው መሆኑን እየማለች ነገረችኝ:: በደኅንነት ቢሮው የሚሠራው ባሏም በ48 ሰዓታት ውስጥ አስይዞ የሚፈልገውን ሁሉ በኃይል እንደሚያስደርገኝ ዛተ::

እነዚህ ሁሉ ደጋግ ልቦች እንዴት ባለ ፍጥነት ተቀይረው
ጨካኞች ሆኑ?
ዓለም ከመርፌ ዓይን ይልቅ ጠበበችብኝ:: እጅግ ከማዘኔ
የተነሣ ሞትን ተመኘሁ::
ያለሁበትን ቤት ያከራዩኝ ሰዎች የሆነውን ሁሉ ሲያውቁ እኛም
ችግር እንዳይፈጠርብን ቤቱን ልቀቂልን አሉኝ::

የት ልሂድ?

# ምዕራፍ ስድስት
# አደን ተጀመረ

*ጌታ ሆይ ለፈተና አጋልጠህ አትሰጠንም፤ ብቻችንን እንድንሆንም አትተወንም፤ ከመከራው ጋር መውጫውን አብረህ ታዘጋጅልናለህ እንጂ።*

ኢንጂነር ሳሚር የደረሰብንን ችግር በመስማቱ ማእምራህ[30] በተባለ ቦታ ወደሚገኝ ሌላ አፓርትመንት እንድንዛወር ለማድረግ እየጣረ መሆኑን ሴቷ ልጄ ነገረችኝ። በአሁኑ ጊዜ የመዝናኛ ወቅቱ ስላለፈ በአካባቢው ማንም አይኖርም። ስለዚህም ማንም ስለማያውቀኝ በሰላም እኖራለሁ ብዬ አሰብኩ። ሳሚር መጣና ወደ ቦታው ወሰደኝ። እዚያም እንደተለመደው እኔን ትተውኝ እነርሱ ወደ ካይሮ ተመለሱ። እግዚአብሔር ብቻ አብሮኝ ነበረ።

ከሦስት ቀናት በኋላ የእግዚአብሔር ድምፅ ቀሰቀሰኝ። የሳሚርን አፓርትመንት በአስቸኳይ ለቅቄ መውጣት እንዳለብኝም ነገረኝ። ደነገጥኩና «ለምን ጌታ ሆይ? ደግሞስ የት እሄዳለሁ» ብዬ ወደ እግዚአብሔር ጮህኩ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሴቷ ልጄ ደወለችልኝና «ሳሚርን የመንግሥት የደኅንነት ኃይሎች ስለያዙት ቤቱን በአስቸኳይ ልቀቂ» ስትል ነገረችኝ። ምን ላደርግ እችላለሁ? የትስ መሄጃ አለኝ?

ወዲያውም እግዚአብሔር መልሱን ሰጠኝ። «ወደ ገዳም ሂጂ፤ እዚያ መፍትሔውን ታገኛለሽ» አለኝ። እኔም ወደ ገዳሙ አመራሁ። እዚያ ያገኙኝ አባት እኔን በሕይወት በማየታቸው ተደሰቱ። «እግዚአብሔር ወደዚህ እንዲያመጣሽ እየለመንኩት ነበር» አሉኝ። ቀጠል አድርገውም «አንድ ወንድማችን የደረሰብሽን ስለ ሰማ የቤቱን ቁልፍ ሰጠን። ቤቱ የሚገኘው በእስክንድርያ ከተማ መካከል ሲሆን ከፍታው ላይ ሆኖ ባሕሩን የሚያሳይ ነው። ተከራዮቹ የሚፈልጉት በበጋው ጊዜ ብቻ በመሆኑ አሁን እዚያ ማንም የለም። አካባቢው በበጋ ለመዝናናት ለሚመጡ ቱሪስቶች የመቆያ ሥፍራ በመሆን ነው የሚያገለግለው። የምትፈልጊውን ጊዜ ያህል መቆየት እንድትችይ ፈቅዷል» አሉኝ።

ጌታ ሆይ በእያንዳንዷ እስትንፋሴ ቁጥር ባከብርህም እንኳን፣ ብመሰግንህም እንኳን ላንተ ጥበቃ ግን ውለታውን ለመክፈል አልችልም። እስከ ሕይወቴ ፍጻሜ እንኳን በፊትህ ብንበረከክ ለውለታህ በቂ አይሆንም። «ትሰብራለህ፣ ትጠግናለህም፤ ታቆስላለህ፣ እጆችህም ይፈውሳሉ[31]»

እኒያ አባት ለሁለት ቀናት ያህል በካልዩብ[32] ከሚገኙት ቤተሰቦቻቸው ጋር እንዳሳልፍ ጋበዙኝና ሄድኩ። የልጆቼን ሁኔታ ለማወቅ በየጊዜው እደውልላቸው ነበር። አንድ ቀን ትንሿ ልጄ «በጎረቤታችን ስልክ አትደውይልን፤ እዚያ ሆነን አንቺን ለማናገር እናፍራለን» አለችኝ። እናም በታናሽ እኅቴ ስልክ እንድደውልላቸው አሳሰበችኝ። የልጄ ሃሳብ አላስደሰተኝም። ለምን እንደዚያ ማድረግ ፈለጉ? ጎረቤታችን ጥሩ ሰው ናት። ልጆቿም እንደርሷው ጥሩዎች ናቸው። ለልጆቼ በደወልኩ ቁጥር እነርሱን ለማገናኘት አቅማምታ አታውቅም። ልጄን «የሆነ ተንኮል ልትሠሩ ነው አይደል?» ስል ጠየቅኋት። እርሷም ምንም ክፋት የሌለበት እንደሆነና ከመጠን በላይ ተጠራጣሪ በመሆኔ ያለመደሰቷን ነገረችኝ። ስለዚህም በእኅቴ ቤት ስልክ ልደውልላቸው ቀጠሮ ያዝኩ።

የደወልኩት ከካህኑ ቤት ነበር። ወንዱ ልጄ የእኔን ደኅንነት አጥብቆ ለማወቅ የፈለገ ይመስል ሰላምታውን አስረዘመው። እኅቴ ልትረዳኝ ብትፈልግም ከመጠን ያለፈ ለዘብተኛነት አየሁባት። የስልኩ ውይይት ከአስራ አምስት እስከ ሃያ ደቂቃ ባለው ጊዜ ውስጥ አበቃ። ወዲያው የእግዚአብሔር ድምፅ «ይህ ወጥመድ ነው» ሲለኝ ተሰማኝ. «አንቺን አጭበርብረው ያለሽበትን ቦታ ስልክ ለማወቅ የሠሩት ተንኮል ነው» አለኝ።

ከግማሽ ሰዓት በኋላ አንድ የሆነ ሰው ደወለና «ከውጭ ሀገር ለዚህ ስልክ ባለቤት በፖስታ ዕቃ ስለተላከለት የባለቤቱን ስም እና አድራሻ ለማወቅ ፈልጌ ነው» አለና ጠየቀ። ደዋዩ የተላከው ፖስታ ስም እና አድራሻ ሳይሆን የቤቱ ስልክ ብቻ እንደተጻፈበት ገለጠ። ወዲያውኑ ትንሿ ልጄ በእኅቴ ስልክ እንድደውልላቸው ለምን እንደ ፈለገች ገባኝ። የእኅቴ ባል ከቤተ መንግሥቱ ጋር ግንኙነት ያለው ሰው በመሆኑ የካህኑን አድራሻ በስልኩ አማካኝነት በቀላሉ ለማግኘት ይችላል። ጌታ ሆይ እንዴት ያሉ ክፉዎች ናቸው። የሚፈልጉትን መረጃ በተለመደው መንገድ ለማግኘት ሰዓታት አይፈጅባቸውም። እናም ከዚህ ቦታ በአስቸኳይ ለቅቄ መውጣት እንዳለብኝ ገባኝ።

ቶሎ ብዬ ከዚያ አካባቢ ወጣሁ። ልቤ በኀዘን ተመቷል። እኅቴ፣ ወንዱ ልጄ፣ እና ትንሿ ሴት ልጄ ከደኅንነቶች ጋር ተባብረው ወጥ

30. ማእምራህ የእስክንድርያ ከተማ የመዝናኛ መንደር ነው።

31. ኢዮብ. 5÷18

32. ካልዩብ በታኅታይ ግብጽ ከካይሮ ሰሜን 25 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኝ ከተማ

መድ አጠመዱልኝ ማለት ነው። ወንዱ ልጄኮ ዕድሜዬን በሙሉ የምወድደው ልጄ ነበር። የምወዳት ትንሽዋ ልጄ እና እኅቴ - ይህንን ሳስበው ራሴን ልስት ምንም አልቀረኝም። የተፈጸመውን ሁሉ ማመን አልቻልኩም። ነገር ግን «ወንድምም ወንድሙን፣ አባትም ልጁን አሳልፎ ይሰጣል፤ ልጆችም በወላጆቻቸው ላይ ይነሣሉ፤ ይገድሏቸውማል፤ በሁሉም ስለ ስሜ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ። እስከ መጨረሻው የሚጸና እርሱ ይድናል[33]» የሚለውን አስታወስኩ።

ወደ ገባሬ ተአምራት ማር ሚና ገዳም ሄድኩ። ለማንም ስለ ማንነቴ ሳልናገር እዚያ ሦስት ቀናት ተቀመጥኩ። ገዳሙ ከካይሮ ደቡብ ምዕራብ 60 ኪሎ ሜትር ይርቃል። በየቀኑ ለቅዳሴ በጠዋት እነሣለሁ። ሥጋወ ደሙንም እቀበላለሁ። ቀሪውን ጊዜ ደግሞ በጸሎት አሳልፈዋለሁ። በዚህም ራሴን ለማረጋጋትና ለማጽናናት ቻልኩ።

በአራተኛው ቀን የኒያ የካህኑ ወንድም ሊወስደኝ ሲመጣ ገረመኝ። እኔም «ፖሊሶች ስምህን እና አድራሻህን እንደማያውቁ ርግጠኛ ነህ?» ስል ጠየቅኩት። «ኧረ ፈጽሞ! ፖሊስ ጨርሶ ሊመጣ አይችልም። ምናልባት ከፍርሃትሽ የተነሣ ነገሮችን በሃሳብሽ የምትስያቸው ይመስለኛል። በይ ተነሽና እንሂድ፤ የተወሰነ ቀን ከቤተሰባችን ጋር ታሳልፊያለሽ» አለኝ። ነገሩን በዚህ መልኩ ማቃለሉ እና አገላለጡ አልተመቸኝም። እናም «ምን ማድረግ ይሻለኛል?» ብዬ አሰብኩ። ምርጫ የለኝም። ዕቃዎቼን ሰብስቤ ወደ መኪናው በመሄድ ላይ እያለሁ «ይህ ሰው የመጣው ለፖሊስ አሳልፎ ሊሰጥሽ ነው» የሚል የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰማሁ። እናም ከድንጋጤዬ ብዛት ብርክ ያዘኝ። «ጌታ ሆይ ምን ላድርግ? ልተወውና ወደ እስክንድርያ ልሂድ? መወሰን አቃተኝኮ» አልኩት።

ከልጁ ጋር በመኪና መጓዝ ጀመርን። በመንገድ ላይ እያለን በልቤ «በእጃቸው መውደቅን አልሻም፤ ርኅራኄ የሌላቸው አራዊት ናቸው። ለእነርሱ አሳልፈህ ትሰጠኛለህን?» እያልኩ እጸልይ ነበር። እግዚአብሔርም «አትጨነቂ፤ በትክክለኛው ጊዜ አድንሻለሁ፤ ያን ጊዜም ሁሉም ሥራዬን ዐውቀው ስሜን ያከብራሉ።» አለና መለሰልኝ። እኔም «ጌታ ሆይ ደካማነቴን ርዳኝ፣ ይቅርም በለኝ። የምታድነኝ ከሆነ እባክህን ምልክትን ስጠኝ። እጅግ በጣም ፈርቻለሁና» አልኩት። ወዲያውኑ ደመናት ፀሐይን ጋረዷት። ዝናምም ዘነመ። «እባክህን ደመናው ይገለጥ፣ ዝናቡም ይቁም» ስል እኔም አምላኬን ለመንኩት። ዝናቡ ሲያቆም ደቂቃ አልወሰደም። ደመናውም ተገለጠ። ፀሐይም በድጋሚ ወጣች። እኔም እግዚአብሔርን አመሰገንኩት።

33. ማቴ. 10÷21-22





ልጁ መኪናውን የሚነዳው ቀስ ብሎ ነው። በካይሮ/ እስክንድርያ የበረሃ ጎዳና ላይ ከ40–50 ኪሎ ሜትር በማይል ነበር የሚያበረረው። በየደቂቃው ደግሞ በስፖኪዮው ወደ ኋላ ያያል። የሚያደርገውን ነገር የማልከታተለው መሰልኩ። ከዚያም «ቀስ ብለህ ለምን ትነዳለህ?» ስል ጠየቅኩት። «መኪናው የቴክኒክ ችግር ስላለበት በፍጥነት ብነዳው እዚህ በረሃ ውስጥ ተበላሽቶ ይቀራል ብዬ ነው» አለኝ። በዚያ ሰዓት «ከአባ ብሶይ ገዳም ስትደርሱ አስቁሚውና ሥራዬን ታያለሽ» የሚል የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰማሁ። እንደተባልኩት ከአባ ብሶይ ገዳም እርሻ ጋ ስንደርስ «አቁምልኝ» አልኩት። መጀመርያ እምቢ ሊለኝ ሞከረ፤ ነገር ግን ደጋግሜ ስጨቀጭቀው ለጥቂት ደቂቃዎች ሊያቆምልኝ ተስማማ።

እዚያ ስደርስ ያጋጠመኝ ነገር የሚገርም ነው። መነኮሳቱ ሁሉ በካህኑ ቤት የደረሰውን ችግር ያውቃሉ። «የት ነበርሽ? ፖሊስ በእኩለ ሌሊት መጥቶ የካህኑን ቤት እንደ በረበረና ያገኘውን ሁሉ እንዳሠረ ታውቂያለሽ?» ሲሉ ጠየቁኝ። አስቀድሜ የገመትኩት ነገር ቢሆንም አስደንጋጭ መርዶ ነበር። የካህኑን ወንድም በጥላቻ ዓይን አየሁት። እርሱም «ይቅር በይኝ፤ ሽማግሌውን ካህን በጭካኔ ሲመቷቸው ስላየሁ ተፈተንኩ» አለኝ። እኔም «እኔ ይቅር ብዬሃለሁ፤ እግዚአብሔር ይቅር ይበልህ» አልኩት።

አሁን ግን መሄድ ያለበት ብቻውን ነው። «ፈጽሞ ብቻዬን አልሄድም እባክሽ አብረሽኝ ነይ» ሲል ለመነኝ። «አእምሮ ቢስ መሰልኩህ እንዴ? ራሴን በራሴ አሳልፌ እንድሰጥ ትፈልጋለህ? አንዱ ያንተ ወንድም ምስክርነቴን በቴፕ እንድቀዳው፣ ስሜን እና አብረውኝ የነበሩትን አብሬ እንድቀዳ አደረገኝ። ያም መረጃ በገዳሙ ቤተ መጻሕፍት ውስጥ በምሥጢር እንደሚጠበቅ ቃል ገባልኝ። በቀጣዮቹ ቀናት ግን በመላው ግብፅ ተሠራጨ። ያ ሳያንስ አንተ ደግሞ በፈቃዴ እጄን ለፖሊስ እንድሰጥ ልታግባባኝ ትሞክራለህ» አልኩት።

እንዴት የተምታታ ነገር ነው። እያንዳንዷን የክፋት ጽዋ በመጎንጨት ላይ ነኝ። በኃይለኛ ጥፊ የተመታሁ ያህል ነው ያመመኝ። አንድ ሰው በሌላ ሰው ሲከዳ ምን ሊሰማው እንደሚችል ተረዳሁት። ጌታ ሆይ በማንም ላይ እየፈረድኩ አይደለምና እባክህን ይቅር በለኝ። ከአንተ ዘንድ ረድኤትን ካላገኘን በቀር እኛ ደካሞች ነንና። ያለ አንተ ረድኤት ማንንም ልንቋቋም አንችልም። ከደቀ መዛሙርትህ አንዱ በከዳህ ጊዜ የተሰማህን አሁን እኔም ቀመስኩት። ከመከራህ ጥቂቷን እንድቀምሳት አደርገህኛልን የተመሰገንክ ሁን።

አሁን ምን ባደርግ ጥሩ ነው?

በአባ ቢሾይ ገዳም የሚገኙት መነኮሳት ሁሉ መጡና ከበቡኝ:: ከመካከላቸው አንዱ «ለፖሊስ እጅሽን መስጠት አለብሽ፤ መሸሹ አያዋጣሽም:: ከበባው እየጠበበብሽ ነውና ማምለጫ አይኖርሽም» አሉኝ:: ሌላውም ቀበል አድርገው «በአንገትሽ ዙርያ ደም ተነክረሽ በሕልሜ አይቼሻለሁ፤ ትርጉሙም ለመገደል የታሠርሽ መሆኑን ያመለክታል» አሉኝ፣ ሦስተኛው ደግሞ «ስለ ክርስቶስ ብለሽ ሰማዕትነት መቀበልን አትፈልጊም እንዴ? እርሱኮ ኑ እናንተ የአባቴ ብሩካን ዓለም ሳይፈጠር የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ ብሏል» ብለው ጨመሩበት:: ሁሉም ቢላዋ ይዘው ያለ ርኅራኄ ሊያርዱኝ የከበቡኝ መሰለኝ::

እኔ ያን ጊዜ ለራሴ «ምናልባትምኮ እውነታቸውን ይሆናል:: እጄን መስጠት ሳይኖርብኝ አይቀርም» በዬ አሰብኩ:: የእጅ ቦርሳዬን ከፈትኩና የያዝኩትን ሁሉ ለመነኮሳቱ ሰጠኋቸው:: እጄን ለመስጠትም ወሰንኩ:: መጀመርያ ግን ወደ እስክንድርያ መሄድና ንብረቴን መሰብሰብ አለብኝ:: ምክንያቱም በዚያ ያሉትን ዶክመንቶች ፖሊስ ካገኛቸው ነገሩ ሊከርብኝ ይችላል:: ደግሞም ከእኔ ጋር ለመሆን የመጣችውን ትልቋን ልጄን ወደ አባቷ እንድትሄድ በማድረግ እኔን ከሚጠብቀኝ መከራ እንድታመልጥ ባደርጋት መልካም ነው:: መቼም በመንግሥት የደኅንነት ኃይሎች ሊደረስብኝ የሚችለው ነገር የዋዛ አይሆንም:: ነገር ግን ከእሳቱ ጉድጓድ ሠለስቱ ደቂቅን ያዳነ እግዚአብሔር እኔንም እንደሚያድነኝ አምናለሁ:: ደግሞስ ለምን አያደርገውም? እኔኮ ለእርሱ ብርቅዬ ልጁ ነኝ::

የካህኑ ወንድም ትቶኝ ለብቻው ሄደ:: እኔ ግን በካይሮ/ እስክንድርያ የበረሃ ጎዳና አጋማሽ በሚገኘው የእንግዳ ማረፊያ ከታላቋ ሴት ልጄ ጋር መቆየት ፈለግኩ:: መቼም አንዱን የከባድ መኪና ሾፌር ብንለምነው ሳይወስደን አይቀርም:: ወደ እስክንድርያ ለመሄድ ለአንድ ሰዓት ያህል ታክሲ ጠበቅን:: ከዚያም የግሬይሃውንድ አውቶቡስ ቆመልንና ወደ እስክንድርያ ወሰደን::

መንገድ ላይ በልቤ «እግዚአብሔር ሆይ ይህ መጨረሻዬ ነውን? እውን ለመንግሥት የደኅንነት ኃይሎች እጄን መስጠት አለብኝን? እነርሱን አንተ ከእኔ በላይ ታውቃቸዋለህ:: የጭካኔያቸውን መጠን ታውቀዋለህ:: እኔ ግን ያንን መቋቋም የማልችል ደካማ ነኝ:: እባክህን በሚደርስብኝ መከራ ምክንያት እንዳልዳከም እርዳኝ::» እያልኩ እጸልይ ነበር:: እርሱም ወዲያውኑ ድምፁን አሰማኝ:: «እጅሽን እንድትሰጭ ብፈልግ ኖሮ አሳልፎ ሊሰጥሽ መምጣቱን አልነግርሽም ነበር:: የገዳሙን እርሻ እንድትጎበኝ የነገርኩሽም እዚያ እውነቱን እንድትረጅ ብዬ ነው:: እንዲሁም አሳልፌ እንደማልሰጥሽ ምልክት ልሰጥሽ ብዬ ነው:: ፈጽመሽ እጅሽን አትስጭ፤ ወደ እስክንድርያ ሂጅና





እዚያ ጠብቂ» አለኝ::

እስክንደርያ ስደርስ በጣም ደክሞኝና ታክቶኝ ነበር:: ያንተ ሰላም ግን አእምሮዬን ሁሉ የሚያልፍ ነው[34]:: መኖርያዬን ወደ ሌላ ቦታ መቀየር አለብኝ:: ምናልባት አንዱ አድራሻዬን ነግሯቸው ሊይዙኝ ይመጡ ይሆናል እያልኩ በሃሳብ ስላጋ ያንን ሌሊት በዚያው ቤት እንዳሳልፍና ጠዋት ሌላ ቤት እንድፈልግ እግዚአብሔር መራኝ::

በነጋታው አንዲት የተሟላች ክፍል ወዳለቻቸው ክርስቲያን ቤተሰቦች እግዚአብሔር መራኝ:: በዚያው ቀን ያንኑ ክፍል በሊዝ ተከራየነው:: በዚያ ቦታ ረዘም ላለ ጊዜ መቆየት እንድችል ለአከራዮቼ ስለ ማንነቴ አልነገርኳቸውም:: ካይሮ ደውዬ ጓደኞቼን ጠራኋቸው:: አንደኛው ድምፄን ሲሰማ ማመን አልቻለም ነበር:: «እውነት አንቺ ናህድ ነሽ? ፈጽሞ ማመንኮ አቃተኝ፤ የመንግሥት የደኅንነት ኃይሎች አግኝተውሽ እንደ ገደሉሽ ሰምተን ነበር:: ወደ አንቺ መጥተን እስክናይሽና የሆነውን ሁሉ ካንቺ እስክንሰማ እባክሽን ካለሽበት ቦታ ወደ ሌላ አትሂጅ» አለኝ:: እንዳለውም ለአስቸኳይ ጉዳይ ካልሆነ በቀር ከቤቴ አልወጣም ነበር::

አንድ ቀን የቤቱ አከራይ የክፍሌን የመጥሪያ ደወል ደወለች:: ወደ ውስጥ እንድትዘልቅ ስጋብዛት «በኢየሱስ ክርስቶስ አምና ክርስቲያን ስለ ሆነች ሙስሊም ሴት ሰምተሻል? ስሟ ናህድ ይባላል::» አለችኝ:: እኔም በፍርሃት ተውጬ ስለ እርሷ መስማቴን ነገርኳት:: እርሷም በደስታ ተውጣ «ክርስቶስን እንዴት በራእይ እንዳየችውና እንዴት እርሱ እንዳነጋገራት የሰጠችውን የምስክርነት ካሴት ገዝተነዋል» አለችኝ:: «ታድያ አመንሻት» ስል ጠየቅኳት:: «አዎ ያለ ጥርጥር:: ያንን የመሰለ ሥልጣን፤ የትምህርት ደረጃ ያላት፤ ያንን ከመሰለ ታላቅ ቤተሰብ የተወለደች ሴት እንዴት በውሸት ታሪክ ራስዋን ለመከራ አሳልፋ ትሰጣለች ብለሽ ነው:: ያየችው ነገር እውነት ካልሆነ በቀር» አለችኝ::

አምላክ ሆይ ክብር ምስጋና ይግባህ:: ይህንን መስማት ብቻ ለእኔ በቂዬ ነው:: የኔን ጽድቅ ሳይሆን፣ መጠን የሌለውን ክብርህን በእኔ ለመግለጥ ወድደህ ስለ መረጥከኝ አመሰግንሃለሁ:: ዛሬም ዘወትርም በእስትንፋሴ ቁጥር ልክ አመሰግንሃለሁ:: አብረን ወደ እርሷ ቤት ገባንና የምስክርነቱን ቴፕ አዳመጥነው:: ነገሩን ለመጀመርያ ጊዜ የሰማሁ ሰው መሰልኩ:: እኔ ግን እያንዳንዷን ነገር በዓይነ ኅሊናዬ እመለከታት ነበር::

ሲያልቅ «ፖሊስ እስክንድርያ ከተማ መሆንዋን ደርሶበት እየፈ

34. ፊልጵ.4÷7

ለጋት ነው አሉ» አለችኝ::

አሃ!እስክንድርያን ለቅቄ የሆነ ቦታ መሄድ አለብኝ ማለት ነው:: ይሁን እንጂ የሚረዳኝ ሰው እስካገኝ ድረስ መጠበቅ ነበረብኝ:: ከሁለት ቀናት በኋላ የማምነው አንድ ጓደኛዬ ሊጎበኘኝ መጣ:: ሲያየኝ ዓይኑን ተጠራጠረው:: «አንቺ በእኅትሽ ቤት ለልጆችሽ ስልክ እንድትደውይ ያደረገው ያለሽበትን ቦታ ለመለየት ሲል የመንግሥት የደኅንነት ኃይል ነውኮ:: እናም የስልኩን ባለቤት ስም እና አድራሻ ሲያገኙ በእኩለ ሌሊት ፖሊስ አካባቢውን ከብቦ መመንጠር ጀመረ:: አንቺን በቦታው ሲያጡሽ ያገኙትን ሁሉ አሠሩ:: ያለርኅራኄ ሁሉንም መግረፍና ማሰቃየት ጀመሩ:: በዚህ ምክንያት የቄስ ቡትሮስ ወንድም መከራውን መቋቋም ስላልቻለ አንቺን አሳልፎ ለመስጠት አሰበ:: ወደ ማር ሚና ገዳም በመጓዝ አንቺን አምጥቶ ሊሰጣቸው ተስማማ:: አንቺን ያሳፈረበት መኪና በሚከታተሉት ሁለት የደኅንነት መኪኖች ታጅቦ ነበር:: አባ ብሶይ ገዳም እንደ ደረሳችሁ ስትቆሙ አልፈዋችሁ ሄዱና ጠበቋችሁ::

ልክ የልጁ መኪና በዋናው መንገድ ላይ መጓዝ ሲጀምር ተከተሉትና አብረውት ሄዱ:: አንቺና ልጅሽ መኪናው ውስጥ ያላችሁ መስሏቸው ነበር:: የካይሮ መግቢያ ኬላ እስኪደርስ ድረስ ተከተሉት:: ለአንድ ሰዓት ተኩል ያህል ከአንቺ ርቀው ከነዱ በኋላ ነበር በመኪናው ውስጥ ያለመኖርሽን የተረዱት::

የመንግሥት ደኅንነቶች መንገዱን ሁሉ ዘግተው ወደ ካይሮ የሚገቡ መኪኖችን ሁሉ መፈተሽ ጀመሩ:: በፍተሻ እንዳላገኙሽ ሲያውቁ ወደ አባ ብሶይ ገዳም እርሻ ተመለሱና ፍለጋቸውን አጧጧፉት:: በዚያ ሲያጡሽ ደግሞ ከፖሊስ ልታመልጥ ስትሸሽ ተገደለች ብለው አስወሩ ማለት ነው:: አብሮሽ የነበረው ያ ልጅም በእሥር ቤት በመሰቃየት ላይ ይገኛል::»

ሳሚር አፓርትመንት እንድታገኝ ረድተሃታል ተብሎ ታሥሯል:: ያንቺን የምስክርነት ቴፕ ሲያባዛ የተገኘ አንድ ሰውም እንዲሁ ታሥሯል:: ያንቺ ሴት ልጅ ጸሐፊው ሆና ትሠራ ስለነበር እና አንቺንም በገንዘብ ስለረዳሽ ኢንጂነር ራሽድም ታሥሯል:: ሁሉም ክርስትናን በመስበክ እስልምናን እንድትቀይሪ አድርገዋል በሚል ወንጀል ተከስሰዋል[35]:: አሁን ከእጃቸው እንዳመለጥሽ ስላወቁ በእስክንድርያ ከተማ፣ በካይሮ እንዲሁም በመግቢያና መውጫ በሮች መንገድ እየዘጉ ፍተሻቸውን አጠናክረዋል» አለና የራሴን ታሪክ አጫወተኝ::

35. በእስልምና ሀገሮች እስላምን ሰብኮ ክርስቲያን ማድረግ በወንጀል ያስቀጣል::





እስክንድርያን ለቅቄ ካይሮ ለመግባት ወሰንኩ:: ሁሉንም ለእኔ እንደሚሆን አድርገህ የምታከናውን አንተ ነህ:: አንዷ ጓደኛዬ በእርሷ አፓርትመንት እንድቆይ ጋበዘችኝ:: ዕቃዬን ሰብስቤ ወደ ካይሮ አመራሁ::

የእስክንድርያ መውጫ መንገድ ለፍተሻ ተዘግቷል:: ከከተማው የሚወጡትን መኪኖች ሁሉ የደኅንነት ኃይሎች እያስቆሙ ይፈትሻሉ:: የኛ ተራ ደረሰና ኬላው ላይ ቆምን:: አንዱ ፈታሽ ዝቅ ብሎ እንኳን በመኪናው ውስጥ ምን እንዳለ ሳያይ «እለፉ» አለን:: መንገዳችንን እየመራህ ከፊታችን አንተ ከሄድክ ማን ሊያስቆመን ይችላል?

ካይሮ ደረስንና ወደ ሄልዮፖሊስ[36] አመራን:: የምንሄድ በትቤት በኑዝሃ አካባቢ ከሚገኘው የፖሊስ ጣቢያ አጠገብ ነበር:: እዚያ ሁሉም ያውቁኛል:: ስለሆነም መስኮቴን መክፈት፣ ከቤቴ ወጣ ማለት፣ ትንሽ እንኳን ድምፅ ማሰማት፣ ሌላው ቀርቶ በር መክፈት እንኳን አልችልም ነበር:: ምክንያቱም በዚያ አፓርትመንት ተከራይ መኖሩ መታወቅ የለበትምና::

በዚያ የሚገኙ ሁሉ ያ ቤት ባዶ መሆኑን እና ማንም በውስጡ እንደሌለበት ነው የሚያውቁት::

36. ሄልዮፖሊስ በሰሜን ካይሮ የሚገኝ ክፍለ ከተማ ነው::

# ምዕራፍ ሰባት
# ስደት

ቀናቱ ቀርፈፍ እያሉ ነበር የሚያዘግሙት:: ከባድ የሆነ ጭንቀት ተጫጭኖኛል:: ታላቋ ልጄ አብራኝ አለች:: አብረን ከግብጽ ለመውጣት ወስነናል:: በዚያ ቤት ውስጥ እያንዳንዱን ቀን በረሃብ ነበር ያሳለፍነው:: እንዲያም ተርበን እንኳን ከዚያ ቤት መውጣት አንችልም ነበር:: በዚያ የተደበቅንበትን መጋረጃ መግለጥ አደጋ ነው:: አንድ ሰው ማታ መጥቶ ምግብ እስኪጥልልን በትዕግሥት መጠበቅ ነበረብን:: አንዳንዴ ምግብ የሚያመጣልን ሰው ለሁለት ቀናት ያህል ለሥራ ወደ ሌላ ቦታ ይሄዳል:: እኛም ረሃቡን ችለን እርሱን መጠበቅ ግዴታችን ነበር:: በዚያ ቦታ ከትዕግሥት በቀር ምንም ነገር ማድረግ አንችልም ነበር:: በዚህ መልኩ ዐርባ ቀናት አለፉ:: ምናልባት ለሠራሁት ኃጢአት እግዚአብሔር እየቀጣኝ ይሆናል ብዬ አሰብኩ:: ጌታ የሚወደውን ይቀጣልና[37]::

«ጌታ ሆይ ይቅር በለኝ:: በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በድዬህ ይሆናልና፤ ደግሞስ እንዲህ ያለውን መከራ እስከመቼ ነው የምሸከመው» እያልኩ እጸልይ ነበር:: እሥር ቤት ያለሁ ያህል ነበር የሚሰማኝ:: በዚህ መካከል አንዱ ጓደኛዬ ከሀገር ለመውጣት የሚያስችሉ ሁለት ፓስፖርቶች ሊያገኝልኝ እንደሚችል ቃል ገባልኝ:: እኔም እግዚአብሔርን «በዚህ ሁኔታ መቀጠል አልችልምና እባክህን ርዳኝ» ብዬ ለመንኩት:: የእግዚአብሔርም ድምፅ «ከመጀመርያው ጀምሮ የነገርኩሽን አላስተዋልሽምን፤ ወደ እኔ ተመልከች፣ አያሌ ጊዜ ከመከራ አውጥቼሻለሁ፤ አንቺ ግን አሁንም ትፈሪያለሽ፣ ፈራሽ በስባሽ በሆኑ ሰዎችም ትተማመኛለሽ፤ አሁንም ተነሽና ውጭ፤ እኔ ላንቺ ፓስፖርትሽን አዘጋጅልሻለሁ:: በአዲስ ስምም ወደ ውጭ ትወጫለሽ» አለኝ:: «ይህ ሰውኮ ከጊዜ በፊት ቃል ገብቶልሽ የነበረ ሰው ነው:: ነገር ግን የምስክርነትሽ ካሴት በሰፊው ሲሠራጭና ነገሩ ከቁጥጥር ውጭ ሲሆን ፈራና ካንቺ ራቀ:: አሁንም ይህንን ሥራ እንዲሠራልሽ ኃይል እና ጽንዐት እሰጠዋለሁ:: አይዞሽ አትፍሪ፤ ሰላሜ ካንቺ ጋር ነው:» አለኝ::

ጌታ ሆይ ይቅር በለኝ:: ደካማ ነኝና:: ድካሜን አበርትተህ ኃይ

37. ዕብራ.12÷6





ልህን አድለኝ:: በነጋታው የእግዚአብሔርን ጋሻ እና መከታነት ተማምኜ ከቤቴ ወጣሁ:: ለዚያ ጓደኛዬ ስደውልለት «ትናንት እያሰብኩሽ ነበር:: እኔና ቤተሰቤ ባንቺ ጉዳይ ላይ ተወያየንና በጉዳዩ ጸለይንበት:: በመጨረሻም ሁለት የመታወቂያ ካርዶች ላንቺና ለልጂሽ ለማውጣት ወሰንን:: እባክሽን ያንቺን እና የልጅሽን ፎቶግራፎች ላኪልኝ:: በተቻለ መጠን በፎቶአችሁ ላይ ራሳችሁን ቀየር ለማድረግ ሞክሩ:: ደግሞም አፍጥኝው» አለኝ::

ይህንን ስሰማ በደስታ ልዘልል ምንም አልቀረልኝም ነበር:: ጌታ ሆይ ትናንት አንተ በነገርከኝ ሰዓት መታወቂያውን ሊያወጡልኝ ተስማሙ ማለት ነው፤ የመታወቂያ ካርድ ስለ አንድ ሰው ማንነት፣ ሃይማኖት፣ ሞያ፣ የምርጫ ክልል፣ የልደት ቀንና ቦታ፣ ዕድሜ፣ ክብደት እና ቁመት ወዘተ የሚይዝ ነው:: ከዚህም በላይ ደግሞ የባለ መታወቂያውን ፎቶግራፍ ይይዛል:: አንተ ባታጸናቸው ኖሮ እንዴት ችግሩን እያወቁ ሊያወጡልኝ ይወስኑ ነበር? አመሰግንህ ዘንድ እግርህ ሥር እደፋለሁ:: እነሆ ድምፅህን ሰማሁት፤ እንዲህም አልከኝ «አይዞሽ ኃይልና ጽናትን እኔ እሰጠዋለሁ፤ እርሱም ላንቺ እና ለልጅሽ ገና ፓስፖርቱን ጨምሮ ያወጣል»::

ይህንን ሰው ለማግኘት የተቀጣጠርንበት ቦታ ሄድኩ:: የሚኖረው ከካይሮ ሰባ ኪሎ ሜትር ርቆ በሚገኝ ከተማ ነው:: እዚያ ስደርስ ክርስቲያናዊ በሆነ አቀባበል ተቀበለኝ:: ወለም ዘለም የማያውቅ ሰው ሆኖ አገኘሁት:: የሁለታችንን ፎቶ ግራፎች ሰጠሁትና በሁለት ቀናት ውስጥ መታወቂያውን ሊሰጠኝ ቃል ገባልኝ:: ከዚያም ወደ ካይሮ ተመለስኩ:: እንዴት ነገሮች ሁሉ በአንድ አፍታ ተለዋወጡ:: በካይሮ ጎዳናዎች ላይ ያለ ፍርሃት እጓዝ ነበር:: የምጠቀመውም የሕዝብ ማመላለሻ ትራንስፖርት ነበር:: ፍርሃት ከእኔ ርቋል:: የእግዚአብሔርም ሰላም በውስጤ ነግሦአል::

ነገሮችን በጉጉት ነበር የምጠብቃቸው:: አዲሱን መታወቂያ የማገኝበትን ቀንና ሰዓት መቁጠር ጀመርኩ:: አይቀርምና ቀኑ ደረሰ፤ ከዚያም ሰውዬው ወዳለበት ቦታ አመራን:: ሰውዬው ቃሉን አክብሮ ሁሉንም መታወቂያዎች እጄ ላይ አስረከበኝ:: እግዚአብሔር ካዘዘ ማን እምቢ ይላል! እግዚአብሔርን አመሰገንኩት:: ያ ጓደኛዬ «ወደ ውጭ መሄድ ትፈልጊያለሽ?» ሲል ጠየቀኝ:: «አዎን ወደ ውጭ ለመውጣት አስባለሁ፤ ግን ይህንን ለምን ጠየቅከኝ?» ብዬ መልሼ ጠየቅኩት:: «ላንቺና ለልጅሽ ሁለት ፓስፖርቶችን ለማግኘት አስቤያለሁ፤ ነገር ግን ከሌላ ከተማ ነው:: ትስማሚያለሽ?» ሲል ጠየቀኝ:: «እስማማለሁ እንጂ» አልኩት:: «አስፈላጊ ቅጻ ቅጾችን ሞልቼ ለመጨረስ አንድ አሥር ቀን ያህል ስጭኝ» አለኝ:: እኔም አመሰገንኩት::

ወደ ቤቴ ስመለስ ልቤን ወደ አምላኬ አነሣሁ:: «ጌታ ሆይ አመሰግንሃለሁ:: አንተን ብቻ አመሰግናለሁ:: በሕይወቴ ዘመን ሁሉ አንተ ለቃልህ ታማኝ ነህ:: አንተ ሁሉን በእጅህ ታደርጋለህ:: ለእኛ ካንተ ሌላ የሚያስፈልገን ነገር የለም:: ራሳቸውን ላንተ ያስረከቡ ሰዎች ብቻ ናቸው አንተ የሰዎችን ሕይወት በሚገባ የምትመራ መሆኑን የሚያውቁት:: ሁሉንም በበረከት ስትጎበኝ አንተ ፈጣን ነህ:: ትናንት ሲፈራኝ እና ሲሸሸኝ የነበረውን ሰው በደቂቃዎች ውስጥ ለወጥከውና ለእኔ መታወቂያ ከማውጣትም አልፎ ፓስፖርት እንዳገኝ የሚተጋልኝ ሰው ሆነ::»

ወደ ቤቴ ተመለስኩና ወደ እስክንድርያ ለመሄድ ወሰንኩ:: የግል ትራንስፖርት አያስፈልገኝም:: ግሬይሃውንድ በተባለው የሕዝብ አውቶቡስ ተሳፈርን:: አምላኬ ሆይ አንተ ከፊቴ ቀድመህ መንገዱን እየመራኸኝ ነበር:: የምሄደው ካንተ ኋላ ኋላ ነው:: ሰላምና ደስታ፣ ጥበቃ እና ክብካቤ ካንተ ዘንድ ናቸው::

እስክንድርያ ከተማ በባሕሩ ዳር ወደሚገኘው እና ጸጥ ወዳለው አፓርትመንት ጉዞ ጀመርን:: ወቅቱ ታኅሳስ በመሆኑ አየሩ ቀዝቃዛ ነው:: በአካባቢው ማንም አልነበረም:: አንተ ግን በልቤ እና በነፍሴ ውስጥ አብረህኝ ነበርክ::

ዐሥር ቀናት አለፉ:: መቼም ፓስፖርቱ አሁን ተዘጋጅቶ ማለቅ አለበት:: የሚያወጣልንን ሰው ለማግኘት ሄድኩ:: በሕጉ መሠረት በሁለት ምስክሮች አስመስክሮ ፓስፖርቱን አዘጋጅቶ ጠበቀኝ:: አብረን ፓስፖርቱን ለመቀበል ወደሌላው ከተማ ተጓዝን:: ፓስፖርቱን ጨርሰው ማኅተም አድርገው ሰጡን:: እግዚአብሔር ሆይ አንተ መጋቢ፣ አንተም ወሳኝ ነህ:: እንዴት ሊሆን ይችላል ብሎ መደነቅ አያስፈልግም:: ይህ የአንተ ተአምር ነውና:: ለስምህ ክብር ምስጋና ይሁን::

አዲሱን መታወቂያ እና ፓስፖርት ይዘን ወደ እስክንድርያ ተመለስን:: አሁን ጥያቄው የመግቢያውን ቪዛ እንዴት እናገኘዋለን የሚለው ነበር:: ደግሞስ ለቪዛ ማመልከት ያለብን የትኛው ሀገር ነው? እያልኩ አስብ ነበር:: ካይሮ ውስጥ በቆየሁባቸው ሃምሳ ቀናት አንዱን ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄድኩ:: እዚያ አንድ ካህን አገኘሁ::

ቤታቸው ጋበዙኝና ሄድኩ:: «ለመንግሥት ደኅንነት እጅሽን መስጠት አለብሽ፤ በሽሽት መኖር የለብሽም፤ ባንቺ የተነሣ በእሥር የሚሰቃዩ ብዙ ሰዎች አሉ» ሲሉ መከሩኝ:: እኔም ረጋ ብዬ «ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፤ እኔ ምንም ማድረግ አልችልም» አልኳቸው:: «አንቺን ለመያዝ ባለመቻላቸው መናደዳቸውን ታውቂ





ያለሽ? በዚህ ምክንያትም አንቺን የሚያውቅሽንም ሆነ ካሴቱን የያዘውን ሁሉ ከመያዝ አይመለሱም» በማለት ይበልጥ ሊያስፈራሩኝ ሞከሩ:: «በእጃቸው እንደማልወድቅ እግዚአብሔር ቃል ገብቶልኛል:: እኔ የተላክሁብት ሌላ ተልዕኮ አለኝ፤ እርሱ ሁሉን ላንቺ አዘጋጃለሁና አትፍሪ ብሎኛል »አልኳቸው::

የምቀልድ ስለመሰላቸው የለበጣ ፈገግታ አሳዩኝና «እኔ ግን በቶሎ እጅሽን ብትሰጭ ሁኔታው የተሻለ ይሆንልሻል ብዬ እመክርሻለሁ» አሉኝ:: እኔም «ምናልባት ቢይዙኝና ቢደበድቡኝ ያን ጊዜ በመከራው ተገፋፍቼ በገንዘብ የሚረዱኝንና ያስጠለሉኝን ሰዎች ስም እነግራቸው ይሆናል» አልኳቸው:: ልክ ይህንን ስናገር ደነገጡና «በጭራሽ የአንዱንም ስም መንገር የለብሽም፤ ማንኛውም ሰው አንቺ ባለ ጥሩ ደረጃና ባለ ጥሩ ደመወዝ እንደነበርሽ ያውቃል:: ካጠራቀምኩት ገንዘብና ከመኪናዬ ሽያጭ ነው የተጠቀምኩት ማለት ነው ያለብሽ» አሉኝ::

«አዲስ መታወቂያ እና አዲስ ፓስፖርት እንደምናገኝና ከሀገር የምንወጣበትንም መንገድ እንዳመቻቸልን እግዚአብሔር ነግሮኛል» ስላቸው «ያንን ማድረግ ከቻልሽማ ወደ አንዱ የአውሮፓ ሀገር የመግቢያ ቪዛ አገኝልሽ ነበር» አሉኝ:: እጃቸውን ስሜ ከዚያ ቤት ወጣሁ::

«ወደ አንዱ የአውሮፓ ሀገር የመግቢያ ቪዛ አገኝልሻለሁ» ያሉኝን ነገር ሳስበው ጎሊናዬን መታኝና መልሼ ደወልኩላቸው:: ከዚያም ፓስፖርቱን ልሰጣቸው ተቀጣጠርን:: «አቤቱ ጌታ ሆይ ሰማይና ምድር ያልፋል፣ ቃልህ ግን አያልፍም፤ አላቋርጥም ስላንተ እናገራለሁ፤ ዐውጃለሁ፤ ቃልህ የማይታበል መሆኑን እኔው ራሴ ደርሶልኝ አይቼዋለሁና:: እንዳውቅህ፣ እንድወድህና በአንተ ልቡናዬን ሁሉ እንዳሳርፍ አድርገህኛልና አመሰግንሃለሁ::

ካወቅኩበት ጊዜ በፊት ላውቅህ እፈልግ ነበር:: አንተ ግን ሁሉን የምታደርግበት የራስህ ጊዜ አለህ:: አንተ ምንጊዜም ትክክለኛውን ጊዜ ትመርጣለህ::

በነጋታው የግሬይሃውንድን አውቶቡስ ይዘን ወደ ካይሮ አመራን:: የሚገርመው ነገር ፍተሻው በየኬላዎቹ ላይ ተጧጡፏል:: ነገር ግን ፖሊሶቹ የሚፈትሹት የግል መኪኖችን ብቻ ነበር:: መቼም ደፍሬ በአውቶቡስ የምሄድ አይመስላቸውም:: አሁንም ፈርቼ የምሸሸ፣ የምደበቅ መስሏቸዋል:: ወይም ራሴን በመኪና የዕቃ መጫኛ ውስጥ ሠውሬ ለማለፍ የምጥር አድርገው ይገምታሉ::

ለምን? ምክንያቱም አንተን አያውቁማ!

እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል[38] የሚለውን አልተረዱማ! የቃሉንም ትርጉም ፈጽሞ አያውቁትም:: እኔ ግን በአንተ ፈቃድ ዐወቅኩት:: ኖርኩበትም:: ድምጼንም ከፍ አድርጌ «እግዚአብሔርን ቸር እንደሆነ ቅመሱ፣ እዩም[39]» ለማለት ይዳዳኛል::

ካይሮ ውስጥ በጠራራ ፀሐይ ቤተ ክርስቲያን እሄዳለሁ:: ከጓደኞቼ ጋር እገናኛለሁ:: ማንም ግን አያየኝም ነበር:: በመጨረሻም ለካህኑ ፓስፖርቶቻችንን ሰጥቻቸው ወደ እስክንድርያ ተመለስኩ:: ታክሲው ሰባት ሰዎች እስኪሞላለት ጠበቀና ተንቀሳቀሰ:: እኔና ልጄ ከፊት ከሾፌሩ አጠገብ ነበር የተቀመጥነው:: የተወሰነ መንገድ ከተጓዝን በኋላ በአንዱ የፍተሻ ኬላ ደረስንና ቆምን:: ፈታሹ በሩን ከፈተና ከኋላ ያሉትን ብቻ አየት አድርጎ እጁን በማወዛወዝ እለፉ አለ:: የሰው ዘር ሁሉ ተስፋ ለሆነው ለመድኃኔዓለም ክብር ምስጋና ይሁን::

1990 ዓም ገባ:: ባለፉት ጊዜያት ላደረግክልኝ ሁሉ በፊትህ ቆሜ ምስጋና አቀረብኩ:: 1989 ዓም የሆነውን ሁሉ እንደ ፊልም በኅሊናዬ አየው ነበር:: እንዴት ያለ የውጣ ውረድ ዘመን ነበር:: ነገር ግን በነገሮች ሁሉ ያንተ ክንድ ይጠብቀኝ፣ ያድነኝም ነበር:: ስምህ ቅዱስ ነው[40]፤ ካንተ ጋር እና ላንተ ካልሆኑ የእኔ የሕልውናዬ ዕለታት ምን ዋጋ አላቸው:: አንተን ለማዬት እጓጓ ነበር:: በዚህ ዓለም የተቆረጠልኝ ዘመኔ የሚያልቀው መቼ ይሆን? እኔ ለዚህ ዓለም እንግዳ ነኝና[41]::

«ጌታ ሆይ ወደ አንተ ውሰደኝ:: እናት የምታጠባውን ልጅ እንደምትከባከብ ሁሉ የሚከባከበኝ ማነው[42]? ለትኬት የሚሆነውን ገንዘብ ከየት ይሆን የማገኘው? ፎቶዬ በመላዋ ግብጽ ተለጥፏል:: ታድያ እንዴት ይሆን በአውሮፕላን ተሳፍሬ የምጓዘው:: ስሜስ አዲስ ስም ነው:: ፎቶዬን ግን ማንም ሊለውጠው አይችልም:: ታድያ የአውሮፕላን ማረፊያውን ፍተሻ እንዴት ይሆን የማልፈው? እርግጥ ነው ለእኔ የማይቻል ለአንተ ይቻላል[43]:: ተስፋዬ አንተ ነህ፣ ጭንቀቴንም ሁሉ በእግርህ ሥር አራግፌያለሁ::» እንዲህ እያልኩ በልቤ ስቃትት «አትፍሪ፤ ወደ እኔም ተመልከቺ፤» የሚል ድምፅህን ሰማሁ:: ያን ጊዜ ውስጤ ተረጋጋ:: አንተ ምንጊዜም ታጽናናኛለህ፣ ታበረታኛለህም::

38. ሮሜ.8÷31
39. መዝ.33÷8
40. ሉቃ.1÷50
41 ዕብራ.11÷13፤መዝ.38÷12
42 . ኢሳ.66÷10-13
43. ሉቃ.1÷37





በዚያ ሌሊት እግዚአብሔር ትኬቶቹን ሲሰጠኝ በራእይ አየሁ:: ስነቃ በእግዚአብሔር ፊት ለምስጋና ቆምኩ:: አመሰግንሃለሁ፣ አከብርሃለሁ፣ አወድስህማለሁ፣ ደግሞም ለድካሜ ይቅርታን ካንተ አለምናለሁ::

ቀናቱ አለፉ:: ቪዛውን የምቀበልበት ቀን ደረሰ:: ያንን የተለመደውን ግሬይሃውንድ አውቶቡስ ይዤ ወደ ካይሮ ሄድኩኝ:: እንደተለመደው የመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች መንገዱን ዘግተው ይፈትሻሉ:: ማንም ግን ሊያየኝ አልቻለም:: ቪዛውን አገኘሁ:: ካህኑ «3000 ፓውንድ አዘጋጅቼልሻለሁ:: ገንዘቡ ያስፈልግሻል ብዬ አምናለሁ:: እንደዚሁም ለጉዞሽ እንዲሆንሽ 1000 ዶላር ተዘጋጅቶልሻል» አሉኝ:: እኔም 3000ውን ፓውንድ አልወሰድም:: በሰማይ ያለው አባቴ ትኬቱን ሲሰጠኝ አይቻለሁና እባክዎን ትኬቱን ይግዙልኝ» አልኳቸው:: እርሳቸውም በዚህ ተስማሙ:: እኛም አመስግነን ወደ እስክንድርያ አመራን::

በሕዝብ ማመላለሻ ትራንስፖርት ፊት ለፊት ተቀምጠን ነበር የተመለስነው:: ፍተሻው ቀጥሏል:: አያዩንም እንጂ ይፈልጉናል:: ውስጤን አረጋግተህ ፍርሃተን አውጥተህ የጣልክልኝ አምላክ ምስጋና ይግባህ::

ወደ እስክንድርያ ከመመለሴ በፊት አንድ ጓደኛዬን ለማግኘት ፈልጌ ነበር:: እርሷ እግዚአብሔር ልቡናዋን ብርሃን ያደረገላት ጥሩ ክርስቲያን ነበረች:: ብዙዎች ፈርተው በራቁኝ ጊዜ ልቧን እና በርዋን የከፈተችልኝ ሰው ናት:: ከአንድ ወር በላይ ለሆነ ጊዜ ከጎኔ ሳትለይ በቤቷ አስጠልላኛለች:: በፍቅር ስለተከባከበችኝ እናቴ ትመስለኛለች:: ባልዋ እንደ ወንድሜ፤ ልጆቿ እንደ ልጆቼ ነበሩ:: ልሂድና ልጠይቃት ይሆን? ብዬ እግዚአብሔርን ጠየቅኩት:: እርሱም «ሂጂ ጠይቂያት:: አትፍሪ» አለኝ:: ከዚያም ወደ ቤቷ አመራሁ:: ገና በሩቁ ስታየኝ ሮጣ መጥታ በፍቅር ተጠመጠመችብኝ:: ከእርሷ ጋር አንድ ሰዓት ያህል ቆየሁ::

በጨዋታችን መካከል ወንድሟ «ምን እያሰብሽ ነው ታድያ፤ ለምን ከካይሮ ውጭ በሚገኝ ሌላ አውሮፕላን ማረፊያ አትጠቀሚም:: ደግሞም ሌላ የትራንስፖርት መንገድ ተጠቅመሽ ወደ አውሮፕላን ማረፊያው ሂጅ እንጂ በቀጥታ ወደ መዳረሻሽ አትብረሪ» ሲል የሚገርም ሃሳብ ለገሰኝ:: ይህ የእግዚአብሔር መልእክት መሆን አለበት:: ወደዚህ ቤት ለመምጣት ያለ ምክንያት ልቤን አላነሣሣኸውም፤ የመንገዴን ነገር ልታመለክተኝ ነው ማለት ነው::

እንዴት ታላቅ ነህ፤ እንዴትስ ድንቅ ነህ፤ ልቤ እና ነፍሴ ፍቅ

ርህን ለዓለም ያውጃሉ:: ሃሳቤ እና ኅሊናዬ ባንተ ታድሰዋል:: ሰው ሁሉ ያንተ ጥበቃ ከሚታሰበው እና ከሚጠበቀው በላይ መሆናቸውን ያውቅ ይሆን?

ሃሳብ ሁሉ አይደርስብህም:: የሰማይ ወፎችን፣ የባሕር ዓሦችን፣ ሌላው ቀርቶ የምድር ትላትልን ሳይጠይቁህ የምትመግባቸው አንተ ነህ:: ታድያ ዘመናቸውን እና ሕይወታቸውን ሙሉ ላንተ ያስረከቡህን ልጆችህንማ እንዴት አትመግባቸውም? ምንጊዜም ከእኔ አለመለየትህን እንድረዳ ታደርጋለህ፤ ጠፍቼ የነበርኩት ልጅህ እኔ እንደ ሆንኩ ይሰማኛል:: አንተ በፍቅርህ፣ በቸርነትህ እና በደግነትህ አጥለቅልቀህኛል::

እስክንድርያ እስክንደርስ ድረስ የጓደኛዬ ወንድም የመከረኝ ምክር በኅሊናዬ ይመላለስ ነበር:: ይህንን የመሰለ መንገድ ያዘጋጀልኝን እግዚአብሔርን አመሰገንኩት:: ከሁለት ቀናት በኋላ ካህኑ ደወሉልኝና «ነገ ዕቃዎችሽን ሁሉ ይዘሽ ነይ:: ሁሉም ነገር ተዘጋጅቶልሻል» ብለው አበሠሩኝ:: በአካል ስንገናኝ ደግሞ «ከካይሮ አውሮፕላን ማረፊያ ለመነሣት እንዳልፈለግሽና ከሌላ አውሮፕላን ማረፊያ ለመሣፈር ማሰብሽን የሆነ ነገር በጆሮዬ ሽው አለኝ:: ስለዚህም ጉዞውን ከፋፍለን እናቀናጀው ማለት ነው:: ወደ ጉዞሽ መጨረሻ በሌላ ሀገር በኩል ተሸጋግረሽ ብትሄጅ ይመረጣል» በማለት የሚደነቅ ነገር ነገሩኝ::

ይህንን ነገር በድጋሚ ስሰማው የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን አረጋገጥኩ:: አንተ ለእኔ ከራሴ በላይ ትቀርበኛለህ:: እኔ ያለሁት ባንተ ነው:: የወይኑ ቅርንጫፍ ነኝና:: ሁላችንስ የክርስቶስ አካል አይደለንምን?[44] ጌታ ሆይ ያንተ ጥበቃ እንዴት ምቹ ነው፤ አንተ ሁላችንንም ትመግበናለህ:: በነገር ሁሉም ትመራናለህ:: ከተቀደሱት እጆችህ ትኬቱን ተቀብያለሁ፤

ከጸለይን በኋላ ከካህኑ ዘንድ የመሰነባበቻ ግብዣ ተጋበዝን፤ ካይሮንም ተሰናበትኳት:: ካይሮን ካሁን በኋላ ደግሜ የማያት አይመስለኝም::

ሀገሬን እጅግ በጣም እወድድ ነበር:: በርሷ ውስጥ መኖርም እጅግ ደስ ይለኝ ነበር:: ነገር ግን እንዳንተ ፈቃድ እንጂ እንደ እኔ ፈቃድ አይሁን:: መከራ በከበበኝ ቁጥር ስንት ጊዜ ወደ አንተ ጮህኩ? ሕዝብህን እስራኤልን ከግብጽ አውጥተህ እንደመራሃቸው፣ እኔን እና ልጄንም ምራን:: በቀጣዩ ሰንበትም ወደ መጨረሻው መዳረሻዬ በባቡር አመራሁ::

44. 1ኛቆሮ.12÷27





በአውሮፕላን ወደምንሳፈርበት ከተማ ደረስን:: እዚያም ጥቂት ቀናትን አሳለፍን:: ቀናቱ በፍጥነት ነበር የሚጓዙት:: በእግዚአብሔር ፊት ቆሜ ሙሴ የጸለየውን ጸሎት ጸለይኩ:: «አንተ ከኛ ጋር ካልወጣህስ ከዚህ አታውጣን[45]» ያን ጊዜ እግዚአብሔር «አትፍሪ፤ ርምጃሽን ሁሉ እጠብቃለሁና» ሲል በፍጥነት መለሰልኝ:: እኔም «አቤቱ ወደ ጸጥታው ወደብ ምራኝ» አልኩት::

አውሮፕላን ማረፊያው በሰዓቱ ነበር የደረስነው:: ከልጄ ጋር ተያይዘን ፓስፖርት ወደሚመረመርበት ቢሮ ገባን:: በሃሳብ ብዛት ራሴን ልስት ትንሽ ነበር የቀረኝ:: «አቤቱ የቀረችኝን ይህችን ወሳኝና ከባድ ሰዓት እባክህን ርዳኝ» ብዬ እየጸለይኩ ነበር:: በፓስፖርት ፈታሹ የደኅንነት ሹም ጠረጴዛ ላይ "ትፈለጋለች" ተብሎ ፎቶዬ ተለጥፏል:: ሹሙ ፓስፖርቴን እና ትኬቱን ተቀበለና ካገላበጠው በኋላ ለምን እንደምወጣ ጠየቀኝ:: ለሕክምና እንደምሄድና እዚያ ዘመዶቼ ስላሉ ከእነርሱ ጋር እንደምሰነብት እንደ ቀልድ አድርጌ ነገርኩት:: እርሱም የመውጫ ቪዛውን መታና መሄድ ትችያለሽ ብሎ አሰናበተኝ:: ልጄ ከኔ በኋላ ቆማለች:: የርሷም ቪዛ ተመታላትና ወደ መሣፈሪያው ቦታ አመራን:: እየሆነ ያለው ነገር ሁሉ ማመን የምችለው ነገር አይደለም::

ከደቂቃዎች በኋላ ስሜን በማይክራፎን ጠሩና ፓስፖርቴን ይዤ እንድመጣ ተናገሩ:: ልቤ በኃይል ሲመታ በዙርያዬ ካሉት ድምፆች ሁሉ እርሱ ብቻ የሚሰማ ይመስል ነበር:: መቆም ተሣነኝና ተቀመጥኩ:: ያን ጊዜ በልቡናዬ ወደ እግዚአብሔር ጮኼ «ጌታ ሆይ ቃል ገብተህልኝ ነበር:: በእነዚህ ጨካኝ ሰዎች እጅ እንደማልወድቅ ቃል ገብተህልኝ ነበር:: አሁንም እንደቃልህ እንደሚሆን አምናለሁ» እያልኩ እጸልይ ነበር:: ወዲያውም «በሰላም ትጓዣለሽና አትፍሪ» የሚለውን የጌታዬን ድምፅ ሰማሁት::

ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ፓስፖርት መርማሪው ሹም ወደ እኛ መጥቶ ምንም ቃል ሳይናገር ፓስፖርቴን መለሰልኝ:: ወደ አውሮፕላኑ እንድንሳፈር ስንጠራ ከደስታችን ብዛት እኔና ልጄ ዕቃችንን ረስተን ነበር የገባነው::

ለኛ በዚያ ወቅት ዋናው ነገር ከዚያ ሀገር መውጣታችን ነበር:: አሁንም ስማችን በድጋሚ ተጠራ:: ከድንጋጤዬ የተነሣ ተዘለፈለፍኩና መልስ መስጠት አቃተኝ:: ልጄ የሆነውን ለማየት ወጣች:: ለካ ረስተነው የነበረውን ዕቃችንን እንድንወስድ ኑሯል የጠሩን::

45. ዘጸ.33÷15

ጥቂት እና አስጨናቂ ደቂቃዎች አለፉ::

ከዚያም አውሮፕላኑ ተንቀሳቀሰ::

አኮበኮበና ተነሣ::

እናም እየራቀ......እየራቀ......
እየራቀ........እየራቀ ...........ሄደ::

✝ ተፈጸመ ✝

## የባለ ታሪኳ ማስታወሻ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤ አሜን፡፡
ስቃወመው እና ሳሳድደው የነበረውን እምነት ዛሬ በጽናት እንድመሰክርለት ጸጋውን የሰጠኝ ጌታ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ፡፡ ለእግዚአብሔር አብ እና በመከራችን ወቅት ረድኤቱ ለማይለየን፣ እኔን ትጉቱ ባርያውን ለእናንተ መጽናኛ እሆን ዘንድ ለፈቀደ ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምስጋና ይገባል፡፡ ይህንን ሁሉ ያደረገልኝ ስለ በጎ ሥራዬ አይደለም፤ ለእናንተ ድኅነት ሲባል በእኔ ላይ ባደረው በእግዚአብሔር ጸጋ ምክንያት እንጂ፡፡ ዘወትር እግዚአብሔርን አክብሩት፤ በእኔ ያደረገውን ድንቅ ሥራውንም አስቡ፤ እኔን ሰው ሰብኮ አልመለሰኝም፡፡ እምነቴን ያገኘሁት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ከራሱ ነው፡፡ ዛሬም ዘወትርም ክብር ምስጋና ለእርሱ ይሁን፤ አሜን፡፡
ይህንን ምስክርነት የምጽፈው በእግዚአብሔር ፊት ነው፡፡ እንደማልዋሽ እርሱ ያውቃል፡፡ የእግዚአብሔር ሥራው እንዴት ድንቅ እንደ ሆነ፤ በእኔም ላይ ያደረገውን ድንቅ ሥራ እመሰክራለሁ፡፡
ጌታ ሆይ ስምህን ለመስደብ አንደበቴ ፈጣን እና ያልታረመ ነበር፡፡ አንተ ግን የአንተ በግ አደረግከኝ፡፡ ከአሁን በኋላ ራሴን ለአንተ አሳልፌ ሰጥቻለሁ፡፡ አንተን ለዓለም እሰብካለሁ፡፡ ከአሁን በኋላ የእኔ ሳይሆን ያንተ ፈቃድ ይሁን፡፡ ሁለመናዬ ያንተ ነው፡፡ ይህ መሆኑ ብቻ ለእኔ በቂዬ ነው፡፡ ሌላ ተጨማሪ ነገር አልጠይቅህም፡፡ ከፈቃድህ ውጭ አንዳች ነገር አደርግ ዘንድ አሳልፈህ አትስጠኝ፡፡ እባክህን በልቡናዬ ያለው ፍቅርህ ይምራኝ፡፡
መስማትንስ በጆሮዬ ሰምቼ ነበር፤ አሁን ግን ዓይኔ አየችህ፤
(ኢዮብ. 42$25)

አማኑኤል ማተሚያ ቤት

ዋጋ 25 ብር